**ግብረገብነትን የተራቆቱት ማስታወቂያዎቻችን**

ኃይሉ አሰለፍ ገብሬ

**የጥፋቶች ሁሉ ትልቁ ጥፋት ነገን አለማሰብ ነው**

መስፍን ጌታቸው

**አነግ ከሁለት ያጣ ጎመን**

ደረጀ ይመር


መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 38 ጥር 2011 ዓ.ም ዋጋ 14.99


እንኳን ለብርሃን ልደቱ አደረሳችሁ!



# ዜግነት በብሔር ላይ ይሰለጥን ይሆን ?

## የቅንጅት ትንሳኤ በኢትዮጵያ?



"ኢዴፓ የግለሰብ ንብረት የመሆኑ ጉዳይ አክትሟል"

ዶ/ር ጫኔ ከበደ

"ሰማያዊ የከሰመው ለውህደቱ ቁርጠኛ አቋም ስለያዘ ነው"

አቶ የሺዋስ አሰፋ


"ከቅንጅት መፈራረስ ብዙ ተምረናል"

አቶ ቸኮል ጌታነህ


"የተገመደ ተስፋና የጋራ ሀገር ስላለን መከፋፈሉ አይጠቅመንም"

አቶ አንዷለም አራጌ

ግዮን
ቅጽ 1 ቁጥር 38 ቅዳሜ ታህሳስ 27 2011 ዓ.ም



አቶ አንዷለም አራጌ



አቶ ቸኮል ጌታነህ



ዶ/ር ጫኔ ከበደ



አቶ የሺዋስ አሰፋ

# የቅኝጅት ትኝሳሌ በኢትዮጵያ? 14-18


4 የውህደቱ ሒደት በአንክሮ ሊጤን ይገባል

5 ዜግነት በብሔር ላይ ይሰለጥን ይሆን ? የለውጥ ንፋስ በፓርቲዎች መንደር
መለክ ቢ..

8 ከኤርትራ መንግሥት ድንበር መዝጋት ጀርባ ምን አለ?
ተስፋዬ ሽብሩ

9 አፋር አሁንም አላረፈችም
ሔማስ ታፈረ

10 ግብረገብነትን የተራቆቱት ማስታወቂያዎቻችን
ኃይሉ አሰለፍ ገብሬ

11 ኦነግ ከሁለት ያጣ ጎመን
ደረጀ ይመር

19 የጥፋቶች ሁሉ ትልቁ ጥፋት ነገን አለማሰብ ነው
መስፍን ጌታቸው

21 ስለሌላው ነጻነት ከማሰብ በፊት...!?
ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

23 የአሰላሳዮቹ አብዮት
ተሾመ ሽፈራው

25 ሲዊዲናዊው ጀነራል በኢትዮጵያ
ብሩክ መኮንን

27 «የመሸበት የእግዜር እንግዳ!»
ሱለይ አደም

40-40-20 ኢትዮጵያዊ የአፓርታይድ ሥርዓት
አንዱአለም ቡኩቶ ገዳ

28 የታህሳስ ወር በታሪክ ውስጥ


ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ
ጥር 04
ይጠብቁን!




ቁጥር 37 ዕትም

## ከዲያስፖራ ትረስት ፈንድ በሚልየን የሚቆጠር ገንዘብ ተሰበሰበ



ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው ልማት ተሳታፊ እንዲሆኑ በማሰብ በቀን ከሚጠጡት ማኪያቶ አንድ ዶላር ለሀገራቸው አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ጥሪ ማቅረባቸው ይታወሳል:: በዚህም መሰረት ከኢትዮጵያውያን አንድ ሚልየን ዶላር ለመሰብሰብ ታቅዶ የዳያስፖራ ትረስት ፈንድ ተቋቁሞ ስራ የጀመረ ሲሆን 1 ሚልየን 569 ሺህ 412 ዶላር መሰብሰብ ተችሏል:: ከዳያስፖራው በትረስት ፈንድ አማካኝነት የሚሰበሰበው ገንዘብ በሀገሪቱ ማኅበራዊ ተቋማትን ለመገንባት ታስቦ የታቀደ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በውጪ ከሚኖሩ ጋር ባደረጉት ውይይት ዳያስፖራዎች መናገራቸው የሚታወስ ሲሆን ኢትዮጵያውያኑም ለሀገራቸው ጥሪ ፈጣን ምላሽ ሰጥተዋል::

## ሲጓተት የቆየው የብሔራዊ ቴአትር ህንፃ ግንባታ ሊጀመር ነው

ከ10 ዓመታት በላይ ሲጓተት የቆየው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ሕንፃ ግንባታ ጥር 15 ቀን 2011 ዓ.ም ከተቋራጭ ድርጅቱ ጋር ውል ተካሂዶ ወደ ሥራ ሊገባ ነው::

የቴአትር ቤቱ የግዥ፣ የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ እዮብ ታምሩ እንደገለፁት ዘመናዊው ባለ አራት ፎቅ የቴአትር ቤት ሕንፃ ግንባታ ጨረታውን ካሸነፈው አፍሮ ፅዮን ኮንስትራክሽን ድርጅት ጋር ውል በመግባት ግንባታው እንደሚጀመር አስታውቀወል:: ግንባታው 1.4 ቢሊየን ብር የሚፈጅ ሲሆን በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል::

ግንባታው የሚካሄደው በአሁኑ ወቅት እንደ ቢሮ በሚያገለግለው ቦታ ላይ ስለሆነ ሌላ ቢሮ በመከራየት ለግንባታው ቦታው መለቀቁን ኃላፊው ገልፀዋል:: የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር የተገነባው ከ64 ዓመት በፊት ሲሆን 1 200 ተመልካች የመያዝ አቅም አለው::

## በቡራዩ ከተማ በተነሳ ግጭት 109 ሰዎች ክስ ተመሰረተባቸው

ጠቅላይ አቃቤ ሕግ በቡራዩ ከተማ ተከስቶ በነበረው ግጭት 109 ተጠርጣሪዎች ላይ ክስ መመስረቱን አስታወቀ:: የፌዴራል ጠ/አቃቤ ሕግ መስከረም 4 ቀን 2011 ዓ.ም በቡራዩ ከተማ በተፈፀመው ጥቃት በተሳፊነት በጠረጠራቸው 109 ግለሰቦች ላይ ክስ መመስረቱን ገልጿል::

ከተጠርጣሪዎቹ መካከል 81 የተያዙ ሲሆን ሃያ ስምንቱ የፍርድ ቤት ማዘዣ ወጥቶባቸው እየታደኑ ነው ተብሏል:: የቡራዩን ጥቃት ተከትሎ በአዲስ አበባ ከተማ በታየው የፀጥታ ችግር በማነሳሳት እና በተሳታፊነት የተጠረጠሩ ግለሰቦች ላይ ክስ ተመስርቷል::

በተመሳሳይ በሐዋሳ ከተማ በወላይታና ሲዳማ ብሄረሰቦች መካከል ግጭት ለመፍጠር የተንቀሳቀሱና ጥቃት በመፈፀም የተጠረጠሩ ከ90 በላይ ግለሰቦች ላይ ክስ መመስረቱንም የፌደራሉ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ አስታውቋል:: ከተጠርጣሪዎቹ መኻከል የሐዋሳ ከተማ የቀድሞ ከንቲባና የፖሊስ አባላትም ይገኙበታል::

## የሲቪክ ማኅበራት ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጀ

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት አዋጅ ረቂቅ ማሻሻያ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት መላኩን የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ አስታወቀ:: ይህ ረቂቅ የማሻሻያ አዋጅ በቅርቡ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ በመፅደቅ ወደ ሥራ ይገባል ተብሎ ይጠበቃል:: ረቂቅ አዋጅ የመደራጀት መብትንና የፀረ ሽብር አዋጅንም ለማሻሻል ተዘጋጅቶ ያለቀ መሆኑንና በቅርቡ ለሚመለከተው አካል እንደሚቀርብም የተገለፀ ሲሆን በተጨማሪም የሥነ ሥርዓትና ማስረጃ አዋጅ፣ የሕገወጥ የሰዎች ዝውውር አዋጅ፣ የንግድ ሕግ የጦር መሳሪያ አያያዝና አስተዳደር አዋጅ የምርጫ ሕግ የመረጃ ነጻነትና የመገናኛ ብዙኃን አዋጅ እና የኃይል አጠቃቀም አዋጅን ለማሻሻል የተዘጋጀ ረቂቅ አዋጆች በውይይት መድረኮች ዳብረው እንደሚቀርቡ ለምክር ቤቱ አስረድተዋል::

## የህዳሴው ግድብ ግንባታን ለማፋጠን እየተሠራ ነው



የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ግንባታ ለማፋጠን የሚያስችል ስምምነት ተፈረመ:: ጂኢ ሀይድሮ ፍራንስ በቅድሚያ እንዲያመነጩ ታስበው ዲዛይን የተደረጉትን ሁለት ተርባይኖችን ጨምሮ አምስት ኃይል ማመንጫ ዩኒቶች ኮሚሌክስ ከተባለ ድርጅት ጋር በጥምረት ለማምረት ለመግጠምና ለመፈተሽ የ53 ነጥብ 9 ሚሊዮን ዩሮ ስምምነት ተፈርሟል::

በተሰመሳሳይ ተቋሙ ሲኖ ሀይድሮ ከተባለ የቻይና ኩባንያ ጋር የብረታ ብረት ሥራዎች ጋር በተያያዘ ስምምነት ለመፈራረም ድርደሮች መጠናቀቃቸው ተገልጿል::

ሲኖ ሀይድሮ የሚሠራው ሥራ የሲቪል ሥራዎችን በማፋጠን ከአጠቃላይ የኃይል ማመንጫ ዩኒቶች ሁለቱ አስቀድመው ኃይል እንዲያመነጩ ያግዛል ተብሏል::

## የቀድሞ የአዳማ ከንቲባ ተያዙ

የቀድሞው የአዳማ ከንቲባ አቶ ሲሳይ ነጋሽን ጨምሮ 5 ግለሰቦች በሙስና ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የኦሮሚያ ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን አስታወቀ።አቶ ሲሳይ ነጋሽ ከዚህ ቀደም በተለያ የመንግሥት እርከኖች በአመራርነት ያገለገሉ ሲሆን ከ15 ሚሊዮን ብር በላይ የሕዝብና የመንግሥትን ንብረት በመመዝበር ተጠርጥረው ነው የተያዙት።

ግለሰቡ በወንጀሉ ተጠርጥረው እስከተያዙበት ጊዜ ድረስ የኦሮሚያ ስቴት ዩንቨርስቲ ምክትል ፕሬዝዳንት ሆነው እያገለገሉ ነበር።

## በኮማንደሩ መኖሪያ ቤት 498 ሽጉጦች ተገኙ

በባህርዳር ከተማ ከአንድ የሕግ አስከባሪ ኮማንደር መኖሪያ ቤት 498 ሕገ ወጥ ሽጉጦች በቁጥጥር ስር ዋሉ:: ከኅብረተሰቡ የደረሰውን ጥቆማ ተከትሎ ፖሊስ ባደረገው ጥብቅ ክትትል መሳሪያዎቹ መያዛቸውን የገለፁት ምክትል ኮማንደሩ የዜጎችን ደኅንነት ለማስጠበቅ የኅብረተሰቡ ትብብር ወሳኝ በመሆኑ ይኸው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቀዋል::

በክልሉ የሚገኙ የጦር መሳሪያዎች ሕጋዊነት እንዲረጋገጥ መንግሥት የ17 የክልሉ ፖሊስ ሕገ ወጥ የመሳሪያ ዝውውርን ለማስቀረት ጠንክሮ እየሰራ መሆኑ ተገልጿል::

# ከአዲሱ የፕሬስ ሴክሬታሪ ኃላፊ ለውጥ ይጠበቃለ

አቶ ንጉሱ ጥላሁን ታህሳስ 24 ቀን 2011 ዓ.ም የፕሬስ ሴክሬታሪያት ኃላፊ ሆነው ተሾሙ:: ለረዥም ዓመታት የአማራ ክልል የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ዋና ዳይሬክተር እንዲሁም የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን በመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ፅህፈት ቤት ሚኒስትር ዴኤታ ሆነው አገልግለው ነበር::

ባለፉት ሁለት ወራት የተዋቀረው የፕሬስ ሴክረታሪ የቀድሞውን የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት ተክቶ የሚሰራ መሆኑን ተናግረዋል::

በዋናነት ከክልል መንግሥታትና ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ጋር ተቀናጅቶ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃዎችን የማድረስ አላማ አለው ተብሏል::

በቀድሞዎቹ ኃላፊዎች፣የሥራ ዘመን የሚዲያ መረጣ የተደረገበት ሒደት በብዙዎች ዘንድ ቅሬታ ፈጥሮ ማለፉ የሚታወስ ሲሆን በአዲሱ ኃላፊ ችግሮች ተስተካክለው የተሻለ ለውጥ ይጠበቃል ተብሎ ይታሰባል:: ወ/ሮ ቢልለኔ ስዩም እና ምክትላቸው ሄለን ዮሴፍ በኃላፊነጽ የቆዩት ሁለት ወራት ሳልሞላ ጊዜ ነው::



# የትግራይ ክልል አቶ ጌታቸው አሰፋን አሳልፌ አልሰጥም አለ



የቀድሞው የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው አሰፋ በትግራይ ክልል ተሸሽገው እንደሚገኙ መንግሥት መረጃ እንዳለውና እርሳቸውን በሕግ ቁጥጥር ስር ለማዋል መሳሪያ በመምዘዝ የሌላ ሰው ሕይወት እንዲጠፋ ፍላጎት እንደሌለው ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አሳወቁ፡፡

በዜጎች ላይ አሰቃቂ የሰብኣዊ መብት ጥሰት እንዲፈፀም በማድረግ የተጠረጠሩትን አቶ ጌታቸው አሰፋን በሕግ ቁጥጥር ስር ለማዋል የክልሉ መንግሥት አሳልፎ እንዲሰጥ ጥያቄ ቢቀርብለትም ፈቃደኛ አለመሆኑን ተናግረዋል፡፡ ከአቶ ጌታቸው በተጨማሪ የክልሉ ተወላጅ ያልሆኑ ተጠርጣሪዎች ክልሉ ከለላ እንደሰጠና በሕግ ቁጥጥር ስር ማዋል አለመቻሉንም አስረድተዋል፡፡ ፓርላማው በዚህ ጉዳይ ላይ አቋም ይዞ ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ድጋፍ ሊያደርግ እንደሚገባም ጠይቀዋል፡፡

## ከ5 ዓመት በፊት የተጀመሩ ፓርኮች ግንባታቸው አልተጠናቀቀም

በአዲስ አበባ ከተማ 117 ሚሊዮን ብር ውጭ የተደረገባቸው ሦስት የሕዝብ መናፈሻ ፓርኮች በተያዘው ዓመት ይጠናቀቃሉ:: ግንባታቸው ከተጀመሩ ከአምስት በላይ ያስቆጠሩት ሆላንድ ኤምባሲ ጀርባ (ጦር ኃይሎች)፣ ኢስኤ ጀርባ እና አቃቂ መናፈሻ ፓርኮች ግንባታ እስካሁን መጠናቀቅ አለመቻላቸው ታውቋል::

የአዲስ አበባ የተፋሰስ እና አረንጓዴ አካባቢዎች ልማት እና አስተዳደር ኤጀንሲ የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ አደባባይ ሰንደቁ መናፈሻዎቹ ከሚገባው በላይ የዘገዩት የዲዛይን ችግር በማጋጠሙ ነው ብለዋል:: ግንባታቸው ቢጓተትም በአሁኑ ወቅት ከ98 በመቶ በላይ መድረሱን ገልፀዋል::

## 48 ሺህ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ሳይጀመሩ ግማሽ ዓመት ተጠናቀቀ

በአዲስ አበባ ከተማ 48 ሺህ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ በተያዘው ዓመት ለመጀመር እቅድ ቢያዝም ግንባታው ሳይጀመር የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ተጠናቀዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ቤቶች ልማት አስተዳደር ቢሮ የቤቶቹን ግንባታ ለማካሄድ አቅዶ የነበረው በቦሌ ክፍለ ከተማ በቦሌ አራብሳ፣ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በኮዬ ፈጬ አካባቢዎች በሚገኙ ስምንት ሳይቶች ነበር፡፡

የቢሮው የቤቶች ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ኢንጂነር ዘርይሁን ዓምደ ማርያም እንዳስታወቁት የቤቶቹን ግንባታ ማካሄድ ያልተቻለው ቦታዎች ከይገባኛል ነፃ መሆን ስላልቻሉ ነው ብለዋል፡፡ የከተማው መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ቦታዎቹን ነፃ አድርጎ እንዲያስረክባቸው ወይም ተለዋጭ መሬት እንዲሰጣቸው መጠየቃቸውን ምክትል ቢሮ ኃላፊው ተናግረዋል፡፡

## በሕጋዊ መንገድ ወደ መካከለኛው ምስራቅ መጓዝ አልተጀመረም

ሕጋዊ የውጭ አገራት የስራ ስምሪት በይፋ መጀመሩ ቢገለፅም እስካሁን ሕጋዊ መስመሩን ተከትሎ ወደ መካከለኛው ምስራቅ አገራት ለስራ የተጓዘ ሰው የለም፡

የስራ ስምምነት በተፈፀመባቸው አገራት ጉዞው አለመጀመሩም ኤጀንሲዎች ለአላስፈላጊ ወጪ እየዳረጋቸው መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ተጓዦች በሞያ ማሰልጠኛ ተቋማት ሰልጥነውና የሞያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና አጠናቀው ለጉዞው ዝግጁ ቢሆኑም እስካሁን ግን ወደ አገራቱ የተጓዘ የለም፡፡

ሕጋዊ የሥራ ስምሪቱ አለመጀመሩም ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውሩ እንዲንሰራራ አድርጓታል ብለዋል፡፡

# የውህደቱ ሒደት በአንክሮ ሊጤን ይገባል

ሀገራችን በቆመችበት መስቀለኛ መንገድ ላይ ጥንድ እና ተጻጻሪ የፓለቲካ ኃይሎች ተፋጠዋል::በአንደኛው ጥግ በዘውግ ማንነት የተሰባሰቡ የፓለቲካ ቡድኖች የተፈጠረላቸውን ምቹ አጋጣሚ በመጠቀም ተከታዮቻቸውን እያበራከቱ ነው::በሌላኛው ጫፍ ደግሞ የዜግነት ፓለቲካ አቀንቃኝ ኃይል በዘውግ ድርጅቶች የሚቀለሰውን የልዩነት ግምብ በአምክንዮ ለማፈራረስ ጥብቅ ትግል ውስጥ ገብቷል::ግብግቡ የዋዛ አይደለም::ስሜት በአምክንዮ ላይ ሰልጥኖ ፣አችናፊ ሆኖ የሚያውቅበት አጋጣሚ በታሪክ ፊት ተከስቶ ስለማያውቅ በፓለቲካዊ መርህ የሚመራው ቡድን በማሳረጊያው ድሉ የእርሱ እንደሚሆን ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም::የዘውግ ማንነትን መሠረት ያደረጉ ድርጅቶች በፓለቲካ ፓርቲነት መፈረጅ የማይቻሉ እንደሆነ ሳይንሱም ቢሆን ያስረግጣል ::እነዚህ ድርጅቶች ዋንኛ መለያ መስፈርታቸው የዘረመል ፓለቲካ(DNA Politics) ሲሆን በአብዛኛው በጠላትነት የሚፈርጁት ማኅበረሰብ ይኖራቸዋል::በአንጻሩ የዜግነት ፓለቲካ የሚያቀነቅኑት ድርጅቶች በፓርቲ ቁመና መገለጽ ይቻላል::ምክንያቱም ድርጅቶቹ ከጎሳ መር ፓለቲካ በተቃራኒ ለሁሉም ዜጋ ክፍት የሆነ አምክኖዋዊ መርህን ስለሚከተሉ ነው::

እንግዲህ የቀድሞ ምርጫ ቦርድ በአባልነት የመዘገባቸውን(ሕወሓት ኢሕአዴግ ቀለብ የሚሰፍርላቸውን ጨምሮ) በዘውግ እና በርዕዮተዓለም የፓለቲካ መስመር የተከፋፈሉ ከ80 በላይ በፓርቲ ስም የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች እንዳሉ ይታወቃል::አንዳንዶቹ የውሀደት ሒደት ውስጥ ገብተዋል::ከእነዚህ ውስጥ የዜግነት ፓለቲካን በማቀንቀን የሚታወቁት ሰማያዊ ፓርቲ፣ኢዴፓ ፣የቀድሞው የአንድነት አባላት እና ከመንግሥት ጋር ተደራድሮ ወደ ሀገር ውስጥ የገባው አርበኞች ግንቦት ሰባት ለአንድነት እና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ ይገኙበታል::ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቅርቡ ባካሄዱት ጉባኤ ላይ  ፓርቲዎቹ ጥምረት ፈጥረው  3 እና 4 ሆነው እንዲገዳደሯቸው ጥሪ ማቅረባቸው የሚታወስ ነው::እዚህ ጋር አንድ ልብ መባል የሚባለው ነጥብ ውህደትን ተከትሎ የሚመጣው ጣጣ ነው::ሐዲቱ በአግባቡ ካልተጤነ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያዘነብላል ::የሀገራችን የፓለቲካ ታሪክን ዞር ብለን ስንመለከት በሸር እና በሴራ የተበተበ ነው::ፓለቲካን የሥልጣን እና የቁስ ጥም ማርኪያ መንጠላጢያ ተደርጎ ስለሚወሰድ ከቅን ግለሰቦች ይልቅ በሴራ የተካኑ ፓለቲከኞች በምህዳሩ ላይ ተሰልፈዋል::

የአራቱ የፓለቲካ ፓርቲዎች ውህደትም በዚህ ማእቀፍ ውስጥ ነው መገምገም ያለበት::በ1997 የተከሰተውን የቅንጅትን የውህደት ሳንካን መለስ ብሎ ማየት ይገባል::ከቅንጅት ውድቀት እና ስኬት መለስ ብሎ መማር ወደፊት ለሚመሠረተው ሀገርአቀፍ ፓርቲ ግብዓት ይሆናል:: በርግጥ በዛን ወቅት ሥልጣን ላይ የነበረው ሕወሓት/ኢሕአዴግ እና በገለልተኛነት ስም የተቀመጠው ምስለኔው ምርጫ ቦርድ፣ በጋራ ይሸርቡት የነበረው ሴራ ከጥቅመኛ ግለሰቦች ጎን ለጎን ትልቁን ድርሻ ተወጧል:: አሁን ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ሀገሪቱን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማሸጋገር የምር የተነሳ ይመስላል፤ምርጫ ቦርድም በፍትሕ ተሟጋቿ ብርቱካን ሚዴቅሳ የሚመራ በመሆኑ ከዚህ ቀደም በተቋሙ ላይ ይሰነዘር የነበረው ሐሜት በአንጻራዊ መልኩ የተሻለ ነው::ከቁስ ሰቀቀን ያልተላቀቁ ፓለቲከኞች ግን አሁንም ከአውዱ አልጸዱም::

እነዚህ ግለሰቦች በጥንቃቄ በዐይነ ቁራኛ መጠበቅ፣ ከፍ ሲልም  ብስለት በታከለበት ፋጣን እርምጃ ገለል ማድረግ ተገቢ ነው::በአሁኑም የፓርቲዎቹ የውህደቱ ሒደት ላይ ከዚህ ቀደም ያኮረፉ ኃይሎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሊኖራቸው የሚችለውን አፍራሽ ሚና በአግባቡ ሊጤን ይገባል::ወደ ውሀደት በሚገቡት ፓርቲዎች ውስጥ ያሉት ግለሰቦች ካኮረፉት ኃይሎች ጋር የእከክልኝ ልከክልህ የግንኙነት ሰንሰለት መበጠስ፣አለመበጠሱ በአግባቡ መመርመር አለበት::ያኮረፉት ግለሰቦች እጅ ረጅም ከሆነ ላለፉት ዘመናት ሕዝባችን ላይ ሲቀለድበት የነበረው የፓለቲካ ቧልት መልሶ መከሰቱ አይቀርም:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ በዜግነት መርህ ላይ በተመሠረተ የፓለቲካ ፓርቲዎች ውህደት ዓይነት ዘውጌ ተኮር ድርጅቶችም በአንድነት ተሰባስበው ትርጉም ያለው ትግል መጀመር ይኖርባቸዋል::በአጠቃላይ የውህደቱ መንገድ በተስፋም በአደጋም የተሞላ ነው::ሀገራችንን ዝንፍ በማይል የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሐዲድ ውስጥ ለማስገባት ሊኖረው የሚችለው ሚና ከጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም::


**ግዮን መጽሔት**

**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና**
**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ
አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ
ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ማኔጂንግ ኤዲተር**
ደረጀ ይመር

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ብሩክ መኮንን

**አዘጋጅ**
ተስፋዬ ሽብሩ

**ተባባሪ ዘጋቢያችን**
ቶማስ አያሌው(ከአሜሪካ)

**አምደኞች**
ወንድሙ ነጋሽ(ኢ/ር ከለንደን)
ተረፈ ወርቁ
ሁሴን ከድር

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ሀብታሙ መኮንን

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 5ተኛ
ፎቅ ቢሮ ቁ. 501
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011mag@gmail.com
**Facebook**
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**
አስኮ ማተሚያ ቤት
ክ/ከተማ ቂርቆስ  ወረዳ 15  የቤት ቁ. 23/10
ስልክ ቁ. 0913 18 12 12


በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም

# ዜግነት በብሔር ላይ ይሰለጥን ይሆን?

## የለውጥ ንፋስ በፓርቲዎች መንደር

መለክ ቢ.

ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ ሥልጣንን 'ባትጋሩኝ' ብሎ ለብቻው የያዘው 'ኢሕአዴግ' ከህጻንነት እስከ ወጣትነት መባቻው ድረስ ወንበሩን ይዞ ከርሟል። ኢሕአዴግ እንዳለመታደል ሆኖ ከጅምሩ እስከፍጻሜ መባቻው ዘመኑን ያሳለፈው በተቀውሞ ውስጥ ነው። የኢሕአዴግ የቀደመ ፖለቲካ በአዲሱ የለውጥ ኃይል ከተለወጠ በኋላ ለገዢው ፓርቲም ይሁን ለተፎካካሪ ፓርቲዎች የዴሞክራሲ መንገድ ማሳያ ሆኖ ከፊት ያለው አንድ ግብ ምርጫ 2012 ብቻ ነው። ይህንን ተከትሎ በኢትዮጵያ የተቃውሞ ፖለቲካ ጎራ አሰላለፍ ውስጥ ተዋናይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች በኢሕአዴግ ክርን ተደቁሰው ከተረመረሙበት መሬት ዳግም ነፍስ እየዘሩ መንቀሳቀስ ጀምረዋል። በመንግሥት አስተዳደር ላይ ያለውን ተቃውሞ ወደጋራ ድምጽ ለመለወጥ እና ለኢትዮጵያ ፖለቲካ አማራጭ ሐሳብ ለማቅረብ በሚል በሀገር ውስጥና በውጭ ተቋቁመው የነበሩት የፖለቲካ ፓርቲዎች ከሐሳብ እስከ ትጥቅ ትግል በደረሰ ደረጃ ከኢሕአዴግ መንግሥት ጋር ሲፋለሙ 27 ዓመታትን አስቆጥረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን በመጡባቸው የመጀመሪያ ወራት ወደ አሜሪካ ሲያቀኑ ቀዳሚ ተግባራቸው የነበረው የዳያስፖራ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ሰብስበው ማናገር ነበር። በዚህ ወቅት ፓርቲዎቹ ወደ ሀገር ቤት ገብተው፣ ቢቻል ተዋህደውና ሁለት ሶስት ጠንካራ ፓርቲ ሆነው መንግሥትን በምርጫ 2012 እንዲፎካከሩ ጥሪ አቅርበዋል። "ተዘጋጅተን እየጠበቅናችሁ ነው" ብለዋል። ይህንን ተከትሎም በትጥቅ ትግል ላይ የነበሩም ይሁን ከደርግ ዘመን ጀምሮ ከሀገር ተሰድደው በአሜሪካ እና ሌሎችም የዓለም ሀገራት ውስጥ ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የነበሩ አካላት ሁሉ ወደ ሀገር ቤት ገብተዋል። እንደ ኢህአፓ ካሉ ከ60ዎቹ ግራ ዘመም ፓርቲዎች ጀምሮ የ1997 ምርጫን ተከትሎ ተሳድዶ ከሀገር የወጣው የቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ አመራሮች እስከፈጠሩት ግንቦት ሰባት ድረስ፣ አስመራ ውስጥ ቤዙን አድርጎ በሀገር ውስጥ የትጥቅ ትግል ያካሂድ ከነበረው ኦነግ ጀምሮ እስከ ኦጋዴን ነጻ አውጪ ግንባር ድረስ ሁሉም የሰላም የትግል አማራጮችን በመውሰድ ወደ ሀገር ቤት ገብተው ለመታገል ስምምነት ላይ ደርሰዋል። ኦነግ አሁንም ድረስ ትጥቅ አልፈታም ብሏል ቢባልም ሌሎች በትጥቅ ትግል ላይ የነበሩ ኃይሎች በሙሉ ሰላማዊውን መንገድ መርጠው በምርጫ ቦርድ ለመመዝገብ እና ኢሕአዴግን ተገዳድረው አማራጭ ፓርቲ ለመሆን እየሰሩ ነው።

> ብሄር የዚህች ሀገር
> አፍራሽ ሐሳብ እና ጠባብ
> አመለካከት ነው ብሎ
> ለማሳመን መሞከር
> በፖለቲካው ተጠላልፈው
> እርስ በርስም መስማማት
> ላቃታቸው ኃይሎች
> አማራጭ መድኃኒት
> ስለመሆኑ ጥርጣሬ አለ

በአንዳንዶች አቆጣጠር 70 በሌሎች ደግሞ 80 እንደሆኑ የሚነገረው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ ጥቂት ጠንካራ ፓርቲ ለመሸጋገር ጥረት እንዲያደርጉና በመበታተን ውስጥ ከሚገጥም የኃይል ክፍተት ይልቅ በአንድነት ውስጥ የሚገኘውን ጥንካሬ ተረድተው እንዲሰባሰቡ ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ካሳሰቡ ወዲህ ብዙዎቹ ጥሪውን በመቀበል ፣ አምነው በመንቀሳቀስም ጭምር ወደ ውህደቱ ሲመጡ ተስተውሏል። በተለይም ከአራቱ የኢሕአዴግ ብሔራዊ ድርጅቶች ሁለቱ አስቀድመው በየክልላቸው ከሚንቀሳቀሱ ብሄር ተኮር ድርጅቶች ጋር ውህደት በመፈጸም "አርአያ ሆነው ለመታየት" ሞክረዋል።

በአቶ ለማ መገርሳ የሚመራው የኦሮሞ ዴሞክራቲክ ፓርቲ (ኦዲፒ) በአቶ ሌንጮ ለታ ከሚመራው ኦሮሞ ዴሞክራቲክ ፍሮንት (ኦዲኤፍ) ጋር ለውህደት የሚያበቃቸውን ስምምነት ተፈራርመዋል። የአማራ ዴሞክራቲክ ፓርቲ (አዴፓ) በትጥቅ ትግል ላይ ተሰማርቶ ከነበረው የአማራ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ንቅናቄ (አዴሃን) ጋር ተመሳሳይ የውህደት ስምምነት ፈጽሟል። ያንን ተከትሎም 14 የሚጠጉ በኦሮሚየ የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎችን በመሰብሰብ ውህደት አማራጭ እንደሆነ ሐሳብ አቅርቦላቸዋል።

በተቃዋሚ ፓርቲዎች በኩል የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ፣ የኦሞ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት እና በቅርቡ ወደ ሀገር ቤት የተመለሱ ▶

አምስት ፓርቲዎች ለውህደት የሚያበቃቸውን የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል፡፡ በትግራይ ሕዝብን ወክለው ከሚንቀሳቀሱት ፓርቲዎች መካከልም አረና ትግራይ ለዴሞክራሲያዊ ሉዓላዊነት እና የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ትዴት ) ተመሳሳይ የውህደት ሂደት ላይ ናቸው፡፡

እንዲህ እንዲህ እያለ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ውህደት ቀጥሎ አሁን ደግሞ አርበኞች ግንቦት ሰባት ፣ ሰማያዊ ፓርቲ፣ የቀድሞው አንድነት ለፍትህ እና ዴሞክራሲ እንዲሁም የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ፓርቲ በጋራ ውህደት በማድረግ አዲስ በዜግነት ፖለቲካ ላይ የተመሠረተ ፓርቲ ለማቋቋም ስምምነታቸውን ይፋ አድርገዋል፡፡ በመጪው መጋቢት ወር አዲሱ ፓርቲ ይፋ ይደረጋል ተብሎም ተገልጿል፡፡

ብዙዎች እየተካሄደ ያለውን አንድ የመሆን እንቅስቃሴ “ውህደት? ጥምረት ወይስ ቅንጅት?” ብለው ሲጠይቁ ተስተውሏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ውህደት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላለፉት 27 ዓመታት ተሞክሮ ያልተሳካ የፖለቲካ መንገድ በመሆኑ ከአሁኑ ውህደትም የሚጠበቅ ውጤት የለም ወደሚል ሐሳብ መጥተዋል፡፡

እዚህ ላይ የተለየው ታሪክ የብሔር ፖለቲካ በገነነባት ኢትዮጵያ ውስጥ እነአርበኞች ግንቦት ሰባት እና ሰማያዊ ፓርቲ ሊታገሉበት የተነሱት የዜግነት ፖለቲካ በእግሩ ቆሞ መራመድ ይችላል ወይ የሚለው ጥያቄ ዋናው ነው፡፡ የዜግነት ፖለቲካ የሚያራምዱት ኃይሎች ካላቸው ውስን ኃይል፣ ከሚያዳርሱት ከባቢ ማነስ እንዲሁም በብሔር በታጠሩ ሰፍራዎች ውስጥ ከሚኖራቸው የደጋፊ ድርሻ አኳያ “እውን የዜግነት ፖለቲካ በብሔር ፖለቲካ ላይ ሠልጥኖ (ገንኖ) መውጣት ይችላል?” የሚለው ጥያቄ አሁን ጎልቶ የሚሰማ ድምጽ ሆኗል፡፡

## ያልተሳኩ ታሪኮች ውህደት እና መለያየት

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ጎራ ላለፉት ከሁለት ዐሥርተዓመታት በላይ ለሆኑ ጊዜያት ያካሄደው ውህደትና ጥምረት ያልሰመረለት ነው ተብሎ ይተቻል፡፡

የሀገራችን የፓርቲ ፖለቲካ ከደርግ ዘመን ጀምሮ ሲታይ ያን ያህል የበዛ ዘመን አስቆጥሯል ማለት አይቻልም፡፡ በተለይም ኢሰፓ አንድ ፓርቲ ሆኖ ሀገር ማስተዳደር ከጀመረበት ዘመን በፊት የነበሩትና በደርግ ወደ ሥልጠን መምጣት አካባቢ የተፈጠሩት ኢህአፓ፣ መኢሶን፣ ኢጭአት፣ ወዝሊግ፣ ኢማሌድህ፣እና ወዘተ ያሉ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ኮሚቴ (ደርግ )ዘመን ፓርቲዎች በግራ ዘመም ፖለቲካ የርዕዮተ ዓለም ልዩነት ሳይኖራቸው ነገር ግን የሥልጣን ሽኩቻ አባልቶ ያከሰማቸው ናቸው፡፡ ኢሰፓአኮ ተመስርቶ ብቸኛ ዓላማው የሆነውን ኢሰፓን ከወለደ በኋላ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ዳግም ፓርቲዎች የታዩት በኢሕአዴግ ዘመን ነው፡፡ በ1983 የሽግግር ዘመን እንደ ደርግ ዘመን ሁሉ ብዙ ፓርቲዎች ወደ ፖለቲካው መድረክ ብቅ ቢሉም በአቅም ብዙም ሳይጎለብቱ፣ በውጤትም ብዙም ሳያረፋፍዱ እየከሰሙና በላያቸው ላይ ሌላ እየተወለደ አስከ አሁን ዘመን ድረስ ኖረዋል፡፡

የፖለቲካ ፕሮግራማቸው አንድ ሆኖ ነገር ግን በየቡድኑ ተከፋፍለው በፓርቲነት ሲንቀሳቀሱ የኢሕአዴግን “ዴሞክራሲ ሰፍኗል” ስብከት እያጠናከሩ በተጨባጭ ግን ለሕዝቡ የፈየዱት አንዳች ነገር ሳይኖር የተዋጡ፣

**በኢትዮጵያ በነበረው አፋኝ የፖለቲካ ሥርዓት ሳቢያ በብሔር የተደራጁ ፓርቲዎች በኢሕአዴግ እህት ድርጅቶች እየተቀለጠሙ ከጨዋታ ውጪ ተደርገው ኖረዋል። የብሔር ፖለቲካ በራሱ አባታዊ (ፓትሪያርካል) በመሆኑ ሌሎች መሰል ፓርቲዎች በቤቱ እንዲኖሩ አይፈቅድም። ይህ በሁሉም የብሔር ፖለቲካ በነገሠባቸው የዓለም ሀገራት በሙሉ የታየ ሐቅ ነው**

የተደፈጠጡ እና የከሰሙ ፓርቲዎች ቁጥርም ቀላል አይደለም፡፡

## ምርጫ 97 እስኪደርስ እዛው ቁጭ፣ እዛው ዘጭ

ዛሬ በፖለቲካው ረድፍ የተሰለፉት የተቃውሞ ፖለቲካ ኃይሎች እንደአዲስ ያነሱት የውህደት ጉዳይ በቀደመው የኢሕአዴግ ዘመንም በተመሳሳይ ጊዜ የተነሳ እና በሂደት ስኬቱ ሳይታይ የከሰመ ነው፡፡ ለምሳሌም ኢሕአዴግ አገሪቱን ከተቆጣጠረ በኋላ ከተቋቋሙ የፖለቲካ ፓርቲዎች አንዱ የመላ አማራ ሕዝብ ድርጅት (መአኅድ) ነበር፡፡ መአህድ ነሐሴ 5 ቀን 1994 ዓ.ም ራሱን ወደ አገር አቀፍ ፓርቲነት በመለወጥ መኢአድ በሚል ስያሜ መጠራት ጀመረ፡፡ ይህ አዲስ አካሄድ በአባላቱ መካከል ክፍፍል ፈጠረና ከፓርቲው በልዩነት የወጡ ሰዎችም ኢዴአፓ የሚባል ፓርቲ አቋቋሙ፡፡ የመጀመሪያው ውህደት የተጀመረው ኢዴአፓ፤ከኢዲዩ፣ ከኢዳግ እና ከመድህን ጋር ባደረገው ውህደት ነበር፡፡ ይህ ውህደት ግን የታሰበውን ዓላማ ማሳካት ሳይችል በራሱ ጊዜ ላላ፡፡

በሌላ በኩል መስከረም 20 ቀን 1997 ዓ.ም ኢዴአፓ ከመድህን ጋር መዋሀዱን ይፋ አደረገ፡፡ ግንቦት 97 በሚከናወነው ምርጫ ላይ እሳተፋለሁ አለ፡፡ በዛው ሰሞን ኢዴአፓና መድህንና መኢአድን ጨምረው ለመዋሃድ ያደረጉት ሙከራ ከጫፍ ደርሶ ሳይሳካ ቀርቷል፡፡ ጥቅምት 1997 ዓ.ም ሲሆን ደግሞ ኢዴአፓና መድህን መኢአድን እና ኢድሊን ጨምረው በመዋሃድ “ቀስተ ደመና ቅንጅት” የተባለ ፓርቲ መሰረቱ፡፡ እነዚህ አራት ፓርቲዎች ለምርጫው ጥቂት ወራት ሲቀሩ ህዳር 9 ቀን 1997 ዓ.ም ስማቸውን ለውጠው ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ በሚል ስያሜ ለመወዳደር መወሰናቸውን በፊርማቸው አረጋገጡ፡፡ በጊዜው በሰጡት መግለጫ የተጣመሩት ለምርጫ ብቻ ሳይሆን ሕዝብን ለማገልገል መሆኑን በመግለጽ ምርጫው ቢሸነፉ እንኳን ቅንጅታቸውን ወደ ውህደት በመቀየር አንድ ፓርቲ የመሆን የረጅም ጊዜ እቅድ እንዳላቸው ነበር ያስታወቁት፡፡

ይህ በኢትዮጵያ የተቃውሞ ፖለቲካ ፓርቲዎች ታሪክ ውስጥ የጎላ ድርሻ የነበረውና በብዙዎች ዘንድም ከፍተኛ ድጋፍ ከማግኘቱ ጋር በተያያዘ “መንፈስ ነው” የተባለለት ቅንጅት ብዙዎችን ከጎኑ በማሰለፍ እና ደጋፊዎችን በማሰባሰብ፣ ኢሕአዴግን የሚገዳደር ጠንካራ ፓርቲ ሆነ፡፡

ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚያውቀው ምርጫ 97 ላይ ኢሕአዴግም በራሱ ጠቅላይ ሚኒስትር አፍ እንደመሰከረው ቅንጅት አዲስ አበባ ላይ ኢሕአዴግን በዝረራ አሸንፎ ከወጣ በኋላ ሰኔ ወር አካባቢ በተፈጠረ አለመስማማት የመሰንጠቅ አደጋ አንዣበበበት፡፡ የፓርላማ ግቡ አትግቡ ክርክርና የአዲስ አበባን ወንበር ተረከቡ አንረከብም ምልልስም ቅንጅቱን ወዳልተጠበቀ መስመር ወሰደው፡፡ በዚያው ወር በተመሳሳይ ከመአህድ ተወልዶ ብሔራዊ ቅርጽ በያዘው መኢአድ በውስጣዊ ችግር ተተበተበ፡፡ በዚህ ሳቢያ የተጋረጠበትን የመፍረስ አደጋ ለመቀልበስ ኮሚቴ አቋቁሞ መንቀሳቀስ ጀመረ፡፡ በሌላ በኩል ቅንጅቱ የገጠመው ፈጣን መከፋፈል እየተስፋፋ ቆይቶ ጥቅምት ላይ አመራሮቹን አገደ፡፡

የቅንጅት አመራሮች በኢሕአዴግ ከታሰሩ በኋላ የቀሩት ፓርላማውን የተቀላቀሉ የቅንጅቱ ተመራጮች አራት ቦታ ተሰነጣጠቁና ኢዴፓ፣ የፓርላማ ቡድን፣ መኢአድ እና ቅንጅት በሚል ተከፋፍለው መቀመጫቸውን ያዙ፡፡

## የምርጫ 2002 ትርክቶች

የተቃዋሚ ፓርቲዎች የውህደት እና ልዩነት ታሪኮች በዚህ አላበቁም፡፡ ምርጫ 1997 አልፎ ምርጫ 2002 ዓ.ም ሲቃረብም በተመሳሳይ ምርጫን ዓላማ ያደረጉ ትብብሮች፣ ግንባሮች እና መድረኮች እንዲሁም ቅንጅቶች መከወን ጀመሩ፡፡ ህዳር 25 ቀን 2002 ዓ.ም አሁን ድረስ ያለውና በፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ የሚመራው የኢትዮጵያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ እና የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ኅብረት ግንባር መስርተው መንቀሳቀሳቸውን አስታወቁ፡፡ በሌላ በኩል የካቲት 21 ቀን 2002 ዓ.ም የኦሮሞ አቦ ነፃነት ግንባር፣ የኦሮሞ አንድነት ነፃነት ግንባር፣ የገዳ ሥርዓት አራማጅ ፓርቲ፣ የኦሮሚያ ነፃነት ብሄራዊ ፓርቲ እና የመላው ኦሮሞ ዲሞክራቲክ ፓርቲ የተባሉ በምርጫ ቦርድ የተመዘገቡ አምስት የኦሮሞ ድርጅቶች ቅንጅት መስርተው ለመንቀሳቀስ ስምምነት ላይ መድረሳቸውን አስታወቁ፡፡

በሌላ በኩል አንድነት ለፍትህ እና ዴሞክራሲ የተባለ ፓርቲ ከተቋቋመ በኋላ በታህሳስ 2001 ዓ.ም “መርህ ይከበር” የሚል መሪ ቃል ያነገቡ የፓርቲው ሰዎች ከዚያ ወጥተው ሰማያዊ ፓርቲ የተባለ ፓርቲ አቋቋሙ፡፡ይህ ድራማ ቀጥሎ እንደገና ►

ሰኔ 2000 ዓ.ም መድረክ የተባለ ብዙዎች የተሰባሰቡበትን በአንጋፋ ፖለቲከኞች የሚመራ ፓርቲ ለማቋቋም ምክክር ተካሄደ። ይህ ምክክር ዓመት ካለፈው በኂላ የካቲት 2001 ዓ.ም ላይ ስድስት ፓርቲዎች ጥምረት መስርተው መድረክን መመስረታቸውን ይፋ አደረጉ። መስከረም 24 ቀን 2003 መድረክ ወደ ግንባር ተሸጋገረ:: እንዲህ እንዲህ ብሎ ጠንካራ ፓርቲ ተመሰረተ የሚለው ተስፋ ገና በብዙኃኑ ልብ ውስጥ ሳይከስም አንድነት ለፍትህ እና ዴሞክራሲ ከመድረክ አባልነቱ ታገደ። ብዙም ሳይቆይ አስቀድሞ እንዳደረገው አንድነት ከመኢአድ ጋር ውህደት ለመፈፀም እየተዘጋጀሁ ነው በማለት ከመድረክ መውጣቱ ለዓላማ መሆኑንና በዚያ በኩል የሚያጣውም ሆነ የሚያጎድለው ነገር እንደሌለ ለማሳወቅ ሞከረ።

## እምቦጭ እንዘጭ !

በብዙ የፖለቲካ ምሁራን ዘንድ የተቃውሞው ጎራ ውህደት እና አንድነት የማይሳካለት መሆኑ ነው የሚተቸው። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የተቃውሞ ጎራው በራሱ እግር ለመቆም የማይችል፣ በግለሰቦች የበላይነትና አምባገነንነት ጥላ ስር የወደቀ እና የሀገር ጥቅም ሳይሆን የግል ሩጫ የበዛበት ነው ተብሎ ይተቻል። ላለፉት ከሁለት ዐሥርት ዓመታት በላይ ለሆኑ ጊዜያት የተቃዋሚ ፓርቲዎች የተጓዙበት መንገድ ሲገመገም ኢሕአዴግን በማዳከም እና ለሥልጣን በመብቃት በኩል ይህ ነው ተብሎ የሚጠቀስ ተጨባጭ ውጤት አላመጣም:: ኢሕአዴግ በሕዝብ ግብታዊ ትግል እና በራሱ ሰንሰለት ተጠላልፎ ዘጭ ብሎ ወደቀ እንጂ በውጪ የፖለቲካ ኃይሎች ግፊት ተናደ ለማለት የሚያበቃ ምንም ማስረጃ የለም። በዚህ ሳቢያ በተለይ ከምርጫ 2002 በኂላ ፓርቲዎች አብረው ለመስራት እና ለመቀናጀት የነበራቸው ተስፋ ሁሉ ቀጭጮ ተስፋ የሚያስቆርጥ ደረጃ ላይ ደርሶም ነበር።

እንደታየው ከሆነ ባለፉት ከሁለት ዐሥርተ ዓመታት በላይ የሆኑ ጊዜያት በሀገሪቱ ያሉ ዋና ዋና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሲቀናጁ፣ ሲጣመሩ፣ ሲዋሃዱ ሲፈርሱ ነው የኖሩት:: በፖለቲካ አጥኚዎችም ይሁን በፓርቲው አመራሮች እንደሚታመንበት ለዚህ ምክንያቱ ከሀገራዊነት ስሜት ይልቅ የግለሰቦች ስሜትና ፍላጐት አይሎ መውጣቱ ነው:: ከ1994 ጀምሮ የተሞከሩት ቅንጅቶች እና ጥምረቶች በሙሉ ሴራ ያልተለያቸው፤ የግለሰቦችን ፍላጐት ብቻ ጠብቀው የተፈጠሩ በመሆኑ ሲፈርሱ የተገነቡበትን ያህል እንኳ ኃይልና ጊዜ አይጠይቁም ነበር። በትንሽ ተንኮል ይፈርሳሉ:: ከዚህ ሁሉ የከፋው ደግሞ ተንኮል ተደራጅቶ በመስፈኑ መፍረስ ብቻ ሳይሆን አንዱ ሌላውን ለመዋጥ መፈለጉ አንደኛው ስጋት ሆኖ ነው የወጣው።

ብዙዎች እንደሚናገሩት እና አሁንም ድረስ የክርክር ምንጭ እንደሆነው በ1997 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ ጉልህ ስፍራ የነበረው ቅንጅት የፈረሰው በሴራ ነው።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ትግልን ውጤት አልባ ያደረገው ይህና የኢሕአዴግ የቆረጣ ታክቲክ ነው ብለው ብዙዎች ያምናሉ።

ኢሕአዴግ ዘመኑን ሁሉ ከተቃውሞ የጸዳ መንገድ ላይ ለመራመድ በነበረው ፍላጎት የሚገዳደሩትን ቀርቶ ሊወዳደሩት የሚያስቡትን ጭምር እያጠፋ ነው የኖረው። ኅብረቶችንና ቅንጅቶችን መሀል እየገባ ሰንጥቆና አለመተማመን ፈጥሮ በሴራ ሲያፈርስ ኖሯል።

## ምርጫ 2012
## የዘንድሮው ጥምረት እና ውህደት

ባለፉት ሁለት ዐሥርተ ዓመታት በላይ በመቀናጀት፣ ግንባርና ጥምረት በመፍጠር ውጤት ያመጣና ዓላማውን ያሳካ ፓርቲ አልታየም። ብዙዎች እንደሚተቹት በዋናነትም የፓርቲዎች ውህደት እና ጥምረት ውጤታማ የማይሆነው ጥምረታቸው ከፕሮግራም፣ ከአላማ እና ከግብ አንድነት በሚመነጭ ሳይሆን ኢሕአዴግን ተሰባስቦ ለማሸነፍ ካለ ፍላጐት ብቻ መነሻ አድርጐ የሚፈጠር በመሆኑ ነው።

ፓርቲዎች ብዙውን ጊዜ ለመቀናጀትና ለመጣመር የሚሯሯጡት በምርጫ ሲቃረብ መሆኑ በራሱ ችግር አለው። መሯሯጣቸውም ይህን ያመለክታል፣ ምርጫን ብቻ ግብ ያደረጉ ጥምረቶች ከታሪክ እንደታየው ከምርጫው በኂላ ዋጋ አይኖራቸውም ::

ለዚህ እንደምክንያት የሚጠቀሰው ፓርቲዎች አንድነቱን ከመፈለግ ባሻገር ማን አመራር ይሁን በሚለውና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ በቂ ዝግጅት አለማድረጋቸው ነው። በተለይም በስራ አስፈፃሚ ውስጥ ትልቁ ድርሻ የማን ነው? ምን አይነት የመንግሥት አወቃቀር ሊኖር ይገባል፣በመሬትና በቋንቋ እንዲሁም በፓርቲው ስያሜ ዙሪያ ቀድሞ መስማማት ካልተቻለ ውህደቱ ወደልዩነት የማምራቱ እድል ሰፊ ነው።

ለምሳሌ ባለፈው ዘመን መኢአድና ኢዴፓ ያልተስማሙበት አንድ ጉዳይ ለመዘላለፍ አብቅቷው እንደነበር አይዘነጋም። በወቅቱ መኢአድ የመንግሥት ሥርዓቱ ፕሬዚዳንታዊ ይሁን ሲል ኢዴፓ በበኩሉ ፓርላሜንታዊ ይሁን በማለቱ የፕሮግራም ልዩነቶችን ተፈጠሩ። በዚያም ልዩነትን አቻችሎ እንደመጓዝ እስከ መዘላለፍና መወነጃጀል የደረሱ አለመግባባቶች ተከሰቱ።

ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ የአስካሁኑ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ጉዞ ሕዝብን ተስፋ ያስቆረጠ ነበር። በዚህ ሳቢያም ነው አንዳንድ ወገኖች

ባለፉት ሁለት ዐሥርት ዓመታት በሀገሪቱ ለተስተዋለው ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ቀውስ በሥልጣን ላይ ካለው ኢሕአዴግ በበለጠ ተቃዋሚዎች ተጠያቂዎች ናቸው የሚሉት። ኅብረት፣ ቅንጅት፣ አማራጭ ኃይሎች፣ መድረክ እየተባለ የተኬደው ጉዞ ሲገመገም አንድ ነጥብ እንኳን ማስቆጠር አለመቻሉ በራሱ አሁን ምን ቢደረግ ያዋጣል የሚል የመፍትሄ ጥያቄ ያስነሳል።

የኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ብዙ ዘመን አስቆጥሯል ማለት ባይቻልም ብዙዎች ማደግ ሲገባቸው እየቀጨጩ ቀተዋል። ብዙ ፓርቲዎች ፕሮግራማቸው አንድ ሆኖ እንኳ ተከፋፍለው መንቀሳቀሳቸው ወደ ውድቀትና ተነጥለው ወደ መመታት አድርሷቸዋል። ይህም ለኢሕአዴግ የሥልጣን እድሜን መራዘም እና ለሕዝቡ ትግል አስተባባሪነት ድክመት አንዱ ምክንያት ሆኖ ይጠቀሳል።

## የዛሬው ዜግነትና የኖረው ብሔርተኝነት

በኢትዮጵያ በነበረው አፋኝ የፖለቲካ ሥርዓት ሳቢያ በብሔር የተደራጁ ፓርቲዎች በኢሕአዴግ እህት ድርጅቶች እየተቀለጠሙ ከጨዋታ ውጪ ተደርገው ኖረዋል። የብሔር ፖለቲካ በራሱ አባታዊ (ፓትሪያርካል) በመሆኑ ሌሎች መሰል ፓርቲዎች በቤቱ እንዲኖሩ አይፈቅድም። ይህ በሁሉም የብሔር ፖለቲካ በነገሠባቸው የዓለም ሀገራት በሙሉ የታየ ሐቅ ነው። ከዚህ አንጻር እስካሁን በነበረው ሂደት የብሔር ፖለቲካ ላይ የነበሩ ኃይሎች ተሰድደው ሲንቀሳቀሱ ነበር የሚስተዋለው።

አሁን አዲስ በተፈጠረው የፖለቲካ መድረክ ደግሞ የብሔር ፖለቲካ ገንኗል። በአንድ ክልል አማራን እንወክላለን፣ ኦሮሞን እንወክላለን የሚሉ ኃይሎች በሙሉ ከያሉበት መጥተው ለሕዝባቸው አለን ማለት መጀመራቸው በራሱ የዜግነት ፖለቲ ጨዋታን ከባድ ያደርገዋል። ኢሕአዴግ በቋንቋ ላይ ተመስርቶ የፈጠረው ፌዴራሊዝም ብሔርን እንደመከለያ እና ብቸኛ አዳኝ አድርጎ የሚያይ ትውልድ እና ዜጋ በመፍጠሩ ዜግነተን የሚያቀነቅን ፓርቲ በዚያ አካባቢ ቢንቀሳቀስ ውጤታማነቱን ጥያቄ ወስጥ ይከትተዋል።

እንደ ምሳሌም በቅርቡ የተመሰረተው የግንቦት ሰባት፣ ሰማያዊ፣ኢዴፓ እና አንድነት ፓርቲዎች ውህደት የዜግነት ፖለቲካ ላይ እንደሚያተኩር ተናግሯል። ከምርጫ 97 በፊት በመላው ኢትዮጵያ እንደአሸን ፈልተው የነበሩት ፓርቲዎች በአብዛኛው ኢትዩጵያዊ ቀለም ኖሯቸው አንድነት እና ዜግነት ላይ ያተኮሩ ቢሆኑም (ከነሙሉ ድክመታቸውም ቢሆን) አሁን ደግሞ ያ ቀለም ጠፍቶ ብዙዎች በብሔር ፖለቲካ ተውጠው መታየታቸው የሀገሪቱን የፖለቲካ አዙሪት የቤርሙዳ ትሬያንግል አድርጎ እንዳያስቀረው የብዙዎች ስጋት ነው።

በተለይም ካለፉት ሰባት ወረት ወዲህ በመላው ኢትዩጵያ የታየው የብሔር ግጭት ታስሮ እንደተፈታ ጥጃ በየቦታው ሲፋንን መታየቱ በብዙዎች ዘንድ ኢትዮጵያዊነት ስለማበቡ እና ዜጎች በዜግነታቸው ብቻ የሚከበሩባት አንድ ሃገር መገንባት ስለመቻሉ ጥያቄ ውስጥ ከትቶታል።

በዚህ ዘመን ብሄር የዚህች ሀገር አፍራሽ ሐሳብ እና ጠባብ አመለካከት ነው ብሎ ለማሳመን መሞከር በፖለቲካው ተጠላልፈው እርስ በርስም መስማማት ላቃታቸው ኃይሎች አማራጭ መድኃኒት ስለመሆኑ ጥርጣሬ አለ። በዚህ ስሌት የዜግነት ፖለቲካን ለማራመድ መላውን ሀገር አዳርሶ አንድ ሐሳብ ማምጣት ግድ ነውና ለዚያ የሚሆን ሕዝባዊ ዝግጁነት በዚህች ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ገና ይቀረዋል።

ነገር ግን ረጅም ጉዞ ከአንድ እርምጃ ነውና የሚጀመረው አሁን አሃዱ የተባለው አዲስ የሚመስል ግን የኖረ የፖለቲካ መንገድ ኢትዮጵያን ካለባት ማጥ ለማውጣት ተስፋ የሚጣልበት አካሄድ ነው ብሎ መገመት አያሳፍርም። ምክንያቱ ደግሞ በብሔር ላይ የተመረኮዘ ፖለቲካ ይዘው የሚጓዙ ስታሊናዊ መርህ ተከታዮች ሁሉ መጨረሻቸው አላምር ብሎ መታየቱ ነው። ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፉ የፖለቲካ ልምድ የተለየ ተዓምር ሊፈጠርባት የማትችል ሀገር ናትና ብሔር ሳይሆን ዜግነተን መሰረት ያደረገ ፖለቲካ መስፈኑ ለመጪው ዘመን አንድ መንደርደሪያ ሊሆን እንደሚችል አስረግጦ መናገር ይቻላል። በኢትዮጵያ የሚገኙ ክልል አቀፍ ፓርቲዎች እና ሌሎችም በየራሳቸው ፍላጎትና የትግል ስለት የተቋቋሙ ፓርቲዎች ወደዜግነቱ እያጋደሉ የብሔር አስተሳሰብን እያከሰሙ እና አንድነትን እያጎለበቱ መጓዛቸው ለዚህች ሀገር የቆዩ ህመሞች ፈውስ ቢሆን እንጂ ጉዳት የለውም።

# ከኤርትራ መንግሥት ድንበር መዝጋት ጀርባ ምን አለ?

በተስፋዬ ሽብሩ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኂላ ቅድሚያ ትኩረት የሰጡት ለኢትዮ ኤርትራ ዳግም ግንኙነት ነበር:: ላለፉት 20 ዓመታት ሰላምም ጦርነትም የሌለበት ቀጠና ፈጥረውና በስጋት ተወጥረው የቆዩት ሁለቱ ሀገራት በወርሃ ሐምሌ 2010 ዓ.ም በመንግሥታት ደረጃም ሆነ የሕዝቦች ግንኙነት በመጀመር በውጥረት ተሞልቶ የነበረውን ቀጠና ወደ ሰላማዊ የሕዝቦች ትስስር ለመመለስ ችለዋል:: ይህም ክስተት ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከአገር ውስጥም ሆነ ከዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ ከፍተኛ አድናቆትንና ድጋፍን አስገኝቶላቸዋል::

የውጥረቱ መርገብ ለሁለቱ አገሮች የማይናቅ ጠቀሜታ እንዳለው ቢታወቅም ለኤርትራውያኑ ግን የተለየ ቦታ እንደነበረው በጊዜው ፕሬዝዳንት ኢሳይያስ አፈወርቂ ገጽታ ላይ የነበረው የደስታ እና የስሜት እርካታ ምስክር ነው::የኤርትራ ሕዝብም ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ያደረገውን አቀባበል መለስ ብለን ስናስታውስ ኤርትራውያኑ በብዙ መልኩ ምን ያህል ፈተና ውስጥ እንደበሩ ማስረጃ ሊሆነን ይችላል::

በተለይ ኤርትራውያን በተደረገው እርቀ ሰላም፣ ደስታቸው ልዩ ነበር ፤ሁኔታው በከፍተኛ የኢኮኖሚ ድቀት ውስጥ ለምትገኘው ትንሿ አገር ሰርግና ምላሽ ሆኖ አልፏል:: የአገሮቹ ግንኙነት ለሁለቱም አገሮች ይዞት የመጣው መልካም አጋጣሚ የመኖሩን ያህል ግንኙነቱ ስርዓት ተበጅቶለትና በሕጋዊ ማዕቀፍ የማይሄድ ከሆነ ዳግም ግጭት እንዳይቀሰቅስ ስጋት ያላቸው አስተያየት ሰጪዎች ነበሩ::

ሰሞኑን ታዲያ ዳግም ክፍት የተደረጉት መንገዶች መዘጋታቸውን የዛላንበሳ ነዋሪዎች እየገለፁ ይገኛሉ:: ከሐምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በአስመራ ያደረጉትን ጉብኝት ተከትሎ ግንኙነቱ በመሻሻሉ፣ ተከፍቶ የነበረው የሁለቱም አገራት ዜጎች ሲመላለሱበት የቆየው የኢትዮ ኤርትራ ድንበር ከረብዕ ታህሳስ 17 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ተዘግቷል::

ድንበሩ የተዘጋበት ምክንያት ባይታወቅም፣ በአካባቢው ያሉ ምንጮች ድንበሩ ሊዘጋ የቻለው በኤርትራ መንግሥት ውሳኔ መሆኑን ይገልፃሉ:: በዚህ የተነሳ ከሁለቱ አገራት የሚነሱ ዜጎች የመንግሥታቸውን ፈቃድ ሳያገኙ መንቀሳቀስ እንደማይችሉ ተነግሯል:: የኤርትራ መንግሥት በቅድሚያ በዛላምበሳ በኩል ያለውን ድንበር በመዝጋት፣ በመቀጠልም በራማ ድንበር በኩል ተመሳሳይ እርምጃ በመውሰድ የዜጎችን እንቅስቃሴ አግዷል:: በቡሬ ድንበር አስካሁን ድረስ አለመዘጋቱም ለመረዳት ተችሏል::

የኢትዮ ኤርትራ ድንበር ከተከፈተ በኂላ በቀን ከ1000 እስከ 2000 ተሽከርካሪዎች ከኤርትራና ከኢትዮጵያ እንደሚመለሱ እና በየቀኑ ከኤርትራ ድንበር በማቋረጥ ወደ ኢትዮጵያ 390 ያህል ሰዎች ይገቡ እንደነበር ታውቋል:: በድንበሮች አካባቢ ንግድ በመስፋፋቱ በተለይም በዛላምበሳ ፤በራማና በቡሬ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እንደነበር ተጠቁሟል:: ድንበሩ ከተከፈተ ካለፉት ስድስት ወራት ወዲህ ብቻ 27 000 ኤርትራውያን ኢትዮጵያ ገብተዋል::

የድንበሩ መዘጋት ሊኖረው የሚችለው እንድምታ ምን ሊሆን ይችላል? የሚለውን ደምድሞ መናገር ባይቻልም የተለያዩ ወገኖች የሚያነሷቸውን መላምቶች መጥቀስ ይቻላል:: የኤርትራ መንግሥት የድንበር መዝጋት እርምጃውን የወሰደው የቀድሞው መከላከያ ሚኒስትር ላይ ከተደረገው የግድያ ሙከራ ጋር በተያያዘ ሊሆን ይችላል የሚለው ግምት ሚዛን ይደፋል :: የመግደል ሙከራውን ያደረገው ከትግራይ የመጣ ግለሰብ ነው የሚሉ ያልተረጋገጡ ጭምጭምታዎች ተሰምተዋል:: ሌላው ምክንያቱ በግልጽ ባይታወቅም የድንበር መዝጋቱ እርምጃ በኤርትራ መንግሥት በኩል ከትግራይ ክልላዊ መንግሥት ጋር በተያያዘ የመከፋት ስሜት እንዳለ የሚያመለክት መሆኑ ነው:: በትግራይ በኩል ያለው ድንበር ተዘግቶ በቡሬ በኩል ያለው ክፍት መሆኑ የኤርትራ መንግሥት በትግራይ በኩል ያለው ድንበር ስጋት እንደደቀነበት ማሳያ ሊሆን ይችላል የሚሉ አስተያየት ሰጪዎች አሉ::

የሕወሓት ደጋፊዎችና አክቲቪስቶች በኤርትራ መንግሥት ላይ የከፈቱት መጠነ ሰፊ ትችትና ውግዘት ሲታይ በትግራይ ክልልና በኤርትራ መንግሥት መካከል ያለው ግንኙነት ጤናማ እንዳልሆነ ማሳያ ሊሆን ይችላል:: ወትሮም ለሕወሓት መራሹ መንግሥት በጎ አመለካከት የሌለው የኤርትራ መንግሥት መቀሌ የመሸገውን የሕወሓት ቡድን በጥርጣሬ ከማየት አልቦዘነም:: ውጥረቱ በዚህ የሚቀጥል ከሆነ ደግሞ በከፍተኛ ጥረት የተገኘው የሁለቱ አገራት ዘላቂ ግንኙነት ሕወሓት በዘረጋው ወጥመድ አደጋ ሊጋረጥበት ይችላል የሚሉ አካላት አልታጡም::

## ወጥመዱ ይሰበራል?

በመቀሌ የመሸገው ጥቂት የሕወሓት ቡድን የኢትዮ ኤርትራን ዳግም ግንኙነት በአዎንታዊ ጎኑ ተቀብሎታል ብሎ መናገር የሕወሓትን የፖለቲካ ቁመና አለማወቅ ሊሆን ይችላል:: በተለይም ለእርቀ ሰላሙ መውረድ ከፍተኛውን ድርሻ የተወጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ መሆናቸው በሕወሓቶች መንደር ጎምዛዛ ሐቅ ሆኖባቸው ከርሟል:: ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደረግ የፖለቲካ ጨዋታ የመሪነት ሚናውን እኛ ካልተወጣን በሌላው ሊሞከር አይገባም ከሚል የ"ከኔ በላይ" አባዜ የማይለቀው ሕወሓት የአገራቱ ግንኙነት ላይ ያረገዘው ቂም አይኖርም ብሎ መገመት አይቻልም:: ሕወሓት በግንኙነቱ ላይ አላስፈላጊ ውዝግብ ለመፍጠር የዘረጋው ወጥመድ ይኑር አይኑር ወደፊት የሚታይ ቢሆንም የተዘረጋ ወጥመድ የሚኖር ከሆነ ወጥመዱን ለመስበር ከሁለቱ መንግሥታት አዋጭ መላ መፈለግ የሚጠበቅ ይሆናል::

## ያልተጠረጠረ ተመነጠረ

የኤርትራ መንግሥት በዛላንበሳ በኩል ያለውን ድንበር ለመዝጋት መወሰኑ በሕወሓት ላይ ካለው የመጠራጠርና ያለመተማመን መነሻ ሊሆን እንደሚችል አንዳንድ ለጉዳዩ ቅርበት ያለችው አካላት ይናገራሉ:: ሕወሓት በጎሳ ፖለቲካ የተቀየደና በሴራ ፖለቲካ ትንተና የተሞላ ድርጅት እንደመሆኑ በአገሪቱ ውስጥ በሚካሄዱ የፖለቲካ ጉዳዮች ውስጥ እጁን በማስገባት መንቀሳቀሱ የታወቀ ነው:: የሕወሓት የበላይነት የሌለባትን ኢትዮጵያ ላለማየት የሚውተረተረው ሕወሓት ይህ ካልሆነለት ቀድሞ ወደተነሳበት የትግል ጅማሮው በመሄድ ትግራይን ከኢትዮጵያ የመገንጠል፣ የጨነገፈ ሕልሙን ለማሳካት ፍላጎት ሊያድርበት ይችላል የሚሉ ወገኖች አሉ:: ይህን በተመለከተ አንዳንድ የድርጅቱ ደጋፊ ነን ባዮች በማኅበራዊ ሚዲያ በኩል የሚለቁት ውዥንብር ጠቋሚ ይመስላል::

የኤርትራ መንግሥት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የጀመረው የጠበቀ ወዳጅነት ለሕወሓት ቡድን የሚመች አይሆንም የሚሉት አስተያየት ሰጪዎች፤ ዙሪያውን አጋር ያጣው ሕወሓት፣ የኤርትራ መንግሥት ላይ ችግር የሚፈጥሩና ራሱ ሊያሽከረክረው የሚችል "ሳታላይት" ኃይል ለመፍጠር አይሞክርም ተብሎ እንደማይገመት እነዚሁ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ይጠቅሳሉ:: በዚህ የተነሳ የኤርትራ መንግሥት በትግራይ በኩል ያለውን ድንበሩን ለመዝጋት ቢነሳ ኢምክንያታዊ ሊሆን አይችልም በማለት ይናገራሉ:: "ያልጠረጠረ ተመነጠረ" የሚለውን ብሂል ቀድሞ አስቦ ሊሆን እንደሚችልም፣ ጨምረው ይገልፃሉ::

የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በቅርቡ ባደረገው ሪፎርም በአራት እዞች የሰራዊት ምደባ ሲያደርግ በርካታ ወታደሮች ውጥረት ከነበረበት የኢትዮጵያና የኤርትራ ድንበር አካባቢ ማንቀሳቀሱን አስታውቆ ነበር:: ስለጉዳዩ የተጠየቁት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ መለስ ዓለም የድንበር መዘጋቱ መረጃ እንደሌላቸው ገልፀው ወደፊት በጉዳዩ ላይ ዝርዝር ማብራሪያ መንግሥት እንደሚሰጥ ጠቁመዋል::

የኤርትራ መንግስትም ወደ ኢትዮጵያ ለሚጓዙ ዜጎች የመውጫ ቪዛ ግዴታ መጣሉ ተሰምቷል:: አገራቱ ሰላም ከፈጠሩ በኂላ ዜጎች ለወራት በነጻነት ሲዘዋወሩ ቢቆዩም ካለፈው ሳምንት ጀምሮ በኤርትራ የድንበር ተቆጣጣሪዎች ኤርትራውያን ወደ ኢትዮጵያ መግባት ተከልክለዋል::

# አፋር አሁንም አላረፈችም

**በሔማስ ታፈረ**

በሀገራችን ከሚነሰው የለውጥ ንፋስ ጋር ተያይዞ በሀገሪቱ አራቱም ማእዘናት ዘርን መሠረት ያደረጉ ግጭቶችን መስማት እየተለመደ መጥቷል:: ባሳለፍነው ሳምንት በአፋርና በኢሳ ጎሳዎች መካከል የከረረ ግጭት ተፈጥሮ ነበር:: ይህ ግጭት አስቀድሞም በውሃና በግጦሽ መሬት ምክንያት ይቀሰቀስ የነበረ ሲሆን አሁን ግን ፖለቲካዊ ይዘት ተላብሶ፣ መልኩን ቀይሮ ወደ መረረ ግጭት አምርቷል:: ሌላው የችግሩ መንስኤ ከዓየር በዓየር ንግድ ጋር የተያያዘ ነው:: ኮንትሮባንዲስቶች ከበርበራ እስከ ቆሬ ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት ሊቆጣጠራቸው የማይችላቸው ቦታዎችን በመጠቀም፣ በርካታ የኤሌክትሮኒክስና ሌሎች ልዩ ልዩ እቃዎችን ያስገባሉ:: በዚህም የተነሳ የክልሉ መንግሥት ይሄንን ከመስመር የወጣ እንቅስቃሴ ለመጠበቅ ልዩ ኃይሉን ያሰማራ ቢሆንም የሶማሌ ጎሳዎች በሚኖሩበት አካባቢ የሚገኙት ኮንትሮባንዲስቶች በደንብ የታጠቁ በመሆናቸው፣ ከልዩ ኃይሉ ጋር ግጭት ተፈጥሮ በአስራዎቹ የሚጠቀስ የሰው ሕይወት ሊጠፋ ችሏል::

ሌላው የፖለቲካ ትርፍን ለማጋበስ የሚውተረተሩት ኃይሎች በግጭቱ ሒደት ላይ የራሳቸውን ቤንዚን አርከፍክፈዋል:: የአፋር ሕዝብ፣ ከጅቡቲ እና ከሱማሌ ጋር የተቀናጀ ጥቃት ነው የገጠመው:: የማእከላዊ መንግሥትም ይህንን ያውቃል:: ግን መፍትሄ በማምጣቱ ረገድ ድክመት ይታይበታል:: ይህንን ግጭት የጀመሩት የኢሳ ጎሳ ኮንትራባንዲስቶች ሲሆኑ ልዩ ኃይሉ ሲገባ ወደ ሰለማዊው ሕዝብ ላይ በቀጥታ ተኩስ ነው የተከፈተባቸው::አንዳንድ የፓለቲካ ታዛቢዎች ከዚህ ብጥብጥ ጀርባ የተሸነፈው የሕወሓት ክንፍ ሊኖር እንደሚችል ግምታቸውን ሰንዘረዋል:: ከዚሁ ከግጭቱ ጋር ተያይዞ አዋሽ አርባ አካባቢ አንድ በጥብቅ ሲፈለግ የነበረ የአብዲ ኢሌ ልዩ ኃይል እንደተያዘ መረጃዎች ይጠቁማሉ::

በዚ ግጭት በአፋር በኩል ወደ 20 የሚጠጉ ሰዎች ሞተዋል:: በጠቅላላ በሁሉም በኩል ከ40 በላይ የሚሆን የሰው ሕይወት አልፏል::በተለይ ከሱማሌ በርበራ ጀምሮ ኃይል በማሰባሰብ ብዙ ተሽከርካሪዎችም መኪናዎችም እየገቡ ሲሆን የአፋር ሕዝብ ግን ምንም ዓይነት ጥበቃ እየተደረገለት አይደለም:: አሁን በሱማሌና በጅቡቲ ሕዝብ ጣልቃ ገብነት የተነሳ የአፋር ሕዝብ እየተጠቃ ሲሆን በዘላን ደረጃ ሊያዙ በማይችሉ ዘመናዊ መሳሪያዎች ጥቃት እየደረሰበት እንደሆነ ከአካባቢው የሚወጡ ምንጮች ይገልጻሉ:: ይህም ማለት ከጀርባ ኃይል ያለው ድጋፍ መኖሩን የሚያስረግጥ ነው:: መንግሥት ይህንን ችግር አስቀድሞ መፍታት ያልፈለገበት ምክንያትም ከወሰን ማካለል ጋር በተያያዘ እንደሆነም ይነገራል:: ሕወሓት በቀደመው ጊዜ ከሠራቸው ደባዎች አንዱ የአፋር ክልልን በተገቢው ረገድ ማካለል አለመቻሉ ነበር::የችግሩም ትልቁ መንስኤ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው:: አፋሮች ልጆቻቸው እየተገደሉባቸው ፣እየተደፈሩባቸው በብዙ ጥቃት ውስጥ እያለፉ ቢሆኑም ዛሬም ድረስ መፍትሄ አላገኙም::

“የሁለቱንም ሕዝብ በማገናኘት የሕዝብ ለሕዝብ ውይይት እንዲደረግ ዝግጁ መሆናቸውን ገልፀው ፤ነገር ግን መንግሥት ለችግሩ ትኩረት ሰጦ መፍትሄ ለማምጣት በደንብ መሥራት ይጠበቅበታል:: ይህንን ለማገዝ ከመንግሥት ጎን ለመቆም ዝግጁ ነን:: ለመንግሥትም ያቀረብናቸው ጥያቄዎች አሉ:: እስካሁን ግን ያገኘነው መልስ የለም:: መንግሥት በትክክል የመከላከያ ሪፎርም አድርጓል ለማለትን እንቸገራለን:: ምክንያቱም ከነዚህ ከ2ቱም ጦሮች መካከል ከኮንትራባንዲስቶች ገንዘብ እየተሰጣቸው ጥቃት እያደረሱ ያሉ ኃይሎች እንዳሉ ደርሰንበታል::” በማለት የሰብኣዊ መብት ተሟጋች የሆኑት አቶ ጋአስ መሀመድ ለመጽሔታችን በስልክ ስለጉዳዩ አብራርተዋል::

## የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊው ባለሥልጣን

በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆነው የተሾሙትን አቶ ፍፁም አረጋን በመተካት አቶ አበበ አበባየሁ ቸኮል የኢትዮጵያ ኢንቨንስትመንት ኮሚሽን ዳይሬክተር ጄኔራል ሆነው ተሹመዋል::

የጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ ቀኝ እጅ የሆኑት አበበ ቀደም ብሎም የኢንቨስትመንት ኮሚሽኑ ምክትል በመሆን ያገለግሉ ሲሆን፤ የጠቅላይ ሚንስትሩ የሕግ ጉዳዮች አማካሪ ነበሩ::

የሕግ ምሁሩና ባለምጡቅ አዕምሮው አበበ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ወርቅ ተሸላሚ ምሩቅ ሲሆኑ፣ ከደቡብ አፍሪቃው ዌስተርን ኬፕ ዩኒቨርሲቲ (University of Western Cape) በአለም አቀፍ ንግድና ኢንቨስትመንት ህግ የማስተርስ ድግሪ ያገኙ ሲሆን ፤ ከብሪታንያው ደንዲ ዩኒቨርሲቲ ( University of Dundee) በኢነርጂ ሕግና ፖሊሲ በከፍተኛ ማዕረግ የተጨማሪ ማስተርስ ድግሪ ባለቤት ናቸው::

አበበ አበባዬሁ በአለም አቀፍ ንግድና ኢንቨስትመት ከ10 አመት በላይ ያካበተ ልምድ ያላቸው ከመሆናቸውም በላይ የአለም ባንክ አካል በሆነው በአለም አቀፉ የፋይናንስ ኮርፖሬሽን (IFC - International Finance Corporation) የሰሩ ሲሆን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም በሕግ መምህርነት አገልግለዋል::

## ተገቢ ሹሙ ለተገቢ ቦታ

አምባሳደር ሄኖክ ተፈራ በፈረንሳይ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ሆነው ተሹመዋል::

የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በኒስና ፓሪ የተማሩትና ለዶክትሬት ዲግሪያቸውም እጩ ተማሪ ወደነበሩባት ፈረንሳይ በአምባሳደርነት የተሰየሙት አቶ ሄኖክ የሕግ ምሩቅና የኢትዮጵያ አየር መንገድ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ናቸው:: ከአምባሳደር ቤተሰብ የተወለዱት አቶ ሄኖክ የቀድሞው አምባሰደር ተፈራ ሻውል ልጅ ናቸው::

ከዓለማችን ኃያል ሃገሮች አንዷ በሆነችው፣ በበርካታ የአፍሪቃ ሀገራት የውስጥ ፖለቲካ ቀጥተኛ እጅ ላላትና ከኢትዮጵያ ጋር ከመቶ ዓመታት በላይ የቆዬ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ወዳላት ፈረንሳይ ቋንቋዋን የሚያውቅና የሕግ ባለሙያ የሆነ በመመደቡ ፤ ያለፈው መንግሥት እንደ ተሾመ ቶጋ ያሉትን በመሾም የሠራውን ስህተት ባለመድገማቸው ሊመሰገኑ ይገባል::

## ባለተሰጥኦው አምባሳደር

በምዕራብ አፍሪቃዊቷ ሴኔጋል የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሆነው የተሾሙት ኡስታዝ አምባሳደር ሐሰን ታጁ

በቅርቡ ሁለት አዳዲስ መጽሐፎች ለህትመት በቅተው ነበር፤

የታላቁ ነብይ ወላጆች እና የሀሳብ ጠብታዎች የሚሉ::

ሁለቱም ስለ ነቢዩ ሞሀመድና ቤተሰቦቻቸው የሚተርኩ ናቸው:: ሁለቱም መፃኅፍት በእስልምና ዕምነት ተከታዮች ብቻ ሳይሆን የሌላ ዕምነት ተከታይም ለጠቅላላ ዕውቀት ገዝቶ ወይም ተውሶ ያነበባቸውና በርካታ መረጃዎችን ያካታቱ በደነፈናው ተነባቢ ነበሩ :: የሁለቱም መፃህፍት ፀሐፊ ደግሞ አምባሰደር ሐሰን ታጁ ነው::ኡስታዝ ሐሰን ታጁ በዶ/ር ዐቢይ በተቋቋመው 9 የሙስሊሞች የጋራ ለውጥ ምክር ቤት አባል ነው::

በባሕሪው ፣ በዕውቀቱ ፣ በሥራው ፣ በችሎታውና በዉጤታማነቱ ታላላቆች ‹አንቱ› ይሉታል:: በ44 ዓመቱ ፤ (ከ150 በላይ የታተሙ ፤ ከ45 በላይ ያልታተሙ) 196 የሚሆኑ መጽሓፍትን ያዘጋጀ፣ ከ30 በላይ መጽሓፍትን አርትኦት የሠራ፣ ከ300 በላይ መንፈሳዊና ዓለማዊ መጣጥፎችን ያስነበበ፣ በኢትዮጵያ ለ3ተኛ ጊዜ ቁርዓንን ተርጓሚ፣ በኢትዮጵያ የመጀመሪያዉ የቁርዓንን ማብራሪያ አዘጋጅ፣ በኢትዮጵያ የመጀመሪያዉ የነብያዊ ትዉፊት ድርሳናትን ተርጓሚና ማብራሪያ አዘጋጅ፣ ከ1988 እስከ 2001 የተለያዩ ጋዜጣና መጽሔቶችን በማዘጋጀትና በአምደኝነት ሲሠራ የነበረ፣ የሕትመት ቤቶችን ሥራ በማረምና በመገምገም ለተነባቢነት ሲያበቃ የኖረ፣ አሁንም በጥበብ ወላድነት ላይ የሚገኝ የቀለም ቀንድና የእስልምና ሊህቅ ነው ኡስታዝ ሐሰን ታጁ::

## አዲስ አባባ ዩኒቨርስቲ የቀድሞውን ልሂቅ መልሶ አገኘ

የአርበኞች ግንቦት 7 ሊቀመንበር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የአንጋፋው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቦርድ አባል በመሆን ተሹመዋል::

ፕሮፌሰሩ እስከ ምርጫ 97 ድረስ በዩኒቨርሲቲው የኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል ያለምንም ክፍያ በመምህርነት ማገልገላቸው የሚታወቅ ነው::

ኘሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በአሁኑ ሰዓት በዩኒቨርሲቲው የቦርድ አባልነት የመጀመሪያ ንግግራቸውን ለዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ በማሰማት ላይ ይገኛሉ::

# ግብረገብነትን የተራቆቱት ማስታወቂያዎቻችን



ኃይሉ አሰለፍ ገብሬ

ሰሞኑን ሲጃራን እና ከተወሰነ መጠን በላይ አልኮል ያላቸውን የአልኮል መጠጦችን ማስታወቂያ፣ ሽያጭ የተመለከተ ሕግ በሀገራችን ፀደቀ የሚል ዜና ያነበብኩ መስሎኝ ነበር:: ባነበብኩት ዜና የተጠቀሱትን የተወሰኑ የአዲሱ ሕግ ድንጋጌዎችን፣ በተለይ ከ1.5 በመቶ በላይ የአልኮል ይዘት ያላቸው መጠጦችን ከምሽቱ ሦስት ሰዓት በፊት በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ማስተዋወቅ የሚከለክል መሆኑን በትክክል አስታውሳለሁ:: ምክንያቱም የሕግ ክልከላው እጅግ ውስን በሆኑት በሀገራችን የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች ከማስታወቂያም በላይ ፊታውራሪ ሁነው የዘለቁትን የቢራ ምርቶች ማስተወቂያ የሚጨምር በመሆኑ ነው:: ዜናውን ካነበብኩ በኂላ የነበረው ቀጥሏል፣ የታረመ ነገር የለም:: ስለዚህ ያነበብኩት ዜና ያወጀው ሕጉ መፅደቁን ሳይሆን መርቀቁን፣ ወይም የረቀቀው ሕግ ወደሚመለከተው አካል መመራቱን ነበር ማለት ነው::

በከፍተኛ ወጭ፣ አማላይ በሆነ አቀራረብ ሃያ አራት ሰዐት በየሚዲያዎች የሚቀርቡት የቢራ ማስታወቂያዎች ላይ ለዓመታት ጥያቄ አልነበረኝም:: ነገር ግን ከዚህም በላይ የግለሰቦችን ሕይወት የሚቀይሩ ሽልማቶቻቸውን በተመሳሳይ መንገድ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች በተደጋጋሚና ካለምንም ገደብ ለሕዝብ ስለሚያቀርቡበት ሁኔታ፣ ሁለታችንም ቢራቸውን እየተጎነጨን ቢሆንም ለአንድ ጓደኛዬ ከአንድ ወር በፊት አንስቼለት ነበር:: ጓደኛዬ የሥራ አለቃውን እንደ ምንጭ ተጠቅሞ በቢራ ጠማቂዋ ሃገር ጀርመን የቢራ ማስታወቂያዎችን በተመሳሳይ መንገድ ማስተላለፍ የሚቻለው ልጆች ከተኙ በኂላ በምሽት እንደሆነ ነገረኝ:: በሀገራችን ወደፊት ፀድቆ ተግባራዊ የሚሆነው ሕግ ተመሳሳይ ይዘት አለው:: የነበረውንና ዛሬን ከአሉታዊ ውጤቶቹ ጋር ገምግመን የሕጉን መዘግየት፣ አስገዳጅ ሕግ ከሌለ ኃላፊነት የማይሰማቸው፣ ግድ የሌላቸው የሚድያ ተቋማትን፣ የማስተዋቂያ ባለሙያዎችንና ቢራ ጠማቂዎች ልንታዘብ እንችላለን::

የቢራ እንዱስትሪውን ሄኒከንን የመሰሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ከተቀላቀሉት በኂላ በአምራቾች መካከል ካየነው የገበያ ፍክክር በተጨማሪ፣ ከዐሥራ ስምንት ዓመት በላይ ለሆኑ የማይሸጥ ምርት መሆኑን በማስታወቂያ ሰማን:: ከዚያ በኂላ ሁሉም አምራቾች በማስታወቂያዎቻቸው ሲቀባበሉት ኃላፊነታቸውን እየተወጡ እንደሆነ አስቤ አወንታዊ የሆነ እምነትና ተስፋ ነበረኝ:: አሁን ግን በሌሎች ሀገሮች ካላቸው ልምድ አንፃር፣ እያወቁ ለዓመታት በዚህ መልኩ መቆየታቸው፣ ዛሬም በመጨረሻ ሕጉ ከረቀቀ በኂላ፣ ነገ ሕገ ወጥ በሚሆን ሥራ ላይ መቀጠላቸው የሚያስገነዝበው ንቀታቸውንና የጥቅም ሃራራቸውን ብቻ መሆኑን ተረድቻለሁ:: ማኀበራዊ ኃላፊነት የሚባለው ነገር ከገበያ መሳርያነት የዘለለ እንዳልሆነ የሚመሰክርባቸው ሥራ ሁኖ አግኝቸዋለሁ:: በዚህ ጽሑፍ አጠቃላይ የገበያ ማስተዋቂያዎችን ለማንሳት የዳረገኝ ከላይ የገለፅኩት ሁኔታ ሲሆን ዘርፉ የተመሳሳይ ጉልበተኞች መፈንጫ ብቻ መሆኑን መረዳት ይቻላል::

ማስታወቂያ በዋናነት አዲስ ምርትና አገልግሎት የሚተዋወቅበት፣ ወደ ገበያ የሚዘለቅበት፣ ልዮነቶች የሚገለጡበት ቢሆንም በአሰልችና ተደጋጋሚ ለፈፋዎቻቸው በሀገራችን ተግባሩን በገንዘብ ጡንቻቸው የተቆጣጠሩት የገበያ፣ የገቢ፣ የትርፍ ችግር የሌለባቸው እድሜ ጠገብ የቢራ ፋብሪካዎችና ተመሳሳይ ባሕሪ ያላቸው ባንክና ኢንሹራንስን የመሰሉ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ናቸው::

የመዲናችንን ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያዎች ቀያይሮ የሚሰማ፣ የቴሌቭዥን ሥርጭቶችን የሚከታተል አድማጭና ተመልካች፣ ከተማዋ ሌላ ሥራ የሌለባት መሸታ ቤት ብትመስለው አይደንቅም:: የገንዘብ ድጋፍ ከሚያገኙ የየሚዲያዎቹ መርሃ ግብሮች መካከል ደግሞ የስፖርትና የውጭ እግር ኳስ ተንታኞችና መርሃ ግብሮቻቸው ቀዳሚዎች ናቸው:: በእነዚህ መርሃ ግብሮች ስለ አውሮጳ ሀገሮች የተለያዩ የእግር ኳስ ውድድሮች፣ ተጨዋቾች፣ አሰልጣኞች፣ ደጋፊዎች…ወዘተ በጥልቀት ከመተንተኑም በተጨማሪ የሚካሄዱ ጨዋታዎች ከስቱዲዮ በቀጥታ ለሬዲዮ አድማጮች ይተላለፋሉ::

በአንዱ የእግር ኳስ ጨዋታ የቀጥታ ስርጭት ያዳመጥኩት ግን የተለየ ነበር:: የሚተላለፈው ጨዋታ በእንግሊዝ ሀገር የሚካሄድ ቢሆንም የመርሃ ግብሩ መሪና ሁለት ወይም ሦስት ተንታኝ ባልደሮቦቹ በቢራ ጠማቂውና ሌሎች ተቋሞች የገንዘብ ድጋፍ ስርጭቱን የሚያስተላልፉት አሜሪካን ሃገር ካረፉበት ሆቴል መሆኑን በኩራት እየገለፀ "ስፖንሰሮቹን" ያመሰግን ነበር::

ምንም ማድረግ አይቻልም፤ ሲፈለግ ይህንንም ሥራ ማድረግ ይቻላል:: ለሥራው ብሄራዊ ባንክም የውጭ ምንዛሬ ይፈቅዳል ማለት ነው:: የበለጠ እርር የሚያደርገው ግን ለዚህ የወጣው ወጭ የተቋሞች የገበያ ማስታወቂያ፣ የክቡራንና ክቡራት የእግር ኳስ አፍቃሪ ደንበኞቻችን እርካታ የወጣ ወጭ ነው ተብሎ ከተመዘገበ፣ በዚህ ምክንያት ኩባንያዎችም ይሁን አስተዋዋቂዎች የሚጠበቅባቸው ግብር፣ የድሃ ሃገር ገቢ ከተቀነሰላቸው ነው:: እንደሚቀነስ ስለሚጠበቅ እርር ድብን ከማለት ውጭ አማራጭ ያለ አይመስልም::

የእንግሊዝ ኳስ ለማየት ፈቃድ ለጠየቁት ሠራተኞቹ፤ "እግር ኳስን ማየት ከሥራ የበለጠ ፋይዳው ዐይታየኝም ባይሆን የተሻለ ፋይዳ ያለው ራሳችሁ ስትጫወቱ ስለሆነ ከተቻለ ልፈቅድላችሁ የምችለው ለመጫወት ብቻ ነው፤" ብሎ የመለሰ የሥራ አለቃ አውቃለሁ:: እግር ኳስ መዝናኛ ቢሆንም ከላይ በተገለፀው መልኩ የእነዚህ ተቋማት የመጀመርያ ትኩረት ነው:: በዚህ ተጨባጭ ሁኔታ ስንት ስራዎች በማስተዋቂያ እጥረት፣ ከምርቶቻቸውና አገልግሎቶቻቸው ገበያ፣ ከፈላጊዎቻቸው ጋር ሳይገኛኙ ቀርተው ይሆን፤ ስንት ሠራተኛ በትነው፣ ከስረው ይሆን ብሎ ማሰብ ይቻላል:: የማስታወቂያ አየር ሰዐት ዋጋ ለማን ይቀመሳል ብሎ መጠየቅ ብቻ በቂ ነው::

ሌሎችም ቢሆኑ ተመሳሳይ ናቸው:: ይቆጥቡና ይሸለሙ፣ ከውጭ ሀገር የሚላክለወን ገንዘብ በእኛ ዘንድ ተቀብለው ይሸለሙ ወዘተ የሁሉም ባንኮች ማስታወቂያዎች ናቸው:: በትንሹ ቁጠባ፣ በጥረትዎና በልምድዎ ላይ የእኛን ጨምረን አብረን የእርስዎን ሥራ እናሳድጋለን፣ እርሰዎም ያድጋሉ እኛም እናድጋለን፣ ከእኛ ጋር ቢሰሩ የመኖርያ ቤት ወይም ሌሎች ችግሮችዎን ለመቅረፍ፣ ከፍላገቶችዎ ጎን ለመቆም ዝግጁዎች ነን፣ የሚል ልዩ ማስታወቂያ የለም:: የትንንሾች ቁጠባ፣ ተበታትኖ የሚላክ የውጭ ምንዛሬ ተጠራቅሞ የሚቀርብላቸው ለጉልበተኞች ብቻ ነው:: በሁሉም ባንኮች ተመሳሳይ ቢሆንም በሚሊዮኖች ይቆጥቡና ይሸለሙ ቁጠባ፣ በመንግሥት ከለላ የፈረጠመው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተበዳሪዎች በጣት የሚቆጠሩ መሆናቸውን በሰሞኑ ሰምተናል::

በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎቻችን ላይ ብዙ የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ፣ ከውጭ ምንዛሬ ወጭ የሚታደጉን አምራቾቻችን ድምፅ ጎልቶ አይሰማም:: ሂውማን ሄርን የመሰሉ ሸቀጦች፣ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች፣ የመጋረጃ፣ እና መሰል ሸቀጦችን አስመጭዎች፣ እና ላኪዎችን ለመወዳደር አይችሉም:: በተለይ ሥራው የበለጠ ለሚያስፈልጋቸው ለአዲስ ሥራ ጀማሪዎች፣ ለአነስተኛ ተቋማትና በሥራ ላይ ላሉ ግለሰቦች ሁሉ ዝግ ነው ማለት ይቻላል::

አጠቃላይ ሚዲያችን በተለያዩ የበጎ አድራጎትና በእርዳታ ክንውኖች፣ አስተሳሰቦችና መርሃ ግብሮች የተሞላ ነው:: ማስተዋቂያዎቻችን ደግሞ ስኬትን ከሥራና ጥረት ጋር ሳይሆን ከዕድል ጋር እያቆራኙ ቀጥለዋል:: ቢራ ጠማቂዎች ከዚህ በላይ ስኬትን ከቢራና ከጠጭነት ጋር ከሚገኝ ዕድል ጋር በማያያዝ ቀን ከሌሊት ሠርተዋል:: እያንዳዳችን ዛሬ እያወቅንም ሳናውቅም ለዓመታት ያየናቸው፣ የሰማናቸው፣ የቀመስናቸውና ያሸተትናቸው ነገሮች ድምር ውጤት ነን:: ስለዚህ የወደፊት ዜጎቻችን ዕድልንና እርዳታን ቁጭ ብለው የሚጠብቁ፣ ካገኙ መሸተኛ፣ ሀገር ደግሞ ትልቅ መሸታ ቤት ብትሆን አይደንቅም:: በከተሞቻችን የመኖርያ መንደሮች አካባቢ መጀመርያ የምትመለከቱትን የንግድ ሥራ ዓይነት አጢኑ:: ጃንቦና ቁርጥ ቤት ይመስለኛል:: ቁርጡን በጀማሪ መንደር እናውቀዋለን፣ የቤት ኪራይን ወጭ ጨምሮ፣ ማሽኖችንና የመገልገያ ዕቃዎችን በገፍ በማቅረብ የሚፈለፍሏቸው ቢራ ፋብሪካዎች ለጃምቦና ቢራ መቸርቸሪያ እንደሆነ የአደባባይ ምስጢር ነው::

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ለዓመታት ያቆየን የመንግሥት አካል ተጠያቂ ነው:: በሕግ ባይደነገግም፣ እኛ የምናውቀውን ኃላፊነት ለመወጣት፣ የግድ የሕግ ማዕቀብ የምንጠባበቅ፣ ለትውልድ አሉታዊ የሆኑ የመጨረሻ ዕድሎችን ካለ ኃላፊነት የምንጠቀም ባለ ድርሻ አካላት ሁሉ የድርሻችንን ማንሳት ይገባናል:: ይህንን እያወቁ ቸል ያሉ ፣በውጭ ሃገር ከነበሯቸው ተሞክሮዎች የቻሉትን ለዚች ሃገር ያላሰቡ፣ ትንሽ ጥረት ያላደረጉ ሁሉ የሞራል ጥያቄ ያለባቸው ይመስለኛል:: አመሰግናለሁ::



ደረጀ ይመር

# ኦነግ ከሁለት ያጣ ጎመን



## እንደ መግቢያ

ብሔራዊ ጭቆና በሚለው ተረክ ከቀረቡ የዘውግ ድርጅቶች መካከል የዕድሜ ባለጸጋው ኦነግ ዋንኛው እንደሆነ ይታወቃል::ይህ የጥፋት ተረክ ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር ፈጽሞ የማይሄድ፣ ባዕድ ይዘትን የተላበሰ ሲሆን በተረኩ ዙሪያ የተሰባሰቡት የፓለቲካ ኃይሎች በተገፊነት እና በተጠቂነት አውድ ውስጥ የሚወክሉትን ሕዝብ በመጨመር፣ቂምበቀልን በውስጣቸው አዝለው ለጥፋት መባተት መታወቂያቸው ነው::ይህ ተምኔታዊ ትንታኔ ለሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ፀጉረ ልወጥ እንደሆነ ለመረዳት የኋላ ገበናችንን ዞር ብሎ መመርመር በቂ ይሆናል::ጨቋኝ ተብሎ የተፈረጀው የአማራ ማኅበረሰብ በዘውጌ ተኮር ድርጅቶች ለሚስነዘርበት ሐሳዊ ተረክ ባእድ ነው::ወለዬውን፣ጎጃሜውን፣ጎንደሬውን እና ሸዋዌውን ያስተሳሰራቸው የአንድነት ገመድ ኢትዮጵያዊነት እንጂ እንደ ጽንፍ የዘውግ ፓለቲካ አራጋቢዎች፣የአማራ ማንነትን ምሽግ አድርጎ፣ ሌሎች የዘውግ ማኅበረሰቦችን ሲጨቁን የኖረ ሕዝብ አይደለም::አጼ ቴዎድሮስ ሸዋን እና ጎጃምን ለማስገበር ብዙ ጥፋት አድርሰዋል::ይህ ግን ለሀገር አንድነት ሲባል የተከፈለ መስዋዕትነት እንጂ በዘውግ ማንነት ላይ የተንጠላጠለ አልነበረም::

ኦነግ እንደ የደደቢቱ በረሃ ፋሽስታዊ ኃይል ከላይ የተነሳውን የተንሸዋረረ የታሪክ አረዳድን ተጣብቆ ለግምሽ ክፍለዘመን ያህል ያለ ውጤት ሲባክን ኖሯል:: በኢትዮጵያ ታሪክ ፊት የሀገራችንን የዘውግ ማኅበረሰቦች ለመጨቆን የተሰባሰበ፣ ዘርን መሠረት ያደረገ የፓለቲካ አደረጃጀት ካለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት በስተቀር ኖሮ አያውቅም ቢባል እውነታውን ማበል አይሆንም:: ለአብነት ያህል የጅማው አባጅፋር በባሪያ ፍንገላ እና በጨቋኝንነታቸው ወደር የሌላቸው የአካባቢ ንጉሥ ነበሩ::የአባ ጅፋር ጭቆና ዋናው መሠረቱ የመደብ ልዩነት ነበር::ጨቋኙም ኦሮሞ፣ተጨቋኙም ኦሮሞ ነበር :: ይህን ዓይነት የጨቋኝ-ተጨቋኝ ጥምረት በሁሉም የሀገራችን ጥግ ሲተገበር የኖረ ታሪካዊ ክስተት ነው::ለዚህም ነው ኦዲፒ/ኦሕዴድ/ ሕወሓት የፓለቲካ ንግድ ሲቀምርበት የነበረውን የብሔር ጭቆናን ተረክ በአፍጢሙ ተክሎ የመደብ ጭቆና የሚለውን ትንታኔን በአዲስ መልክ የተቀበለው::

እንግዲህ ኦነግ ሰፊውን የኦሮሞ ሕዝብ በታሪክ ፊት የከፈለውን መስዋዕትነት በመካድ ፣የተጨቋኝነት ካባ አልብሶ፣ በአሸዋ ላይ የተቀለሰውን የትግል መርህን አንግቦ፣ ምንም እርባና የሌለው ፓለቲካዊ እርምጃን ሳያስመዘግብ ካለንበት ዘመን ሊደርስ ችሏል::

## ያልተቀደሰ ጋብቻ

በጠባብ ካምፕ ተሰባስቦ ጽንፈኛ ዘውገኝነትን ሲሰብክ የኖረው ኦነግ የራሱ አጀንዳ እንደ ጋንግሪን እየበላው ከሞት አፋፍ ላይ አድርሶታል::በዚህም ጽንፈኝነቱ የተነሳ ብዙ ዋጋ ተከፍሎ በደም እና አጥንት የጸናችውን ሀገራችንን ለዐይን መጠየፍ ሙያ ብሎ ከያዘ ሰንብቷል::ሀገራዊ አርበኝነትን የሚገመግመበት ፓለቲካዊ ማእቀፍ ከሕወሓት ጋር ከአንድ ወንዝ የሚቀዳው ነው ::ሁለቱ ድርጅቶች በመርህም ሆነ በፓለቲካዊ ግብ ሲመዘኑ በአንድ ማሕጸን ነው የተኙት::ኦነግ በትግል ሂደት ውስጥ ያጋጠመውን ፈተና ወደፊት በሚያልማት ተምኔታዊ ምድር ራሱን ሲሸነግል ኖሯል::ይህንን የቁም ቅዥት እያመነዠገ በቀላሉ ከማይወጣበት ቅርቃር ውስጥ ገብቷል ::የታላቋን ኦሮሚያን ሀገር የመፈጠር ሕልምን እንደ ጣኦት እያመለከ ከእወነተኛው ነበራዊ ሁኔታ ጋር ሆድ እና ጀርባ ሆኖ ቆይቷል:: አየሁዶች የሰሩትን የወርቅ ጥጃ በራሳቸው እጅ እንደተበጃጀ ዘንግተውት እግሩ ስር ተደፍተው እንደመለኮታዊ ኃይል ያመልኩት ነበር::ይህ ዓይነት ተላላ አምክንዮ በኦነጋዊያን ዘንድ ሥር የሰደደ ነው::እንደ ጣኦት በሚያመልከው፣ራሱ በቀረጸው የመገንጠል አጀንዳ እንደባከነ ግማሽ ክፍለዘመን እንደዋዛ አከተመ::

ኦነግ እና ሕወሓት የጋራ ጠላታችን ብለው በፈረጁት አማራ ላይ ግንባር ፈጥረው የጭካኔ በትራቸውን አሳርፈዋል::ሁለቱም ጽንፈኛ የዘውግ ድርጅቶች ይህኑን የፈረደበትን ሕዝብ የሚያገል፣የሚያዳክም እና አንገት የሚያስደፋ ሥርዓት፣የሽግግር ቻርተርን ከማርቀቅ ጀምሮ ባልተቀደሰ ጋብቻ አብረው ጥቂት ማዝገም ችለው ነበር::የጥፋት ቃልኪዳናቸው ግን ብዙም ሳያረፋፍድ ተጣድፎ ነፋስ ገባው::የጫጉላ ዘመኑ አብቅቶ ሰዶ ማሳደድ ውስጥ ተገባ::ኦነግ ከሚወክለው ሰፊ ማኅበረሰብ ጋር አብሮ የማይሄድ መናኛ አጀንዳ ላይ የሙጥኝ በማለቱ የተነሳ ፣በሕዳጣኑ ሕወሓት አይቀጡ ቅጣት ተቀጣ::በዚህም የተነሳ ላለፉት 27 ዓመታት የኦሮሞ እና ቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ በድቅድቅ ጽልመት ውስጥ የዋጀበት ሥርዓት እንዲጸና አስተዋጾ አድርጓል::እንደ ቲም ለማ በሀገራዊ አርበኝነት ላይ የተቀለሰ የትግል መርህን ተከትሎ ቢሆን ኖሮ የሕወሓት የጭቆና አገዛዝ ይህን ሁሉ ዓመት ባልተሚዘዘ ነበር::

## ቄሮ እና ኦነግ

ቄሮ ከጥቂት ዓመታት ቀድም ብሎ በተለኮሰው የትግል ስልት ላይ ጎልቶ የወጣ የአልበገርባይነት እና የእምቢተኝነት መንፈስ የተላበሰን የተጋድሎ መጠሪያ ነው::ቄሮዎች በኦሮሚያ ክልል ሕዝባዊ ንቅናቄን በማቀጣጠል ለተገኘው ነጻነት ትልቅ ገድልን ፈጽመዋል:: ቄሮ በአፍላ እንቅስቃሴው ላይ እያለ ታዋቂው አክቲቪስት ጀዋር መሀመድ እንኳን ለጉዳዩ እንግዳ እንደነበር በፌስቡክ አካውንቱ ለመግለጽ ተገዶ ነበር::ኋላ ላይ ትግሉ እያሸተ፣ እየዋለ ሲያድር ግን ጀዋር የመሪነቱን ሚና ለመንጠቅ ችሏል::የቄሮ አጠቃላይ አደረጃጀት ዝርግ ወይም አሞርፈስ ►

በመሆኑ ለሕወሓት መራሹ መንግሥት በቀላሉ አልጨበጥ አልያዝ ብሎ ነበር::ኦነግ በአርባ ዓመቱ የተሳነው ድል ቄሮ በሁለት ዓመታት ውስጥ አሳካው::በዚህ የትግል ሂደት ውስጥ ኦነግ ጠቀመ ቢባል አርማው ብቻ ነው::ከቄሮ ጋር የተባበረ የትግል ታሪክ የነበረው ከኦነግ ይልቅ የአማራ ሕዝብ ነው::ድሉ የሁለቱ ታላላቅ ሕዝቦች አስተጻምሮ/synthesis/ ውጤት ነው::በዚህ ጊዜ የኦነግ አመራሮች በአስመራ ሆቴሎች ሜሎቲ የተባለውን የኤርትራ ቢራ ከመላፍ የዘለለ ፋይዳ አልነበራቸውም::

የወልቃይት የማንነት አስመላሽ ኮሚቴ ሊቀመንበር ኮለኔል ደመቀ ዘውዱ የተኮሳት ጥይት ፋሺስታዊውን ኃይል በተዳፋት ላይ የሚያደርገውን ክልቢያ ያፋጠነች ነበር::በዚህም የተነሳ የቄሮን የትግል ስልት የሚያቃና ሌላ ተገዳዳሪ ኃይል ከአማራ ወገን ብቅ አለ:: በሁለቱ ክልሎች የነበረው ሕዝባዊ ንቅናቄን የሚያግዝ፣የትጥቅ ትግል ነበር ብሎ በድፍረት የሚያስነገር እውነታ መታዘብ አልቻልንም:: ሁለቱ ሕዝቦች "ጣና ኬኛ" እና "የኦሮሞ ደም ደሜ ነው" የሚሉ የትስስር መፈክሮችን ደጀን አድርገው ፈር የቀደዱት ስልት፣ ኋላ ላይ ፍሬ አፍርቶ የሀገሪቱን የፓለቲካ አቅጣጫ ሦስት መቶ ስልሳ ዲግሪ የቀየረውን የቲም ለማ እና የቲም ገዱ ጉድኝትን ሊወልድ ችሏል::

ኦነግ የኦሮሞን ሕዝብ ሕወሓትን በመሰለ፣በቁስ ሰቀቀን ከእግር እስከራሱ በተጠመቀ አውዳሚ የፓለቲካ ኃይል፣ለሁለት ዐሥርተ ዓመታት በምድር ላይ አሉ የሚባሉትን መከራዎች እንዲቀበል ፈርዶበታል ቢባል ማጋነን አይሆንም:: የኦሮሞ ሕዝብ ያን ሁሉ መከራ ሲቀበል ለዜና የሚበቃ እንኳን የሽምቅ ጥቃት ግንባሩ ሰንዝሮ አያውቅም::ሌላው ይቅር እና የኦጋዴን ነጻ አውጪ ግንባር ያህልን መውተርተር አልቻለም::ቄሮ በባዶ እጁ ያስመዘገበውን ድል ታጠቋል የተባለው ኦነግ ረብ ያለው ገድልን አልፈጸመም::

የዚህን ድርጅት ጠንቀኛነት ለመረዳት በሁሉም የሀገራችን ጥግ ተቀባይነት ያገኘውን የዶ/ር ዐቢይ መንግሥትን ለመውጋት ትግራይ ላይ ከመሸገው የጥፋት ኃይል ጋር ግንባር መፍጠሩን ስንመለከት ነው::እግር ሲቆርጡ እና ሲያኮላሹ ከነበሩት ጣውንቶች ጋር አሁን በሥልጣን ላይ ካለው ማእከላዊ መንግሥት የበለጠ ቀርቧቸው ቢራቸውን በመቀሌ እስከመክፈት ደፍረዋል ::ኦነግ በአነዛ የጨለማ ዘመናት ለኦሮሞ ሕዝብ የፈየደው ነገር አልነበረም:: የኦዴፓ ማእከላዊ ጽ/ቤት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆነው አቶ ታዬ ደንደአ ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ እንዲህ ብሎ መናገሩ የሚታወስ ነው::

"እኔ ኦነግ ነህ ተብዮ ለ10ዓመት ታስሬ ነበር::እንደ ዛሬው ኦነግ ሸኔ በሚባለው 5 ቦታ ሳይከፋፈል በፊት::አሁን በኦነግ ስም የሚንቀሳቀሰው ሸኔ የኦሮሞን አንድነት የከፋፈለ ነው::አሁንም የኦሮሞን አንድነት ለመበተን በስፋት እየሰራ ይገኛል::የሸኔ ኦነግ ትላንት ሕዝባችን መከራ ውስጥ እያለ የት ነበር::ትላንት ለሕዝብ መዋጋት በሚኖርባቸው ጊዜ ተደብቀው ዛሬ ሕዝብ ሰላም በሚያስፈልገው ጊዜ መሳሪያ ይዞ ሰላማዊ ሕዝብ ማሸበር ልክ አይደለም::"

ኦነግ በድሉ ማግሥት የድል አጥቢያ አርበኛ ሆኖ ደርሶ ያዙኝ ልቀቁኝ ለማለቱ ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ አስተዳደር ድርሻውን ይወስዳል::ደርጅቱ ወደ ሀገር ቤት እንዲገባ ከመጣደፍ ይልቅ ቅድመ ሁኔታዎች ላይ በቂ ጊዜ መወሰድ ነበረበት::ይህንን ነጥብ የሚያጠናክርልን ሬኔ ሊፍሮህ ነው::

ታዋቂው ፈረንሳዊው የፓለቲካ ተንታኝ ሬኔ ሊፍሮህ ኦነግ እንዲህ ቅጥአምባሩ በወጣ የፓለቲካ ትግሉ ውስጥ ለመግባቱ የመንግሥት ችኩል ውሳኔ አስተዋጾ እንዳለው ይናገራል::ከኦነግ ጋር የተደረገው የጥድፊያ እና የክልቢያ ስምምነት አሁን እየተከሰተ ላለው ችግር ዋንኛ መንስኤ የዶ/ር ዐቢይ አሕመድ መንግሥት ዳተኝነት እንደሆነ ጸሓፊው አሰርግጦ ያስረዳል::

የኦነግ ሸኔው ሊቀመንበር አቶ ዳውድ ኢብሳ በሀገሪቱ ርዕሰ መዲና ተቀምጠው መንግሥት ላይ ጦርነት ያወጁ የዓለማችን የመጀመሪያው ግለሰብ ሳይሆኑ አይቀርም::በቅርቡ የሚዲያ ሰዎችን ሰብስበው በድፍረት የተናገሩትን ፍሬ ነገር ከተመለከትን ግለሰቡን በጊነስወርልድ መዝገብ ላይ ስማቸውን የሚያሰፍር ተግባር ነው:: እንዴት የአንድ የአማጺ ቡድን መሪ ከመንግሥት አፍንጫ ሥር ተቀምጦ ጦርነት ያውጃል? ይህ ለብዙዎች እንቆቅልሽ የሆነ ጉዳይ ነው:: የዶ/ር ዐቢይ ገደቡን ያለፈ ትዕግስት እና ማባበል፣ ሀገሪቱን ውሎ አድሮ የማትወጣበት አዘቅጥ ውስጥ እንዳይጨምራት የፓለቲካ ታዛቢዎች ሥጋታቸውን ይገልጻሉ::

ኦነግ እንደ አሜባ መከፋፈሉን ቀጥሏል::እስካሁን ወደ አምስት የሚጠጉ የኦነግ ድርጅቶችን ለመታዘብ ችለናል:: የሰሞኑ ባለተራ በገላሳ ዲልቦ የሚመራው ኦነግ ነው::ይህኛው ኦነግ ከዳውድ ኢብሳ ኦነግ ጋር የሚፈጥሩት ጥንቅንቅ ሌላ የፓለቲካ ትዕይንትን ይዞ ብቅ ማለቱ አይቀርም:: ኢትዮጵያን ለዐይን የሚጠየፈው ኦነግ እንዲህ መናኛ ሆኖ መከፋፈሉ፣ ለአንድነት ኃይሎች ትልቅ የምሥራች እንደሚሆን ገለልተኛ ጸሓፍቶች ሐሳባቸውን ያጋራሉ::

የኦነግ ሸኔው ሊቀመንበር አቶ ዳውድ ኢብሳ በሀገሪቱ ርዕሰ መዲና ተቀምጠው መንግሥት ላይ ጦርነት ያወጁ የዓለማችን የመጀመሪያው ግለሰብ ሳይሆኑ አይቀርም

## ጃዋር እና ኦነግ

ጃዋር መሐመድ በቀኑ ውስጥ አራት ጊዜ የፓለቲካ መስመሩን የሚቀያይር፣ በአክቲቪስት ስም የሚንቀሳቀስ ተጽእኖ ፈጣሪ ፓለቲከኛ እንደሆነ ይታወቃል::ጠዋት ከትግራይ ቴሌቪዥን ጋር ቃለመጠይቅ ካደረገ፣ ስለሕወሓት ጀግንነት ያለምንም ሐፍረት ሊደሰኩር ይችላል::ተሲያት ለአማራ ማስሚዲያ ቃሉን ከሰጠ፣ የአማራውን ሕዝብ ልብ ያሞቃል ብሎ የሚያስበውን ተገለባባጭነት ለአውደ ርዕይ ያቀርባል ::በየቅርብ ጊዜ የሰጣቸው ቃለመጠይቆቹ ግለሰቡ ምንያህል በፓለቲካ አክሮባት የተካነ መሆኑን የሚያሳይ ነው ::ጃዋር ከኦነግ ጋር ያለውን የፓለቲካ ዝምድና ይፋ ማድረግ አይፈልግም::በአክቲቪስት ጭምብል ለጊዜው ዓላማውን ማሳካት ነው የመረጠው::

ጃዋር የሚያራምደው አቋም የሕወሓት ግልባጭ ነው::በሀገሪቱ ያለብዙኃን ተሳትፎ በኦነግ፣በሕወሓት እና በሻቢዕያ ፊታውራሪነት የተጠነሰሰውን ቻርተር ተከትሎ፣ ለፍሬ የበቃውን የ1987ሕገመንግሥት እንደ መለኮታዊ ሰነድ ይቆጥረዋል::ይህ ጸረ ኢትዮጵያ ሰነድ እንደ ጃዋር ያለን ብስል ሲሉት ጥሬ ፓለቲከኛ የአደባባይ ሰው ለማድረግ የበቃ ነው::አክቲቪስቱ ዘርን መሠረት ያደረገው ፌዴራሊዝም ባለበት እንዲቀጥል ይፈልጋል:: ከዚህም በተጨማሪ ኦነግን በሌላ ቨርዥን ለማምጣት ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል::ለአብነት የኦነግ አርማ በስፋት እንዲተዋወቅ ትልቁን ድርሻ የተጫወተው ይህው ግለሰብ ነው::ግለሰቡ ከኦነግ በበለጠ በራሱ እንደ የጎሳ ድርጅት የሚቆጠር ነው::

ሕወሓት የደም ካሳ እያለ ሃያ ሰባት ዓመት ሙሉ የባርነት ቀምበርን የጫነብንን አካሄድ እንደ ጀዋር አይነት ግለሰብ ወደ ሥልጣን ቢመጣ  ኮፒ ከማድረግ ወደኋላ እንደማይል ናሙና የሚሆነን በተለያየ ጊዜ የሚያደርጋቸው አወዘጋቢ ንግግሮቹ ናቸው::ለውጡ በእርሱ ፊታውራሪነት እንደመጣ በማስመሰል ሲታበይ አስተውለናል:: በትግል ሂደት ውስጥ የእርሱ አስተዋጾ እንደነበር ቢታመንም ፋሺስታዊውን ኃይል ከቤተመንግሥት ያባረረው ግን የአዴፓ እና የኦዴፓ ታሪካዊ ጥምረት እንደነበረ ከማንም የተሰወረ ሐቅ አይደለም:: ይህ ጥምረት በተገቢው መንገድ ባይሄድ ኖሮ በጎዳና ላይ ነውጥ ብቻ የድሉ ባለቤት የሚሆን ኃይል አይኖርም ነበር::እንደ ሶሪያ እና የመን መፍረስ ነበር እጣፍንታችን የሚሆነው::

ጀዋር የራሱን ጡብ አኑሯል::ሌላውም እንዲሁ::ከየትኛውም ኃይል የላቀ አስተዋጾ የለውም::ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአንድ ወቅት ለጃዋር ዓይነት ዲስኩር መልስ የሚመስል በቴሌቬዥን መስኮት ብቅ ብለው ተናግረው ነበር፤ "ከሀገር ቤት ውጪ ሆኖ ትግልን መምራት የሚታሰብ አይደለም::እኛ ነን ከሕዝባችን ጋር መከራን ተቀብለን ታግለን ነፃ የወጣነው::ድሉ የአንድ ወገን አይደለም::የሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፤"ብለዋል::በወህኒ ሲማቅቅ የነበረው፣ዘሩ የተኮላሸው፣እግሩ የተቆረጠው፣በርሀ ወርዶ የታገለው፣በአደባባይ የጥይት ራት የሆነው፣በሀገር ውስጥ በሽምቅ የተዋገው፤ ሁሉም በተገኘው ድል ላይ የራሱን ደርሻ ተወጥቷል::

## ማሰሪያ ነጥብ

ኦነግ ከሁለት ያጣ ጎመን ሆኗል::አንድም አንድነቱ የተጠበቀ ጠንካራ ድርጅት ሆኖ መውጣት አልቻለም::ሁለትም የባተተለትን ሕልም ሳያሳካ መሀል መንገድ ላይ ቀርቷል::ለግማሽ ክፍለዘመን ከፍ ዝቅ ሲልበት የኖረው ትልም እንደጉም በኗል::ድርጅቱ የሰፊውን የኦሮሞ ሕዝብ ልብ የማረከ ፓለቲካዊ ቁመናን መላበስ አልቻለም::አብዛኛው በኦሮሚያ ያለ ወጣት ከድርጅቱ ጋር ያለው ተዛምዶ የተፈጠረው በሕወሓት አገዛዝ ዘመን ከሚደርስበት ግፍ የተነሳ ነው ::ጊዜ በሄደ ቁጥር እንደ ኦነግ ያሉ ቆመ ቀር ድርጅቶች በርዕዮተዓለም በተሰባሰቡ የፓለቲካ ኃይሎች ተሸናፊ በመሆን እርቃናቸውን መቅረታቸው አይቀርም::

"ኢትዮጵያ ትቅደም"



“ጥፋተኛ ነህ ብለው ክስ አልመሰረቱብኝም ወይም ደግሞ ነጻ ሰው ሆነሃል አላሉም ነገር ግን የራሳቸው ኮማንዶ ሃይል ቤቴ መድበዋል:: ከእስር ውጭ ብሆንም በእነርሱ ቁጥጥር ስር ነበርኩ ማለት ነው:: ከአራት ወር በኋላ በወቅቱ ከነበረው ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ማዕረግዎ ተነስቶ ከሰራዊቱ እንዲባረሩ ተወስኗል የሚል ደብዳቤ ደረሰኝ ፤ወታደራዊ ፍርድ ቤትም ሳልቀርብ ነው እንደወጣ የተወሰነው:: አንድ ጄነራል ማዕረጉ ሲገፈፍ የራሱ አሰራር አሉት:: ልዩ ፍርድ ቤት ቀርቦ ነው ማዕረጉ መገፈፍ ያለበት::”

***ሜ/ጄነራል ዓለምሸት ደግፌ***

***ጉለሌ ፖስት መጽሔት ታህሳስ 2011 ዓ.ም***



“በሰላማዊ መንገድ እንታገላለን ከተባለ፣ የኦነግ ሰራዊት የሚባል አይኖርም:: የሁለት የሶስት ወገኖች ሰራዊት እያለ፣ በአንድ ሀገር ውስጥ ሰላም ማስፈን አይቻልም፤ የመንግሥት ሰራዊት ብቻ ነው መኖር ያለበት፤ በሀገሪቱ ሕገ መንግሥት የሚመራ ሰራዊት ነው የሚኖረው:: ከዚህ ውጪ፣ አሁን በሀገራችን እየተከሰተ ነው ተብሎ የሚሰማው፣ “ትጥቅ አልፈታም፣ ወይንም ትፈታለህ” አይነት ነገር ትክክል አይደለም፤”

***ሻለቃ ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ***

***ኢትዮጲስ ጋዜጣ ታህሳስ 21 ቀን 2011 ዓ.ም***



“ምናልባት አፄ ምኒልክ ወደ ኦሮሞ ግዛትና ወደ ደቡብ ባዘምና የማዕከላዊ መንግሥትን ግዛት ባያጠናክሩ ኖሮ ዛሬ ያለችው ኢትዮጵያ በተለያዩ ግዛቶች የተከፋፈለች ልትሆን እንደምትችል አያጠያይቅም:: ስለዚህ አፄ ምኒልክ ግዛታቸውን ለማስፋፋት የወሰዱት እርምጃ ተደርጎ ሳይሆን መታየት ያለበት በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ላይ የምትተዳር ጠንካራ ኢትዮጵያን ከመፍጠር አንፃር ተደርጎ ቢታይ ጥሩ ነው”

***ፕ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ***

***አዲስ ጊዜ መጽሔት ታህሳስ 2011 ዓ.ም***



“ላሊበላን ያነፁት ሰዎች ከልባቸው ቢያንፁትም እኛ ግን ከልቦናችን የመነጎብኘት እንኳን ፍላጎት የለንም:: ለአንድ የሀገር ውስጥ እግር ኳስ ተጨዋች በወር እስከ 250 ሺህ ብር ይከፈለዋል፤ ምን ስላደረገ? በሶማሌ የሚሸነፍ የእግር ኳስ ቡድን ይዘን፣ ለአፍሪቃ ዋንጫ ለማለፍ ከ30 ዓመት በላይ እየፈጀብን፣ የእግር ኳስ ተጫዎቾቻችን ፀጉራቸውን እንደ ባላቶሊ ወይም ቤካም ሲቆረጡ ታያቸዋለህ:: ቤካምና ባላቶሎ እግር ኳስን ከልባቸው ከተጫወቱና ከታወቁ በኋላ ነው ስለ ፀጉራቸው መጨነቅ የጀመሩት:: የኛዎቹ ተጫዎቾች ግን ኳሱን ከልባቸው ሳይጫወቱ ለፀጉር ቁርጡ ይጣደፋሉ::”

***ዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ***

***በኩር ጋዜጣ ታህሳስ 15 ቀን 2011 ዓ.ም***



“በሀገሪቷ በሙሉ በፍትሕ ሥርዓቱ ላይ የሕዝብ አመኔታ መመለስ አለበት:: ምክንያቱም በዳኝነት ሥርዓት ላይ የሕዝብ አመኔታ ካልተመለሰ የሕዝብ አመኔታ በመንግሥት ላይ አይኖርም:: ስለዚህ ዋነኛና ትልቅ ሥራችን ነው::”

***ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት***

***አዲስ ልሳን ጋዜጣ ታህሳስ 23 ቀን 2011 ዓ.ም***

## ትንግርት

### ትንቢት ተናጋሪዋ ዐይነስውር



ባንባ ቫንጋ ትባላለች:: ትውልዷ ከወደ ቡልጋሪያ ነው:: ትንቢት ተናጋሪዋ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየችው በ86 ዓመቷ በ1996 ነበር::ቫንታ የተናገረችው መሬት ጠብ እንደማይል ብዙ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል:: ከዚህ ቀደም በመስከረም 11 በአሜሪካን ላይ የደረሰውን የሽብር ጥቃት፣ የጽንፈኛው አይሲስን መነሳት፣ የኢንዶኔዢያውን የሱናሜ አደጋን እንዲሁም በ2009 ዓ.ም የሰመጠችውን የራሽያ ሰርጓጅ መርከብን በትክክል ተንብያለች::

ከዚህ በተጨማሪ 45ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጥቁር እንደሚሆን ዝንፍ በማይለው የትንቢት ተሰጥኦዋ ተናግራ ነበር::

ቫንጋ የ2019 ዓ.ም ምን ዓይነት የፖለቲካ ትዕይንቶችን ተንብያለች:: ከትንቢቶቹ መካከል ቭላድሚር ፑቲን ላይ የግድያ ሙከራ እንደሚደረግ እና ከመከራው ለጥቂት እንደሚያመልጡ፣ በኢንዶኒዢያ በሚነሳው ማዕበል ብዙ ንፁሃን ነፍስ እንደሚቀጠፍ እና የትራምፕ የጤንነት ሁኔታ አደጋ ደረጃ ላይ እንደሚደርስ ተንብያለች::

| መንግሥቱ [illegible] (19[illegible] ዓ.ም - 19[illegible] ዓ.ም) | | |
|---|---|---|
| በሰው እንደሚያዩት ጠባይና የሕይወት አቋም | ኢ ልብወለድ | 1949 ዓ.ም |
| ብታምንም ባታምንም | ኢ ልብወለድ | 1956 ዓ.ም |
| [illegible] | ልብወለድ | 1959 ዓ.ም |
| ሶማሌው | ልብወለድ | 1957 ዓ.ም |
| [illegible] | ልብወለድ | 1952 ዓ.ም |
| [illegible] | ልብወለድ | 1959 ዓ.ም |

## ዘር

አባቴ፣
መልካም ዘርን ይዞ
ለም መሬት ፍለጋ፣
በዘመኑ ተጋ::
በኋላ
“አገኘሁ” አለና፣ ልጆቹ ላይ ዘራ
“ተመስገን” በማለት፣
እግዚአብሔርን ጠራ::
ግና የዘራው ዘር
ታንቆ መነመነ::
ለም መሬትን ትቶ
ጭንጫን ስላገኘ::
ለካ!
መልካም ዘር በሙሉ
ዕርሻውን አይመርጥም
“የት ነው የምትዘራኝ?”
ብሎ አይጠየቅም::

*አርነት የወጡ ሀሳቦች*
*በዳዊት ፀጋዬ*

## ስጠቅላላ እውቀት

አንዲት እናት ገና ለተወለደው

ልጇ ፍቅራዊ እንክብካቤ እንድታደርግ የሚያነሳሳት ምንድን ነው? ፕሮፌሰር ጀኔት ክሬንሾ ዘ ጆርናል ኦቭ ፐሪኔታል ኤጁኬሽን በተባለው መጽሔት ላይ እንደገለፁት ኦክሲቶሲን የተባለው ሆርሞን በከፍተኛ መጠን መመንጨቱ “አንዲት እናት አራስ ልጇን በምትደባብስበት፣ ትኩር ብላ በምትመለከትበትና ጡት በምታጠባበት ወቅት፣ የእናትነት ስሜት በውስጧ እንዲቀሰቀስ ያደርጋል::” ከወሊድ በኋላ የሚመነጭ ሌላ ሆርሞን ደግሞ “እናቲቱ ለልጇ ፈጣን ምላሽ እንድትሰጥ” እንዲሁም ከልጇ ጋር ይበልጥ መግባባት እንድትችል ይረዳታል::

## አባባል

- አእምሮ እንደ ማግኔት ነው፤ መባረክን ስናስብ መባረክን እንስባለን፤ ችግርን ስናስብ ችግርን እንስባለን፤ ስለዚህ አዎንታዊ ሐሳቦችን በመኮትኮት ቀናዒ ስብዕናን እንላበስ::
- የስኬት ትልቁ ምስጢር ለራስ ክብር መስጠት ነው፤ በቅድሚያ እንደምንሠራው ማመን ፤ በመቀጠል እንደሚገባን ማመን ፤ በመጨረሻም እንደምናገኘው

# የቅንጅት ትንሳኤ በኢትዮጵያ?


*በሀገራችን የምርጫ ታሪክ ውስጥ የሕዝብን ድምፅ በመቀማትና በመስረቅ የሚታወቀው የሕወሓት ሥርዓት፣ ምርጫን አስታኮ በኢትዮጵያውያን የተመረጠ መንግሥት አድርጎ ራሱን ለመግለፅ ከሞከረባቸው ዓመታት ሁሉ፣ እንደ ምርጫ 97 በገሀድ ውርደትን የተከናነበበት ወቅት የለም ማለት ይቻላል፡፡*

*ጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ በአበልና በግዴታ አደባባይ እንዲወጡ ያደረጓቸውን ደጋፊዎቻቸውንና የመንግሥት ሠራተኞችን ተመልክተው "ይሄ የሕዝብ ማዕበል፣ ኢሕአዴግ ምርጫውን እንደሚያሸንፍ ያረጋግጣል" ብለው በተናገሩ ማግስት፣ የድጋፍ ሰልፍ የጠራው "ቅንጅት" ፣የአዲስ አበባ ሕዝብ ቤቱን ቆልፎ እንዲወጣ፣ የመለስ ማዕበልም "ትንሽዬ ጅረት" እንደሆነች ያረጋገጠበት ታሪካዊ ክስተትና የምርጫ ውጤት፤ ቅንጅቱ በኢሕአዴግ ላይ የበላይነትን እንዲጎናፀፍ ቢያደርገውም፣ አምባገነኑ ሥርዓት ሽንፈቱን አምኖ ከመቀበል ይልቅ በሐሳብና በአማራጭ ልዩነት፣ በሕዝብ ድምፅ የረቱትን ግለሰቦች "ሕገ መንግሥቱን በኃይል ለመናድ ሞክረዋል" በሚል ሀሰተኛ ክስ ወህኒ ወርውሯቸዋል፡፡*

*በፈጠጠና ግልፅ በሆነ አስነዋሪ መንገድ በሚሊዮን የሚቆጠር የሕዝብ ድምፅ የነጠቀው ሕወሓት መራሹ መንግሥት፣ ልዩ ጥምረትና ተቀባይነት ያገኙትን የቅንጅት አባላትን፣ በተለያዩ መንገዶች በመበታተን (ከውስጥ የተመለመሉ አድርባዮችና ከሃዲዎችን ጨምሮ) በሰላማዊ ትግል አዲስ ታሪክ ያስመዘገበው ፓርቲ እንዲጠፋ፣ እንዲከስምና በስሙም ተለጣፊው ድርጅት እንዲቀጥል በማድረግ ታሪክ የማይረሳው ወንጀል ፈፅሟል፡፡*

*እነሆ ከአስራ ሁለትና አስራ ሶስት ዓመታት በኋላ ሥርዓቱን በተለያዩ መንገድ ሲታገሉና በዓላማቸው ፀንተው ለፍትህና ለዴሞክራሲ ሲሰሩ የነበሩ አራት ፓርቲዎች፤ ማለትም አርበኞች ግንቦት ሰባት፣ ሰማያዊ፣ ኢዴፓና የቀድሞው የአንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ አመራር አካላት ቀጣዩን ምርጫ አንድ ሆነው በመዋሃድ ለመስራት ከቅድመ ስምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡ ይህንና አብዛኞቹ የቀድሞው የቅንጅት አባላት፣ በጊዜ ሂደትም ሰፊ ልምድ ያካበቱ የፖለቲካ ሰዎች መሆናቸውን ተከትሎ፣ ተለያይቶ ከመሥራት ወደ ውህደት እያመራ ያለው አዲሱ ፓርቲ የቅንጅትን ትንሳኤ በኢትዮጵያ ያበሰረ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብም ልዩ አማራጭ ሆኖ የቀረበ፣ ጠንካራ ድርጅት እንደሚሆን በብዙዎች እየተነገረለት ይገኛል፡፡*

*ከዚህ በመነሳት የአርበኞች ግንቦት ሰባት አመራር አቶ ቸኮል ጌታነህ፣ የሰማያዊ ሊ/መንበር አቶ የሺዋስ አሰፋ፣ የኢዴፓ ሊ/መንበር ዶ/ር ጫኔ ከበደ፣ የቀድሞው የአንድነት ሊ/መንበር አቶ አንዷለም አራጌን የግዮን ጋዜጠኛ ሮቤል ምትኩ በውህደት ስምምነቱ ሂደትና በቀጣይ ዕቅዶቻቸው ዙሪያ አነጋግሯቸዋል ፡፡ መልካም ቆይታ፡፡*



## "የተገመደ ተስፋና የጋራ ሀገር ስላለን መከፋፈሉ አይጠቅመንም"

### አቶ አንዷለም አራጌ

**ግዮን፡- በቅርቡ አራት የፖለቲካ ፓርቲዎች ውህደት አድርጋችኋል፣ ወይም ወደ አንድነት ስምምነት መጥታችኋል፡፡ በጋራ አብሮ ለመስራት መነሻ ምክንያታችሁ ምንድን ነው?**

**አንዷለም፡-** ከአርበኞች ግንቦት ሰባት፣ ሰማያዊ ፓርቲና ኢዴፓ ጋር በመሆን ነው አራት ፓርቲዎችን ለመዋሃድ የወሰንነው፡፡ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት፣ የኢትዮጵያን ፖለቲካ ተነጣጥለህ መግፋት ስለማትችልና ተነጣጥሎ ለመቀጠልም በቂ ምክንያት የሌለን በመሆኑ፡፡ ፕሮግራማችን፣ የፖለቲካ እምነታችንና ህልማችን ተመሳሳይ ስለሆነ ተለያይተን የምንቆምበት ምክንያት የለምና በአንድ ላይ መሰባሰብ እንዳለብን፤ ፖለቲካውን ከማዘመን አንፃር፣ ይሄ ነገር የሕዝብም ፍላጎት በመሆኑና ከብዙ ነገሮች አንፃር እንድ ላይ መቆምን እናምን ነበር፡፡ በተጨማሪም ከዚህ በፊት የምንተዋወቅ ሰዎች ስለሆንን ፣ አብረን መስራት እንችላለን በሚል ከውህደት ስምምነት ላይ ደርሰናል፡፡

**ግዮን፡- አንተን ጨምሮ ሌሎች ግለሰቦች "የቀድሞ የአንድነት አባላት" በሚል ስያሜ ነው የተዋሃዳችሁት፡፡ ከስምንት ዓመት በፊት አንተ የድርጅቱ ሊ/መንበር እያለህ ነበር ለእስር የተዳረግከው፣ ለመሆኑ በዚህ ውህደት ውስጥ ምን ያህል የቀድሞ የአንድነት አባላት ተካተዋል?**

**አንዷለም፡-** በቁጥር ደረጃ ይሄን ያህል ለማለት አሁን እቸገራለሁ፡፡ የቀድሞ የአንድነት አባላት ብቻ ሳይሆኑ፣ እስር ቤት ውስጥ የነበሩና በዜግነት ፖለቲካ ላይ የምናምን ሰዎች (ከአንድነት ውጪ የነበሩ ማለቴ ነው) የተሳተፉበት ውህደት ነው፡፡በተጨማሪም በአዲስ አበባ ደረጃና በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ በርካታ የቀድሞ የአንድነት አባላት በዚህ ውህደት ውስጥ ይገኙበታል፡፡

**ግዮን፡- ይህ ውህደት ባይፈጠር እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ አልነበርክምና ሰላማዊ ትግሉን በምን መንገድ ትገፋበት ነበር?**

**አንዷለም፡-** እኔ ከእስር ከተፈታሁ ጀምሮ እየሰራሁ ያለሁት በዚህ ጉዳይ ላይ ነው፤ ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ስለማውቅ፡፡ የግል ፓርቲ ማለት በግል አኩርፈህ የምትቀመጥበት ቤት ሳይሆን፣ በትክክል የምታምንበትን ለሀገርህ የምትሰራበት ቤት ነውና መንገዱ ረዥምና አድካሚ ቢሆንም፣ ግን ደግሞ ትክክለኛ መንገድ ስለሆነ በዚህ ዙሪያ ነው ስሰራ የነበረው፡፡

አሁን የተፈጠረው ስብስብ ውስጥ ያሉ ▶

ሰዎች ጥሩ ስራ ሊሰሩ እንደሚችሉ አምናለሁ፣ ሰላማዊ ትግል በተናጠል የምታደርገው ነገር አይደለም፤ በቡድን ስትሰባሰብ ነው ውጤታማ የሚሆነው:: ከዛ አንፃር መርጬ ስታገልለት የነበረ መንገድ ነው:: አሁን ቢያንስ ሰላማዊ ትግል ለማድረግ ኢትዮጵያ አቅም አላት ብዬ አምናለሁ፣ ይሄንን ሐሳብ የሚያሳካ ስብስብም ተፈጥሯል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ:: ከሰላማዊ ትግል ውጪ አማራጭ ኖሮኝ አያውቅም:: ይሄን አማራጭ ወደ ፊት የሚያስኬደው ደግሞ ይሄ መንገድ ነው ብዬ አምናለሁ፣ ስለዚህ ሁለቱ ነገሮች አንድ ላይ ሰምረውልኛል ብዬ አስባለሁ::

**ግዮን፡- የአራቱን ፓርቲዎች ውህደት አስመልክቶ ከወዲሁ የቅንጅት የቀድሞ መንፈስ ይታይበታል እየተባለ ነው:: በዚህ ላይ ምን ትላለህ? በበፊቱ ቅንጅት ውስጥ ብዙዎቻችሁ ነበራችሁና::**

**አንዷለም፡-** ቅንጅት እንደምታውቀው፣ ስሙም እንደሚገልፀው በዋናነት የነበረውና ብዙ ታሪኩ የሚታወቀው በቅንጅት ደረጃ ነው:: ወደ ውህደት ከመጣን በኋላ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነው የታሰርነው:: ስለዚህ ውህደት የፈጠረው ቅንጅት ህልውናው በአገዛዙ ፈርጣማ መዳፎች እንዲመክን ተደርጓል:: አሁን ያለው አደረጃጀታችን ግን ልዩ ነው::

**ግዮን፡- የአሁኑ ከቅንጅት የሚለየው በምን ነው?**

**አንዷለም፡-** በፊት ከላይ ከአመራር ይጀምርና ወደ ታች አባላት የሚወርድ አሰራር ነበር በቅንጅት ዘመን:: አሁን ግን አባላትን እያዋሀድን ፣የአባላት ሉአላዊ የስልጣን ባለቤትነት ከተረጋገጠ በኋላ፣ ሁላችንም ወደ ወረዳችን ወርደን፣ በወረዳችን መመረጥ ከቻልን ብቻ ነው ወደ ላይ የምንወጣው:: በፊት እንዲህ ዓይነት አሰራር አልነበረም:: ይሄ ለየት ያደርገዋል::

**ሁለተኛ፡-** በመከራም ቢሆን ወደ አስራ ሁለትና አስራ ሶስት ዓመታት ከቅንጅት በኋላ አልፈዋል:: ስለዚህ ሳንካ መፍጠር፣ አለመተባበር ወይንም አንድ የሚተባበረን ኃይል ለማፍረስ መሞከር ምን ያህል ጉዳት እንዳለው የተማርንባቸው ዓመታት ናቸው:: ሁላችንም ወሳኝ ትምህርቶችን ወስደናል:: ከቅንጅት የተሻለና፣ ከቅንጅትም የተማረ፣ ሰላማዊ ትግሉን በተሻለ ሁኔታ ወደ ፊት የሚገፋ ፓርቲ እንመሰርታለን ብዬ ነው የማምነው::

**ሦስተኛ፡-** አገዛዙ ወይም ሥልጣን ላይ ያለው አካል የተማረው ነገር አለ፣ አገዛዙ ከዚህ በፊት ፓርቲዎችን በማፈን ስብስቦችን በማፍረስ፣ ደህንነቱን ሁነኛ መሳሪያ አድርጎ የሕዝብን የሥልጣን ባለቤትነት ለማፈን ብዙ ጥረት አድርጎ ነበር:: ያ እንደውም በተቃራኒው የአገዛዙን ግብዓተ መሬት ያፋጠነበት ሁኔታ ስላለ፣ አሁን ያሉ መሪዎች ከዛ የተማሩ፣ በትክክል ለዴሞክራሲ እውን መሆንና ለፓርቲዎችም በነጻነት የመታገል ዕድል ለመስጠት ፍላጎት ያላቸው ይመስለኛል::

አራተኛ፡ ሕዝብም ከዚህ በመነሳት ተገቢውን ትምህርት የወሰደበት ሁኔታ አለ:: በመጨረሻም ለአገዛዙ መሳሪያ ሆነው ያገለግሉ የነበሩ ግለሰቦች፣ ግልፅ በሆነ ሁኔታ ከፓርቲ እየተፈረከሱና እየተነጠሉ የነበሩ ስብስቦች፣ ለግል ጥቅም ተብሎ የሕዝብን ፍላጎት ማዳፈን እንደማይቻል፣ እንዲሁም የእነዛ መጨረሻው ውርደትና በሕዝብ መገፋት እንደሆነ ጥሩ ትምህርት የወሰዱበት ይመስለኛል::እነዚህና ሌሎች ትምህርቶች የተሻለ ነገር እንዲፈጠር እድል ይሰጡናል ብዬ አምናለሁ::

**ግዮን፡- አዲሱ ውህደት አመራሮችን መርጦ ወደ ቀጣይ ሥራ ለመግባት በይፋ እንቅስቃሴውን የሚጀምረው መቼ ነው?** የምትከተሉት ርዕዮተ ዓለምስ ምንድን ነው?

**አንዷለም፡-** እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ይሄን ድርጅት በሕዝብ ፊት እናቆመዋለን ብለን እናምናለን:: ዋናው ርዕዮተ ዓለማችን ሊብራል ሆኖ ወደ ሶሻል ዲሞክራሲ ያዘነበለ፣ ማኅበራዊ ፍትህን በስፋት የሚያይና በእዛ ዙሪያ የሚታገል ነው የሚሆነው::

**ግዮን፡- በቀጣይነት ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር ውህደት ታደርጋላችሁ?**

**አንዷለም፡-** እንደምታውቀው ፖለቲከኛ ከሆንክ ሁልጊዜም ትግል ላይ ነህ:: አንዱን አሳክተህ ሌላውን በቀጣይ ለማሳካት ትጥራለህና፤ እኛ አንድ ሆነን ለመደራጀት ቻልን ማለት ሁሉም ፓርቲዎች አንድ ላይ ሆነናል ማለት አይደለም::ወይንም ደግሞ ህልማችን በሙሉ ተሳክቷል ማለትም አይደለም፣ ለጊዜው ግን ለመነሻ ያህል የቻልነውን አድርገናል፤ በዚህ እንቀጥላለን:: ይሄን ሂደት የሚያምኑ ሌሎች ፓርቲዎች ከታች ተቀርፀው፣ የሕዝቡን ሉአላዊነትና ምርጫ ተቀብለው ፣በሕዝብ ድምጽ ወደ ፊት ለመውጣት፣ ሳይፈልጉ ሲቀሩም ወደ ኋላ ለመቅረት ፍቃደኞች የሆኑ፣ በዜግነት ፖለቲካ ላይ የሚያምኑ፣ በማኅበራዊ ፍትሕ ላይ ዕምነት ያላቸው ወንድምና እህቶቻችን ሁሉ አብረውን እንዲታገሉ እንፈልጋለን::

**ግዮን፡- ብሔር ተኮር ፓርቲዎችና የብሔር ፖለቲካ መስፋፋቱንስ እንዴት ታየዋለህ?**

**አንዷለም፡-** የኢትዮጵያ ህዝብ ዘረኛ ነው ብዬ አላምንም:: ዘረኛም ሆኖ አያውቅም፤ ዘረኛም ይሆናል የሚል ዕምነት የለኝም:: ግን በየብሔሩ ደጃፍ ላይ ቆመው አብዝተው የሚጯሁ ጥቂት ሰዎች አሉ:: ያ ጩኸት የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ወይንም የብሔሮች ድምፅ እየመሰለ የተሳሳተ ዕድል እየፈጠረ እንደሆነ አምናለሁ::

እንግዲህ እነዚህ ወንድምና እህቶቻችን በአንድ ወይ በሌላ መንገድ ተገፍተው፣ ወይንም ተከፍተው እንደሚሆን አምናለሁ:: ነገር ግን አሁን ጥሪዬ እነዚህ ወገኖቻችን ወደ ቀና ልቦናቸው እንዲመለሱ፣ የሚለያየን ሆነ የሚከፋፍለንን፣ ለውድቀትና ለደህንነት የሚደርገንን የዘረኝነት መንገድ ትተው፣ ሁላችንም ወንድማማች መሆናችንን፣ የተገመደ ተስፋና የጋራ ሀገር ያለን፣ ልጆቻችን የሚኖሩበት፣ እኛም የምንሞትባትና የምንቀበርባት የጋራ ሀገር አለችንና ከብሄር ፖለቲካ ይልቅ የሐሳብ ፖለቲካ ላይ አተኩረን እንዴት ሀገራችንን ማሳደግ እንችላለን? እንዴት የልጆቻችንን ተስፋ ከፍ ማድረግ እንችላለን? የሚለው ነገር ላይ ትኩረት ቢያደርጉ ጥሩ ነው እላለሁ::

ለኢትዮጵያ ሕዝብ የማስተላልፈው መልዕክት፤ ዛሬ እንደ ቀልድ እያየነው ያለነው የተለኮሰ የዘር እሳት፣ ነገ የዘር ሰደድ ሆኖ እንዳያጠፋን በጊዜው በእንጭጩ ወደ ልቦናቸው እንዲመለሱ እንዲመክራቸው አደራ እላለሁ:: ሰሞኑን የአምቦ ሕዝብ "ትግሉን ያመጣሁት እኔ ነኝ እያላችሁ የተለያየ ነገር ትላላችሁ:: ትግሉን ያመጣው ሕዝብ ነው፣ እኛ ነን፤ ስለዚህ አርፋችሁ ተቀመጡ" የሚል መልዕክት ለአንዳንድ ፓርቲዎች የአምቦ ሕዝብ መስጠቱን ሰምቻለሁ:: ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ መንገድ ነው መንዝ ያለበት::

ህዝብ ሊያጋጩት፣ ሊከፋፍሉትና ወደ አዘቅት ሊከቱት ለሚፈልጉ ፓርቲዎች ደግሞ ደጋግሞ ይሄንን የአምቦ ህዝብ መልዕክት ማስተላለፍ አለበት ብዬ አምናለሁ::

**ግዮን፡- እናመሰግናለን::**

# "ኢዴፓ የግለሰብ ንብረት የመሆኑ ጉዳይ አክትሟል"

## ዶ/ር ጫኔ ከበደ



**ግዮን፡- ኢዴፓ በቅርቡ ከቀድሞ የአንድነትና ለፍትሕና ዴሞክራሲ አመራር አባላት ከሰማያዊ ፓርቲ እንዲሁም ከአርበኞች ግንቦት ሰባት ጋር ውህደት ለመፍጠር ከስምምነት ላይ ደርሷል:: መነሻችሁ ምንድን ነው?**

**ዶ/ር ጫኔ፡-** ኢዴፓ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር አብሮ ሊመሰረት መቋቋሚያ ደንቡ ይፈቅድለታል:: በተለይ ሀገር አቀፍ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችና በዜግነት ፖለቲካ ላይ የሚሰሩ ፓርቲዎች ጋር አብሮ የመስራት ረዥም ልምድ ያለው ነው:: በዚህ መሰረት ከብዙ ፓርቲዎች ጋር ተዋህዶ የመጣ ነው:: ችግር የለበትም:: በምርጫ 97 ወቅትም ቅንጅትን ከመሰረቱት ጠንካራ ፓርቲዎች

መሀል አንዱ እንደሆነ ይታወቃል::

ፓርቲያችን ላለፉት አስራ ዘጠኝ ዓመታት በሰላማዊ መንገድ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል:: አሁን ለውጡን ተከትሎ የመጣውን አጠቃላይ የፖለቲካ ምህዳር መሰረት አድርገን ኢትዮጵያ ምን ዓይነት የፖለቲካ ስትራቴጂ ያስፈልጋታል ፣ኅብረተሰቡን መጥቀም የሚያስችል ምን ዓይነት ፖሊሲና ፕሮግራም መቅረፅ ይቻላል፣ ከሚል ተነስተን በተናጠል ከፖለቲካ ድርጅቶች ጋር እንደዚሁ ስናወራ ቆይተናል::

እንደምታውቀው መጀመሪያ ወደ እንደዚህ ዓይነት ነገር ውስጥ ከመግባትህ በፊት በመሪዎች ደረጃ የውትወታ ሥራ ነው የሚሰራው :: ከዛ ቀጥሎ በሥራ አስፈፃሚ ደረጃ ታስወስናለህ:: በዛ መልኩ ደረጃውን እየጠበቀ ነው የሚሄደው:: በእኔ በኩል ሥራ አስፈፃሚውም አምኖበት እና ም/ቤቱ አምኖበት ነው ወደ ሥራ የተገባው::

ከዛ አንፃር ከውጭ ከገቡት አርበኞች ግንቦት ሰባት በዚህ ጉዳይ ያለውን ፍቀደኝነት ገለፁልን:: የቀድሞ አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ በአቶ አንዷለም አራጌ በኩል የተሰባሰበ ቡድን አለ:: እሱም ፍላጎቱን ገለፀ:: ከዛ በኋላ በጋራ መስራት የሚያስችለንን መንገድ መፍጠር የሚል ሀሳብ ላይ ደረስን:: ትልቁ ስትራቴጂ ከዚህ በኋላ በግንባር በቅንጅት መልክ መታገል አያስፈልግም፤ ከወዲሁ በውህደት አንድ ጠንካራ ፓርቲ በሀገር አቀፍ ደረጃ መመስረት ነው ጠቃሚ የሚሆነው:: ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብለን ስላመንን በዚህ መሰረት የመጀመሪያውን ውይይት አድርገናል::

**ግዮን፡- ቀጣዩስ ምንድን ነው?**

**ዶ/ር ጫኔ፡-** አሁን በተስማማንበት መሰረት የቀሩ ገደብ ወይንም ደግሞ ዕቅዶችን አውጥተን በዛ መሰረት እየተንቀሳቀስን ነው ያለነው:: ፓርቲዎቹ በየራሳቸው፣ የየራሳቸው የሆነ መተዳደሪያ ደንብ ስለነበራቸው፣ ያ መተዳደሪያ ደንብ በሚፈቅድላቸው መሰረት መውሰድ የሚገባቸውን ዕርምጃ እንዲወስዱ ተደርጓል::

በኢዴፓ በኩል አባላትን ታች ወረዳ ድረስ በክልሎች ላይ ያሉትን ወረዳዎች (የወረዳ አባላት) ያንን ማደራጀትና እንደገና ሀሳቡን ማሰራጨት ስለነበረብን በንዑስ ደረጃ ወደ ክልሎች ወርደን ይሄንን ሰርተናል:: በአብዛኛው ያገኘነው ግብረ መልስ ‹‹ቀጥሉ ጥሩ ነው በዚህ መሰረት ነው ወደ ፊት መጓዝ የሚያስችለን የሚል ሀሳብ ይዘን ነው የተመለስነው::

ይሄንን በእኛ በኩል ለጠቅላላ ጉባኤው አስወስነን፣ ጠቅላላ ጉባኤው በሚሰጠን አቅጣጫ መሰረት ውህደቱን መፈፀም የሚያስችል ዕርምጃ ላይ ነው ያለነው::

**ግዮን፡- ብዙዎቻችሁ በቅንጅት ውስጥ አብራችሁ የሰራችሁ ከመሆኑ አኳያ፣ ያለፈው የቅንጅት መንፈስ ተመልሷል ማለት ይቻላል? ልዩነቱስ ምንድን ነው? ያለፈው ስህተት እንዳይፈፀም ያደረጋችሁት ጥንቃቄስ ምን ይመስላል?**

**ዶር ጫኔ፡-** አንተ እንዳልከው የቅንጅት መንፈስ በጣም ጠንካራ መሆኑ ይታወቃል:: በኅብረተሰቡ ዘንድ ትልቅ አክብሮትና አድናቆት የነበረው ድርጅት ነው:: ነገር ግን ቅንጅቱ ቅንጅት እንዲሆን ሲሰራ የስትራቴጂ ወይንም የታክቲክ ችግር ነበረበት:: ያ ፓርቲዎቹ እንዲፈራርሱ ዕድል ከፍቷል:: በተለይ ከላይ ከመሪዎች ጀምሮ መዋሃድ የሚለው ነገር በስልጣን ይገባኛልና በመሳሰሉት ጥቅማ ጥቅሞች የመለያየት ሁኔታ ተከስቶ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያሳዘነ ክስተት ፈጥረን እንደነበር ይታወቃል::

ይሄ ስህተት እንዳይደገምና በኢትዮጵያ ሕዝብ "ሁልጊዜ አመል አለባቸው" ላለመባል፣ በእኛ በኩል የሚደረገው አጠቃላይ ሂደት በጣም ጥንቃቄ በተሞላበት ከታች ከወረዳ ጀምሮ ነው አባሎቻችንን እያዋሃድን የምንመጣው:: በዛን ደረጃ ከክ/ሀገር ደረጃ ካሉን ጽ/ቤቶቻችን ያለን አባላት ሁሉ እየተዋሀደ ነው ወደ ላይ የሚመጣው:: ስለዚህ እዛ ያለው ውህድ በተለይ ወረዳ ላይ በጣም ጠንካራ የሆነ ም/ቤት ለመመስረት ነው የምናስበው፤ መሰረት የምናደርገው የወረዳውን ማህበረሰብ ስለሆነ::

እንዲህ ያለው ጉባኤ ነው ለጠቅላላ ጉባኤው አካል የሚሆን አባል መርጦ የሚልከው፤ በዛ መሰረት የጠቅላላ ጉባኤው ዳግም አዲሱን ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብና ፕሮግራም ያፀድቃል ስሙንም ያፀድቃል:: ከዛ በኋላ ምርጫ ቦርድ በዛ መሰረት መዝግቦ ሌሎች ፓርቲዎች ፍቃዶቻችን መልሰን የውህድ ፓርቲ አካል ሆኖ መፍረስ በማይችልበት ገመድ አስረን ወደፊት የኢትዮጵያን ህዝብ ጥያቄ መመለስ በሚያስችል መንገድ እንሄዳለን ብለን እናስባለን::

ትልቁ መርሃችን ከምንም በላይ ኢትዮጵያዊነት ይበልጣል የሚል ነው:: ከምንም በላይ የዜጎች መብት ይበልጣም ብለን ነው የምናስበው:: ሥልጣን ምናምን የመሳሰሉ ድክመቶችን ወደ ጎን ትተን እኛ ራሳችን እንደ ማንኛውም ህብረተሰብ ከታች ተወዳድረን ነው የምንመጣው:: ጠቅላላ ጉባኤውም ላይ እንደገና ለመመረጥ ጉባኤ አዘጋጅቶ፣ ኮሚቴው በዕጩነት ካቀረብን፣ በዛ መሰረት ለስራ አስፈፃሚነትም ሆነ ለመአራርነት እየተወዳደርን ድምፅ እያገኘን፣ ዲሞክራሲውን በቀጥታ ተግባራዊ እያደረግን፣ አመራሩ በዛ መሰረት የሚፈጥር ይሆናል:: ከነበረው አደረጃጀትም ሙሉ በሙሉ የተለየ ነው የሚሆነው::

አሁን የዜግነት ፖለቲካ ብለን ስንነሳ የክልል ፓርቲዎች ወይም የብሔር ፓርቲዎችን መብት አንጋፋም፤ ነገር ግን የኢትዮጵያ ህዝብ የብሔር ፓርቲዎችም ሆነ የዜግነት ፓርቲዎችን አወዳድሮ በድምፅ ብልጫ በሐሳብ የበላይነት መምረጥና ማሸነፍ እስከቻለ ድረስ እኛ ተቃውሞ የለንም:: እኛ ግን የሐሳብ የበላይነት እንዲኖረን፣ ዜጎች በመላ ሀገሪቱ በሚኖሩበት አካባቢ መብታቸው እንዲከበር ሰርተው አድገው ለምተው ከማንኛውም ህብረተሰብ ጋር እንዲኖሩ የሚያስችል ስትራቴጂ ይዘን ነው የምንጓዘው:: ይሄንን መሰረት አድርገን መስበክና ማስተማር ከቻልን ብዙኃኑን ሕዝብ የፓርቲያችን አባልና ደጋፊ ማድረግ እንችላለን፤ ድምፁም ይሰጠናል ብለን እናምናለን::

**ግዮን፡- "ኢዴፓ ፈርሷል" እያሉ አቶ ልደቱ አያሌው በሚናገሩበት ወቅት እናንተ ደግሞ አልፈረስንም በሚል ወደ ውህደት እያመራችሁ ነው:: እስኪ በዚህ ጉዳይ ጥርት ያለውን ነገር እርስዎ ለህዝብ ያሳውቁልን?**

**ዶ/ር ጫኔ፡-** ፈርሷል የሚለው ግለሰብ ፓርቲውን ከመጀመሪያው የግል ንብረቱ አድርጎ ይዞት ይጓዝ ስለነበረ ነው::ኢዴፓ የግለሰብ ንብረት የመሆኑ ጉዳይ አክትሟል:: በእኛ በኩል ግን ፓርቲው አልፈረሰም፤ ሁለተኛ በውስጥ በነበረው ክፍፍልም ቢሆን በፍርድ ቤት መብታችንን አስከብረን፣ በፍርድ ውሳኔ መሰረት የፓርቲያችን ህጋዊነት በቀጥታ ተረጋግጦልናል::

ከዚህ አንፃር ግለሰቦች በወጡ ቁጥር ምናልባት ሰውየው ከነበረው የፖለቲካ ተሳትፎ አንፃር ፈጣሪ መስሎ ኅብረተሰቡ ይታየው ስለነበረ ፓርቲው በምንም መንገድ ያልፈረሰና የክልል አደረጃጀቶቻችንም እንዳሉ እንደነበሩ ተጠናክረው የቀጠሉበት ሁኔታ ነው ያለው:: አሁንም ቢሆን ያው መስመር ነው እየቀጠለ ያለው:: ኢዴፓ ጠንካራ አስተሳሰብ ያለው ፣በአመራርም ደረጃ ቢሆን ጠንካራ አመራሮች ያሉበት ፓርቲ ነው:: በአሁን ሰዓት ስለዚህ ፓርቲውን አንድ ዕርምጃ ወደ ፊት ይዞ ለመጓዝ የሚያስቸግረን ምንም ዓይነት የአሰራር ችግር ይገጥመናል ብለን አናስብም::

**ግዮን፡- ኢዴፓ ቆየት ያለ ፓርቲ ከመሆኑ አንፃር በቀጣይ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር ስትዋሃዱ የካፒታልና የንብረት ጉዳይ በምን መልክ ነው የሚታየው?**

**ዶ/ር ጫኔ፡-** አንድ ፓርቲ ከሌላው ጋር ተዋሀደ ሲባል በሁሉም ነገር ነው የሚዋሀደው:: የምርጫ ህጉም ውህደት ከሆነ ያ ፓርቲ የነበረው ካፒታል፣ የሰው ኃይል ሃብትን አጠቃሎ እንደ አዲስ የሚቋቋመው የውህዱ ፓርቲ ንብረት ነው የሚሆነው:: በህግ መሰረት ይተላለፋል ማለት ነው::

ስለዚህ ቢሮም ፣ መኪናም ፣ ገንዘብም ካለህ፤ ስትዋሃድ የውህዱ ፓርቲ ንብረት ይሆናል ማለት ነው:: ይሄ ህጉ በሚፈቅደው መንገድ ወይም ምርጫ ቦርድ በራሱ በኩል ለውህድ ፓርቲ መመዝገቡን የሚያረጋግጥበት ሂደት ይኖራል:: ከዚህ አንፃር ሃብትና ሪሶርሳችን በሙሉ የሚያጋጭን ነገር አይሆንም:: አንዱ ብዙ ፅ/ቤት ሊኖረው ይቻላል፤ አንዱ ብዙ ገንዘብ ሊኖረው ይቻላል፤ ሌላው የሰው ሃብትና ደጋፊ አባላት ሊኖሩት ይቻላል:: ነገር ግን ይሄ በውስጥ አሰራራችን የምንፈታው ሆኖ አጠቃላይ ወህደቱን ችግር ሊሆንበት ፈፅሞ አይቻልም::

**ግዮን፡- እናመሰግናለን::**

**ትልቁ መርሃችን ከምንም በላይ ኢትዮጵያዊነት ይበልጣል የሚል ነው : : ከምንም በላይ የዜጎች መብት ይበልጣም ብለን ነው የምናስበው : : ሥልጣን ምናምን የመሳሰሉ ድክመቶችን ወደ ጎን ትተን እኛ ራሳችን እንደ ማንኛውም ህብረተሰብ ከታች ተወዳድረን ነው የምንመጣው**

# “ከቅንጅት መፈራረስ ብዙ ተምረናል”

## አቶ ቸኮል ጌታነህ



**ግዮን፡- አርበኞች ግንቦት ሰባት ከሰማያዊ ኢዴፓ ፓርቲና ከቀድሞ የአንድነት አባላት ጋር ለመወሃድ ከስምምነት ላይ መድረሱ ታውቋል:: ይህ ያስፈለገበት ምክንያት ምንድን ነው?**

**አቶ ቸኮል፡-** አሁን ውህደት ለመፍጠር ነው የተስማማነው እንጂ ሙሉ ለሙሉ አልተዋሃድንም:: በእኛ ሀገር የተለመደው ውህደት ፓርቲዎች እየተቀናጀ የሚፈጥሩት ውህደት አይደለም:: ከዚህ በመነሳት ውህደት የሚለው ቃል ትርጓሜ አወዛጋቢ እንዳይሆን እሰጋለሁ::

ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም ብዙ ፓርቲ ነው ያለው:: ፓርቲዎች በተቻለ መጠን ወደ አንድ የመሰብሰባቸውን አስፈላጊነት በተመለከተ የመግባባት ነገር ተፈጥሯል:: ከዚህ በመነሳት በየትኞቹ ቦታዎች ነው አብረን ልንሰራ የምንችለውን ስናይ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የተለያዩ ጊዜ የተፈጠሩ ድርጅቶች አሉ:: ከእነዛ ውስጥ ሶስቱ ፓርቲዎችና በቀድሞው አንድነት ፓርቲ ውስጥ የነበሩ ሰዎች የተሰበሰቡት ቡድን አለ::

በእነዚህ ሰዎችና በእኛ መሀል ደግሞ የተለየ ፕሮግራም የለም:: ምናልባት ልዩነቱ አደረጃጀታችን ሊሆን ይችላል:: እሱም ቢሆን ብዙ ልዩነት አላይበትም:: ስለዚህ ለምንድን ነው አንድ ላይ ሆነን የማንሰራው የሚል መግባባት ተደረሰ፤ በዛ መግባባት መሰረት ለውህደቱ የተስማሙት ፓርቲዎች አስቀድመው ይከስማሉ:: ለምሳሌ ሰማያዊ ፓርቲ በቅርቡ ባደረገው ጠቅላላ ጉባኤ የሰማያዊን መክሰም ወስኗል::

አስቀድሞ ፓርቲን ማክሰሙ የሚጠቅመው ትልቁ ነገር አዲስ ለሚቋቋመው አሁን ስሜን ለማናውቀው ሀገራዊ ፓርቲ ሆኖ በዜግነት ፖለቲካ ላይ የተመሰረተ ማኅበራዊ ፍትህን አይዶሎጂው ያደረገ ፓርቲ እንዲኖር ነው የፓርቲው መሰረታዊ አደረጃጀቱ በወረዳ ላይ የሚመሰረት መሆኑ ስምምነቱ ደግሞ ሁሉም አሉን የምንላቸው አባሎቻችን ለምሳሌ በአንደኛው ወረዳ በጋራ ያለን ቦታ ላይ በጋራ አባሎቻችን ይሰበሰባሉ:: ለእዛ ፓርቲ የሚሆኑ የወረዳ አመራሮችን ይመርጣሉ ለአዲሱ አባላት ደግሞ ዕጩ አባላትን ይመለምላሉ::

ከዛ በኋላ ደግሞ ለፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ አባላት በጋራ ቀልጠ ከተዋሃደው የአባላት ስብጥር ውስጥ የተሻለውንና ለእዛ ይመጥናል የሚሉትን ሰው ይመርጣሉ:: እንግዲህ አንድ ፓርቲ ለመሆን ደግሞ ጠቅላላ ጉባኤ ያስፈልጋል፣ ከሁሉም የምርጫ ወረዳዎች የሁሉም ድርጅት አባላት (አንድ ፓርቲ ሆነው ማለት ነው) እነዛ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ይመረጣሉ፣ ጠቅላላ ጉባኤው ተሰይሞ ደግሞ ሌሎች የም/ቤት ወይም በጊዜው ሌላ ስም የሚሰጠው አካል ያቋቋሙና በመጨረሻ አመራሩ ይመረጣል ማለት ነው:: ስምምነቱም ይሄ ነው::

**ግዮን፡- ከዚህ ስምምነት ላይ ለመድረስ ምን ያህል የድርድር ጊዜ ወሰደ?**

**አቶ ቸኮል፡-** በአጭር ጊዜ ነው የሆነው ብዙ ጊዜ ያልወሰደበት ምክንያት አንደኛ የሰዎቹ ቅንነት ነው፣ ሁለተኛ የቀረበው አማራጭ ሐሳብ ደግሞ ብዙ የማያወላዳ ነው:: እንደምታውቀው ከዚህ በፊት ፓርቲዎች ሲዋሃዱ “እኔ ሊ/መንበር እሆናለሁ፣ እኔ ሕዝብ ግንኙነት እኔ ገንዘብ ያዥ ልሁን”

# “ሰማያዊ የከሰመው ለውህደቱ ቁርጠኛ አቋም ስለያዘ ነው”

## አቶ የሺዋስ አሰፋ



**ግዮን፡- በቅርቡ ከሶስት ፓርቲዎች ጋር (የቀድሞ የአንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ አባላትን ጨምሮ) ለማዋሃድ ከስምምነት ላይ ደርሳችኋል፣ የዚህ ውሳኔ መነሻችሁ ምንድን ነበር?**

**አቶ የሺዋስ፡-** መልካም:: አብሮ የመስራትና ወደ አንድ ጥላ የመሰባሰብ ጉዳይ ለረዥም ጊዜ ሲሞከር የቆየና ብዙ ድካሞች አጋጥመውት የነበረ ነው:: እኛ ባለፉት ሁለት ዓመታት ከመኢአድ፣ ከመድረክ ጋር በውጭ ከሚገኙ ጋርም የተለያዩ አብሮ የመስራት ሙከራዎችን አድርገናል:: ነገር ግን አሁን ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ፣ በፊት የነበረው የህዝብ ጥያቄ የመንግስትም ጥያቄ ሆነ:: “ሁለት ሶስት ሆናችሁ በመዋሃድ መወዳደርና መንቀሳቀስ ከተሞከረ ለመንግስትም ለማገዝ ይመቻል፣ ለህዝቡም አማራጭ ለመሆን ይቀላልና ይሄንን አስቡት” የሚል ቀና ሀሳብ ከጠ/ሚኒስትሩ ሲመጣ ተጨማሪ ግፊት ሆነ ማለት ነው::

ዋናው የእዚህ ሀሳብ ገፊ ግን ህዝቡ ነው:: ስለዚህ በዛ መሰረት በሰማያዊ እምነት የኢትዮጵያ ችግር በሰማያዊ ብቻ ወይም ደግሞ በኢህአዴግ ብቻ የሚፈታ አይደለም:: ስለዚህ በአይዶሎጂ የሚመስሉንን እያነጋርን ነበር:: በተለይ በ1997 ዓ.ም በቅንጅት ውስጥ የነበሩትን እነ መኢአድ፣ ኢዴፓን፤ የምህረት አዋጁ ሲመጣ ደግሞ ከአሸባሪነት ስማቸው የተነሳው አርበኞች ግንቦት ሰባትንና ሌሎች ድርጅቶችን በተከታታይ ስናነጋግር ቆይተናል::

አሁን ተገናኝንና ሰማያዊ፣ ግንቦት ሰባት፣ ኢዴፓና የቀድሞ የአንድነት አመራር (ከእስር ▶

የሚል ሲያከራክር የኖረ የረዥም ጊዜ ሂደት ነበር:: ከፕሮግራም ይልቅ የሚይዙት ቦታ ነበር የፖለቲካ ፓርቲዎች መሀል ድርድር ሲካሄድ ብዙ ጊዜ የታዘብኩት::

ይሄ በሌለበት ሁኔታ በፕሮግራም መቅረፅ ላይ የሚካሄድ ውይይት እንጂ ብዙ አወዛጋቢ ነገር አልነበረውም:: ምክንያቱም ብርሃኑ ነጋ የአርበኞች ግንቦት ሰባት ሊ/መንበር ስለሆነ የእዚህ ድርጅት ሊ/መንበር ልሁን ብሎ አያስብም:: ወይንም የሺዋስ የሰማያዊ መሪ፣ ጫኔ የኢዴፓ ስለሆንኩ፣ እነ አንዱ አለምም ቀደም ሲል አመራር ስለነበርን በዚህ አዲሱ ድርጅት ውስጥ ም/ሊቀ መንበር እንሁን አይሉም:: ከዚህ ቀደም በሌሎች ፓርቲዎች ውስጥ ይታይ እንደነበረው ሦስትና አራት ም/ሊቀ መንበር የሚባል ነገር የለም::ስለዚህም ነገሮች ቀለል ባለ መልኩ ወደ ወሳኙ የስምምነት ነጥብ ሊወስዱን ችለዋል::

**ግዮን፡- አብዛኞቻችሁ በ1997 ዓ.ም በሕዝብ ዘንድ ትልቅ ተቀባይነት በነበረው ቅንጅት ውስጥ አባል የነበራችሁ እንደመሆናችሁ መጠን ፣አዲሱ ፓርቲያችሁ ከቅንጅት በምን ይለያል?ቅንጅት ከፍተኛ ተቀባይነት ቢኖረውም ብዙ ስህተቶችን ነበሩበትና?**

**አቶ ቸኮል፡-** ከቅንጅት መፈራረስ ብዙ ተምረናል:: እንደ ድርጅት ደግሞ አርበኞች ግንቦት ሰላማዊ ትግል አያዋጣም ብሎ ወደ ትጥቅ ትግል የሄደ ነበር:: በሂደት ውጣ ውረዶች ገጥመውታል፤ አሁን ደግሞ እዚህ ላይ ደርሷል::

በሰማያዊም በኩል ድርጅቱ እዚህ እንዴት እንደደረሰ የምታውቀው ነው፤ በኢዴፓም በኩል እንደዚሁ የመጡበት መንገድ የሚታወቅ ነው:: በእነ አንዱአለም አራጌ በኩልም ተመሳሳይ በሆነ መልኩ የረዥም ጊዜ ልምድ አግኝተዋል:: ቅንጅት ሲቀናጅ ጀምሮ የጥድፊያ ነገር ነበረው:: እንደገና ደግሞ የድርጅት መሪዎች የተቀናጀበት ሁኔታ ነው የነበረው::

ባጠቃላይ መሰረቱን በሰፊው ዘርግቶ የነበረው ምናልባት መኢአድ እና በተወሰነ ደረጃ ኢዴፓ ናቸው:: ከዛ በመለስ ግን በአጭር ጊዜ የተቋቋሙ ናቸው:: ይህ ቢሆንም የደረሰበት የመንግሥት ድብደባ የሚታወስ ነው፣ ምን ያህል አባሎቻችን እንደታሰሩ፣ ምን ያህል አባሎቻችን ደግሞ እንደተሰደዱ ታሪክ የሚያየው ይመስለኛል::ከእነዛ ጉዳዮች ብዙ ልምድ አግኝተናል:: በውስጣችን ሰላዮችም እየገቡ የሚያተራምሱት ነገር የለም:: የግለሰቦች ክፋት እንኳን ቢኖር አደረጃጀቱ ለእንደዛ ዓይነት ሁኔታ ዕድል አይሰጥም:: የምንዋሃደው ግለሰቦች እንጂ እንደ በፊቱ ድርጅቶች አይደሉም:: ዝም ብሎ ከፓርቲ ም/ቤት ወይም ሥራ አስፈፃሚ እየሰበሰበ በየወረዳው ሹመት የሚሰጥበት አሰራር የለም::

ስለዚህ ለነገ መሬት የረገጠ በኀብረተሰቡ ዘንድ ደግሞ የሚታመኑ አንድ ውህድ የሆነ ድርጅት የሚፈጠርበት ዕድል አለ:: ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት በፖለቲካው ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ልምድ ስለላን ለግለሰቦች ድርጅቱን አሳልፎ የሚሰጥበት ሁኔታ የለም:: ግለሰቦች እንደ ሚናቸው የግለሰብ ነው የሚሆነው እንጂ አንድና ሁለት ግለሰቦች አደባባይ ወጥተው የሚረብሹበት ሁኔታ አይኖርም::

**ግዮን፡- ይሄ ስምምት በትክክልም ወደ ውህደት ተቀይሮ መጋቢት 30 ለሕዝብ ይፋ ይሆናል እየተባለ ነው፤**

**አቶ ቸኮል፡-** እዛ አካባቢ እንደሚሆን ምንም ጥያቄ የለውም:: የምንሰራቸው ሥራዎች አሉ፤ እነሱን ስንጨርስ በዛ ሰሞን ለሕዝብ ይፋ ይሆናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን:: ግን በትክክል የቆረጥነው ቀን የለም::

የወጡት) በተለይ አቶ አንዷለም አራጌና በእሱ ስር የተሰባሰቡ ወጣቶችና ሴቶች አንድ ላይ ሆነን ማኅበራዊ ፍትህን ሊያሰፍን የሚችል፣ በዜግነት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ፓርቲ ለመመስረትና አንድ ተወዳዳሪ፣ ተፎካካሪ የሆነ ኃይል ለመፍጠር እየሰራን ነው ያለነው::

በዚህ መሰረት ሰማያዊ ብዙ ርቀት ሄዷል:: በሥራ አስፈፃሚ፣ በምክር ቤት፣ ከዛም ባለፈው ቅዳሜና እሁድ በጠቅላላ ጉባኤ ሂደት በሙሉ ልብ የሰራንበት ፣ ፓርቲውም የከሰመ መሆኑን በመግለጽ ጭምር ለውህደቱ ፈቃደኝነቱንና ቁርጠኝነቱን አሳይቷል ማለት ነው::

**ግዮን፡- ሰማያዊ በአጭር ጊዜ የመክሰም ውሳኔ በፓርቲው ላይ ሲያስተላልፍ በአባላት መሀል መከፋፈልን አልፈጠረም?**

**አቶ የሺዋስ፡-** ውሳኔው የአጭር ጊዜ አይደለም፤ ከ2009 ዓ.ም ጉባኤ ጀምሮ ይሄ ሀሳብ ሲገፋ ስንወያይበት ነው የነበረው፣ ልዩነቱ በየጊዜው እያወራን ሳይሆን የመጣነው፣ ተመካክረን ሲያልቅ ነው ለህዝብ የገለፅነው:: ለዛ ነው አጭር ጊዜ የመሰለው እንጂ ረዥም ወቅት በዚህ ነገር ላይ አሳልፈናል::

ለምሳሌ በስራ አስፈፃሚ መክረን የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ ካዋቀርን እንኳ ስምንት ወር ይሆነናል:: ለዚህ ጉዳይ ማለት ነው:: በም/ቤት ከወሰንን ደግሞ ሶስት ወር ይሆነናል:: ከዛ በኋላ ነው በጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነው:: አስቀድሞ ግን በስራ አስፈፃሚና በም/ቤት ደረጃ ሙሉ ስምምነት ነበር:: በጠቅላላ ጉባኤው ደግሞ በአብላጫ ድምፅ ነው የተወሰነው::

ፓርቲ ወደ ነፃነት የሚወስድ መንገድ ነው፤ ሀገርን ማገልገያ መንገድ እንጂ በራሱ ግብ አይደለም:: እኛው ነን የሰራነው ፓርቲውን፣ ለሀገር ነው የሰራ ነው :: ስለዚህ ሀገር የሚፈልገው ከሆነ ደግሞ፣ ሀገር በሚፈልገው ቅርፅና አቅጣጫ ማድረግ እንችላለን::

**ግዮን፡- ከፓርቲዎች ጋር ከስምምነት ላይ ያደረሳችሁ የዜግነት ፖለቲካ መሆኑ ይታወቃል፤ በፖሊሲ ደረጃ ልዩነት ያሏችሁ ጉዳዮች ይኖራሉ?**

**አቶ የሺዋስ፡-** እውነት ለመናገር ኢትዮጵያ ውስጥ በአይዶሎጂ ወይም በሀሳብ የተለየ ፓርቲ የለም:: እስካሁን ድረስ:: የትኛውንም ድርጅት ፕሮግራሞቻቸውን፣ ፖሊሲያቸውንም፣ ማኒፌስቶአቸውንም ማየት ትችላለህ፤ ፎቶ ኮፒ እስኪመስል ድረስ አንዱ ከአንድ የተቀዳና ተመሳሳይ ነው::

እኛ ለውህደት የተስማማነው የቅንጅት ቤተሰቦች በመሆናችን፣ ፕሮግራማችንም ሆነ ደንባችን አንድ ስለሆነ ነው:: በጊዜ ሂደት ከመዳበሩ በስተቀር ብዙ ልዩነት የለውም:: ሌሎቹን ፓርቲዎች ብትመለከት ለምሳሌ ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ኦሮሞ ነው ያለው፤ ግን አስራ አምስትና አስራ ስድስት የኦሮሞ ፖለቲካ ድርጅት ነው ያሉት:: እነዚህ በአይዶሎጂ የተለያዩ ልትላቸው አትችልም:: በአማራም ሆነ በትግሬ ስም እንደዛው ነው:: በሲዳማም፣ በአፋርና በሶማሌም እንዲህ ዓይነት ነገር ታያለህ::

ስለዚህ ልዩነቱ የአሰራር ነው::ህገ መንግስቱን ጨምሮ የፓርቲዎች ማቋቋሚያ አዋጅ፣ የአገዛዙ ገፊነት፣ ሁለተኛና ዋናው በሽታ ደግሞ በዘር ወይም በብሔር የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲመሰረቱ ማድረግ ነው:: የፓርቲዎቸ ልዩነት በአይዶሎጂ ቢሆን ኖሮ ከአብዮታዊ ዲሞክራሲ፣ ሶሻል ዲሞክራሲና ሊብራል ዲሞክራሲ ከሶስቱ ውጪ እስከ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ የተሞከረ ነገር የለም::

**ግዮን፡- የሰማያዊ ፓርቲን መክሰም ለምርጫ ቦርድ አሳውቃችኋል?**

**አቶ የሺዋስ፡-** ጉባኤያችንን ስናደርግ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሐይማኖትና የባህል አባቶች፣ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች፣ የግብረ ሰናይ ድርጅቶች መሪዎች፣ የምርጫ ቦርድ ታዛቢ፣ ከአራት መቶ ወረዳ የመጡ የፓርቲ ተወካዮችን ጨምሮ የተለያዩ አካላት ተገኝተዋል:: ከሁሉም ወረዳ ተወክለው የመጡትና ይሄንን ውሳኔ ያሳለፉት ሰዎች ለጉባኤው ሲመጡ ሙሉ ለሙሉ ወጪያቸውን ራሳቸው ናቸው የቻሉት:: ይሄ በፖለቲካ ፓርቲዎች ህይወት ውስጥ አዲስ አብዮት ነው::

ከዚህ በፊት አበል እየተከፈለ፣ ማደሪያ፣ ትራንስፖርት እየተቻለ ነው፤ እኛ ግን ሁሉም የፓርቲ አባል ራሱን ችሎ ሙሉ ወጪውን ሸፍኖ የመጣው:: የወሰነውም በነፃነት ነው:: የፓርቲው መክሰም ሲወሰን ምርጫ ቦርድን ጨምሮ ሌሎችም ታዛቢዎች ነበሩ፤ ምርጫ ቦርድ ታዛቢ እንድልክ በደብዳቤ ጠይቀናል:: ሂደቱም ጤናማና ዴሞክራሲያዊ እንደሆነ፣ የፓርቲያችንን መተዳደሪያ ደንብ ያከበረ እንደሆነ እንዲመለከቱ አድርገናል::


**ግዮን፡- ከፓርቲው መክሰም ባሻገር በጉባኤው የተላለፉ ሌሎች ውሳኔዎች ነበሩ? በተለይ ከካፒታልና ድርጅታዊ ሀብት፣ ንብረት ጋር በተያያዘ?**

**አቶ የሺዋስ፡-** በጉባኤው የተላለፉ ውሳኔዎች አራት ናቸው:: አንደኛው ሰማያዊ ፓርቲ ሙሉ በሙሉ ወደ አዲሱ የውህደት ስምምነት እንዲገባ የሚል ነው:: ሁለተኛ የድርጅቱ አመራርና አባላት ከሊ/መንበሩ ጀምሮ ወረዳ በመሄድ ትክክለኛ የሆነ የህዝብ ውክልና በማግኘት ከታች ወደ ላይ እንዲመጡ የሚል ሲሆን፤ ሶስተኛው የፓርቲው ጥሩ ስም፣ መልካም ዝና፣ የምርጫ ታሪክ፣ ቁሳቁስ፣ ንብረት ሰነዶች፣ በሙሉ ለአዲስ የሚመሰረተው ኃይል ንብረት ሆነው ወደ እዛ እንዲተላለፉ የሚል ነው::

ሌላው ሂደቱ እስኪያልቅ ድረስ ሊ/መንበሩና ም/ሊቀ መንበሩን ጨምሮ ከህግና ምርመራ ኮሚሽን የተዋቀረ ሰባት አባላት ያሉት አስተባባሪ ኮሚቴ ይሄንን እንዲያስፈፅምና እስከ መጋቢት 30 ድረስ አባሉን ወደ ወረዳ በመላክ፣ ንብረቱን በማጣራት በውጭ ኦዲተር በማስመርመር ወደ አዲሱ ውህድ ፓርቲ እንዲያስተላልፍ፤ የፓርቲው ስም፣ አርማ የመሳሰሉ ነገሮች የአዕምሮ ንብረት ሆነው ለሌላ እንዳይሰጡ ተደርገው እንዲያዙ፣ ሰርተፍኬቱ ደግሞ ለምርጫ ቦርድ እንዲመለስ፣ የሚል ውሳኔዎችን አሳልፏል::

**ግዮን፡- እናመሰግናለን::**

# የጥፋቶች ሁሉ ትልቁ ጥፋት ነገን አለማሰብ ነው



መስፍን ጌታቸው

የያንዳንዱ ሰው ወነገ እጣ ፈንታ የሚወሰነው በዛሬ ማንነቱና ድርጊቱ ላይ ነው:: እያንዳንዱ ድርጅትም ሆነ ማህበረሰብ ከፍ ሲልም አገር የሚታነፀው በዛሬ መሰረት ላይ ነው:: ስለነገ ተስፋው ማሰብ የሚያስጨንቀው ሌባና ሽፍታ ብቻ ነው:: መጪውን ግዜ በላቀ አስተዋይነት እየተነበዩ ዛሬ ላይ በጥበብና በቅንነት መስራት እጅግ የተዋበች ብሩን ነገን ይሰጣል::

ነገው ብሩህ የሆነ ግለሰብ ስኬታማ የሆነ ደስተኛ ማህበረሰብ እርሾ ይሆናል:: ብሩህ ተስፋ ያላቸው ማህበረሰቦች ደግሞ በጋራ እጅ ለእጅ በመያያዝ በፍቅር ሲደመሩ አንድነቷ የጠነከረ በእድገት ወደፊት የምትገሰግስና ለዜጎቿ ምቹ የሆነች ታላቅ አገር ይመሰርታሉ::

እንደ እድል ሆኖ እኛ ለዚህ ወግና ክብር አልታደልንም:: ህልማችን ሁሉ ብዝሀነትን ካከበረ ታላቅነት ይልቅ ታናሽ የሆነ ጥበት ላይ ያጠነጥናል:: ፍቅራችን እብሪት የወረሰው ግብዝነታችን ጫማ ስር ወድቆአል:: ከቅንነታችን ይልቅ ክፋታችን ይበረታል::የጋራ ቤታችንን ተስማምቶ ከማነፅ ይልቅ በየጎጣችን ጣሪያ ስር ተወሽቀን የሌላውን ጣሪያና ግድግዳ በክፋት ለመናደድ እንቅልፍ አጥተን እንዳክራለን::

ይሄን የምናደርገው ክፋት ከሰብዓዊነት በላይ ገኖ ስለሰለጠነብን ብቻ ሳይሆን መንፈሳችን በጠቅላላ በገሎ ማሸነፍ ዜማ የተቀኘና ተባብሮ ለታላቅ ድል መብቃትን የሚፀየፍ ደስታችን የሚመዘዘውም ከራሳችን ስኬት ይልቅ ከሌላው ወገናችን ውድቀት እንደሆነ አርገን ስለምናስብ ነው::

በዚህም በአንድ መሰረት ተገንብቶ በአንድ ምሰሶ የታነፀ የጋራ ቤት ውስጥ የምንኖር ወንድማማቾች መሆናችንን በመዘንጋት የሌላውን ጣሪያና ግድግዳ ለመናድ በምናደርገው ጥረት የራሳችንንም ቤት በማፍረስ ተያይዘን እንጠፋለን::

በአጭሩ ሁሉ ነገራችን ነገን ባለማሰብ ባጠፋናት ምድር ላይ ቆም መጪውን ግዜ ይበልጥ ድምጥማጡን በማጥፋት ራሳችንን ወደ ታሪክና ተረትነት ለመቀየር በመሯሯጥ ላይ የምንገኝ ነው የሚመስለው::

ትላንት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በተፈፀሙ ብዙ ስህተቶች ዛሬያችን መልክ አጥታና ዝብርቅርቁ ወጥቶ በጠላትነት ለመጠፋፋት የምንሽቀዳደም ምስኪን ህዝቦች ሆነናል:: አገራችንንም ለዜጎቿ የማትበቃና በልጆቿ መጠፋፋት የደም እምባ የምታነባ የመከራ ምድር አርገናታል::

በጣም የሚያሳዝነው ግን ዛሬ ላይቀ ቆመን ከትላቱ ጥፋት ባለመማር ሳናውቅ ሳይሆን እያወቅን የልጆቻችንን ነገ ድምጥማጡን በማጥፋት ራሳችንንም ሆነ አገራችንን ተረት ለማድረግ የምንረባረብ መሆኑ ነው::

ትላንት እንዲህ ዓይነት ውድቀትና ውርደት ሊመጣ እንደሚችል ባለማሰብ ጥፍር ከመንቀልና ግብረ ሰዶም ከመፈፀም አንስቶ ለመስማት ሳይቀር የሚዘገንኑ የግፍ ተግባራትን በገዛ ወንድማቸው ላይ ሲፈፅሙ የኖሩ ወገኖች ዛሬን ከትላንት ስህተታቸው በመማር እራሳቸውን በንስሃ አንፅተው ነገን የተሻለ ለማድረግ ከመስራት ይልቅ እንዴት የልጆቻቸውን ወጪ ዘመን ከምንም በላይ የሚያጨልም አስከፊ ስራ ለመስራት ይነሳሉ::

ዛሬ በርካታ ወገኖች በትላንት ስህተታቸው ተፀፅተው ነገን የተሻለ ለማድረግ ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ ደፋ ቀና በሙሉበት ወቅት ከተቀረው ወገን ጋ በመተባበር አኩሪ ታሪክ መስራት ሲገባ እንዴት ህዝቡን በሃሰት ፕሮፓጋንዳ አደናግሮ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል በሚል የአጥፊቶ ጠፊ መንፈስ አገር እንዲታመስና የአዲሱ ትውልድ መጪ ግዜ እንዲጠፋ የሚያረግ ድርጊት ይፈፀማል::

ሂትለር ነገን ተንብዮና ድፍን አለምን ሩዋንዳ፣ሳዳም፣ቱኒዚያ እና ጋዳፊ በሃይል የመግዛት ቅዠቱን መርምሮ መጨረሻው የገዛ ወንድሞቹን አስጠፍጥፎ ካበቃ በኂላ እዛች ጠባብ ክፍል ውስጥ አይሞቱ አሟሟት መሞት መሆኑን አስቀድሞ በያውቅ ኖሮ እዛ ሁሉ እብደት ውስት ባልገባም ነበር::

የሩዋንዳ ሁቱዎች ነገን ቀድመው ቢያስቡና በማያልፍ ቀን እንደ ሌላ ቀድመው ቢረዱ ኖሮ ታሪካቸውን ለዘላለም የሚያጎድፍና ዛሬን ቀና ብለው መሄድ እንዳይችሉ በማድረግ አንገታቸውን አስደፍቶ የሚያስቀራቸውን ግፍና ወንጀል ለመፈፀም አይለውጡም ነበር::

የሳዳም ሁሴን ውድቀት መሰረቱ ነገን ያላገናዘበ ግብዝነት ነው:: ሳዳም አለም አልበቃ ብሏቸው ከኢራን ጋ አውዳሚ የሆነ ረዥም ጦርነት አድርገው ከደረሰባቸው ሰፎ የሆነ ሰብአዊና መንፈሳዊ ጉዳት በኂላም ተምረው አደብ መግዛት አልፈለጉም::

እንደገና ኩዌትን በመውረር ህዝባቸውንና ጦራቸውን አስጨፍጭፈው በውርደት ቢባረሩም እሱም ትምህርት ሊሆናቸው አልቻለምeም፡ ሰከን ብለውና ትንፋሽ ወስደው እያደረጉት ያለው ነገር ነገን የቱን ያህል ሊያከፋባቸውና ሊያጨልምባቸው እንደሚችል ለማሰቢያ የሚሆን ግዜም ሆነ ፍላጎት አልነበራቸውም::

በዚህም ታላቋን አገራቸውን ፍርስርሷን በማውጣት ወደ ድንጋይ ክምርነት ለውጠው ከራሱ አልፎ ለሌሎች ይተርፍ የነበረውን ሃብትም ህዝባቸውን ብዙውን አስገድለው፣ ገሚሱን የአካል ጉዳተኛ አድርገው አብዛኛው ኢራቃዊ ከረጂነት ወደ ተረጂነት ወርዶ እጁን ለምፅዋት ይዘረጋ ዘንድ አብቅተው የራሳቸውንም መጨረሻ ፍፁም አሳፋሪና ለወሬ የማይመች በማድረግ እራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ህዝባቸውንም በመግደል ነው ወደ መቃብር የወረዱት::

የጋዳፊ መጨረሻም ከዚህ የተለየ አይደለም:: ህዝብ በእህል ውሃ ብቻ ይኖር ይመስል ሆዱን ሞልተው መንፈሱን በማሰራቸውና አገሩን በአምባገነንነት ረግጠው ስልጣን ላይ ሙጭጭ በማለታቸው መጨረሻቸው ፈፅሞ የማይመቻቸው ከመሆኑም በላይ የአገራቸውና የህዝባቸው መፃኢ እድልም መድረሻውና መጨረሻው የማይታወቅ ረዥም ቁልቁለት ላይ ተጥሎ በመፈጥፈጥና መቼም ሊጠገን በማይችልበት ሁኔታ እንዲንኮተኮት አድርገዋል::

ሆስኒ ሙበረክ ነገን አርቀው ማየትና መተንበይ ቢችሉ ኖሮ የአገዛዝ ዘመናቸውን ያን ያህል የከፋ ባለደረጉት ነበር::

የቱኒዚያ መሪዎች ለአፍተ ቆም ብለው መጪውን ግዜ በድፍረት ለመመልከት ቢጥሩ ኖሮ አገራቸውን ዜጎች ግፍ ግፍ ብለው እራሳቸው ላይ ቤንዚን በማርከፍከፍ በቁም ነደው ለመሞት እስከመጨከን የሚደርሱበት ምድራዊ ገሃነብ አያደርጓትም ነበር::

በጣም የሚገርመው ደግሞ አምባገነኖች ሁሌን ካለፉ ስህተታቸው ወይም ደግሞ የመንፈስ መንትያቸው ከሆኑት አምባገነን መንግስታት አስከፊ ውድቀት ለመማር አለመፍቀዳቸው ነው::

ከዚህ የአምባገነኖች መጨረሻ በመማር እራሳቸውን ከአስከፊ ውድቀት መታደግ ይችሉበት የነበረውን ወርቃማ እድል ቅርጥፍ አርገው በመብላት ካመከኑት አምባገነን መንግስት መሃከል ደግሞ የኛዎቹ መሪዎች በግምባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ::

የኛ መሪዎች ብረት አንስተው ጫካ ከገበቡበት ▶

የመጀመሪያ ግዜ አንስቶ ሁሌም ልባቸው ብቻ ሳይሆን ጭንቅላታቸውም ድፍን ነው:: እንኳን ነገን አርቀው በማሰብ እራሳቸውን የሚያድንና አገራቸውን ከጥፋት የሚታደግ ድርጊት ሊፈፅሙ ቀርቶ በአካባቢያቸው ምን እየተከናወነ እንደሆነ እንኳን ለማወቅ የሚያስችል አቅሙም ሆነ ፍላጎቱ የላቸውም::

ለዚህም ነው በወቅቱ "ተው ከብጤዎቻችሁ ውድቀት ተማሩ" ሲባሉ "ኢትዮጵያ ሊቢያ አይደለችም" መቶ ፐርሰንት በሙሉ ፍቃዱ የመረጠን ህዝብም ልማታዊ መንገዳችንን ከመደገፍ ውጪ ፊፅሞ እጁን አያነሳብንም" በሚል መንፈስ መሳለቅን የመረጡት::

መቼም ቢሆን የራስን ውሸት አምኖ እንደመቀበል የሚከፋ ህመም የለም:: እነ እንትናም "ህዝቡ በሙሉ ልብ አምኖና ፈቅዶ መቶ ፐርሰንት ድምፁን በመስጠት መርጦናል" በሚል ውሸታቸውን ደጋግመው ከመለፈፋቸው ብዛት እውነት የሆነን ያህል አምነው ተቀብለውታል:: ልማታዊ መስመራችን አገሪቱን በተከታታይ በደብል ዲጂት አሳድጎ ሃብታም አርጎአታል የሚል ዲስኩራቸውንም እውነት አርገው ተቀብለውታል:: የነሱ ኑሮ ከለት ወደ እለት በጣም ተሽቀንጥሮ በተተኮሰ ቁጥር የህዝቡም ኑሮ እንደዛው እያደረገ ነው በሚል ጉሮሮ በነጠቁት የተዘረፈ ብር የሚያሰሯቸው ህንፃዎች ቁመታቸው እያደገ በሄደ ቁጥር ድህነት ኑሮውን በተቃራኒው ቁልቁል እያሳደገበት የሚገኘው ምስኪን ህዝብ ህይትም ልክ እንደነሱ ሁሉ እያደር እየጎመራ በህንፃ ላይ ህንፃ በመገንባት በደስታ ጮቤ እየረገጠ የሚኖር መስሎአቸዋል::

እናም እውነት ላይ ከተመሰረተው የወዳጅ ምክር ይልቅ የራሳቸውን ውሸት አምነው በመቀበል ለተቃውሞ አደባባይ የወጣውን ህዝብ በተለመደ አደንቋሪ ጩኸታቸው "የሻቢያ ቅጥረኛ የግንቦት ሰባትና የኦነግ ተላላኪ" በሚል ፈርጀው ጥያቄዎቹን ሁሉ በሃይል ፀጥ ለማሰኘት ሌት ተቀን ተሯሯጡ::

መንፈሳቸው ሰከን ብሎ ሁነኛ መፍትሄ ለመፈለግ የተፈጠረ ባለመሆኑም በሬሳ ላይ ሬሳ ደርቦ መጣልን፣ በግፍ ላይ ሌላ የከፋ ግፍ መጨመርን መረጡ::

የገዛ ውሸታቸውን በማመን ልባቸውን ክፉኛ ያደነደኑት ስለሆነም ይሄን አገር ከጫፍ እስከ ጫፍ ያነቀነቀ ህዝባዊ ማዕበል "የትም የማየደርስ ተራ የዱርዬ ጫጫታ ነው" በሚል መንፈስ እንደሚያሸንፉትና በአጭሩ ፀጥ እንደሚያደርጉት በጣም እርግጠኞች ሆኑ::

ለዚህም ነው ትግሉ ቤተ መንግስተ ድረስ ዘልቆ በመግባት እያንዳንዷን ከፍ ብለው እንዲታዩ ያደረገቻቸውን ምሰሶ እየሰባበረና ቅፅሩን እያፈራረሰ ባለበት ወቅት ሳይቀር ሚዲያ ላይ ወጥተው መደንፋትን የመረጡት::

አሁን ረኸ'ሙ የነፃነት ጉዞ የመጀመሪያ ፍፃሜያቸውን አግኝቶአል:: አምባገነን መሪዎች ከአንድ እናት ተወልደው በአንድ ጭንቅላት አይደል የሚያስቡት:: ጋዳፊ በመጨረሻው ሰዓት ወደ ትውልድ መንደሩ በመመለስ ምሽግ እንደቆፈረው ሁሉ የኛ አምባገነኖችም ተጠራርተው ህዝብ መሃል መደበቅን መርጠዋል::

ሌቦቹና ነብሰ ገዳዮቹ የትላንት ፈላጭ ቆራጮች ሲዘርፉና ሲገድሉ በነበሩበት ወቅት ዞር ብለው እንኳን አይተውት የማያውቁት ህዝብ መሃል ገብተው መደበቃቸው ብዙም ባልከፋ ነበር::

የሚያስከፋውና አደገኛ የሆነው ነገር ህዝቡን እድሜአቸውን ሙሉ ተንከባክበው ባሳደጉትና በመቁረቢያ እድሜያቸው እንኳን ሊፀየፉት እንዳይችሉ ሆኖ በተጣባቸው የጥላቻና የውሸት ፕሮፓጋንዳ አደናግረው ለሌላ ጥፋት ሊያሰልፉት መድፈራቸው ነው::

በእርግጥም ትላንት ነገን በእርጋታ ለመተንበይ ብርታት አጥተው ብልሽትሽቱን ያወጡት ዛሬ ላይ ቆመው ልባቸውንም ሆነ መንፈሳቸውን በንስሃ ከማንፃት ይልቅ መጪውን ዘመን ይበልጥ የሚያጨልም ብቻ ሳይሆን ልክ እንደ ጋዳፊና እንደ ሳዳም ሁሴን የነሱንና የልጆቻቸውን የመጨረሻ ውድቀት የሚያከፋ ድርጊት ላይ መሰማራታቸው አልፎ ተርፎም የጦርነት ድቤ ለማስደለቅ መሞከራቸው በጣም ያሳዝናል::

ጀርመናዊያን በትላንት ድርጊታቸው ያበላሿት ዛሬ ላይ በመቆም ነጋቸውን ይበልጥ ለማዳመን የሚጥሩ ጅሎች አልነበሩም::

ምንም እንኳን ጦርነቱ እጅግ በጣም ብዙ የሆኑ ወንድምና እህቶቻቸውን በማሳጣትና ሃብት ንብረታቸውን ሙልጭ አርጎ በመብላት በትልቅ ግምብ በመክፈል የሁለት አገር ህዝብ ቢያደርጋቸውም ካለፈ ስህተቶቻቸ ው ባለመማር ለሌላ ዘር ጥፋት ግን እራሳቸውን አላዘጋጁም

ይልቁንም የናዚ ፓርቲን በይፋ ፍርስርሱን በማውጣት እንደዚያ ዓይነት ዘርን መሰረት ያደረገ የፖለቲካ ፓርቲ መመስረትን በህግ በመከልከልና ወንጀለኛ ዜጎቻቸውንም ከያሉበት ለቃቅመው ለፍርድ አሳልፈው በመስጠት በፍቅርና በሰላም የፈራረሰች አገራቸውን ነው እንደ አዲስ መገንባት የመረጡት::

ሀዚህም መንገዱ የቱንም ያህል ቢረዝምና ብዙ ልፋት ቢጠይቅም በፅናት ታግለው በመስራት አገራቸውን ከወደቀችበት አንስተው

**ሁቱዎች እጅግ በጣም አደንቁሮ ባሳበዳቸው የዘረኝነት መንፈስ ተመርተው ዳግም ቱትሲዎችን በጥላቻ እናጠፋለን ብለው ቢነሱ ኖሮ ወይም ደግሞ ቱትሲዎች "ትላንት ህዝባችንን በግፍ ፈጅተውብናል" በሚል የበቀል መንፈስ ተሳክረው እጃቸውን ሁቱዎች ላይ ለማንሳት ቢሽቀዳደሙ ኖሮ ዛሬ ሩዋንዳ የምትባልን አገር አፍሪካ ካርታ ላይ ፈልሳ ማግኘት የሚታሰብ አይሆንም ነበር**

ቀና ለማድረግ በቅተዋል:: ለሁለት ከፍሎ የለያቸውንም ግምብ አፍርሰው ህዝቡን በመቀላቀልም ዛሬ ጀርመንን በፍፁም ሊንቃት የማይችል የአለማችን ቀዳሚ ኢኮኖሚ ባለቤት ለመሆን የበቃች ተላቅና ሃያል አገር እንድትሆን አርገዋታል፡

በርግጥ እንዲህ ዓይነቱን አኩሪ ተግባር ለመፈፀም ጥበብና አርቆ ማሰብ የሚችል ጭንቅላት ያስፈልጋል:: ጀርመኖች ትላንት ካለፈ ስህተታቸው ባለመማር እራሳቸውን ለሌላ ጥፋትና እልቂት አዘጋጅተው ቢነሱ ኖሮ የዛሬዋ ታላቅ አገር በህይወት መኖት ትችል ነበር?

በፍፁም አትችልም ልክ እንደ ጋዳፊና እንደ ሳዳም ጥፋትን በጥፋት በማባዛት የአገሪቱም ሆነ የመሪዎቿ እጣ ፈንታ ተረት ሆኖ መቅረት ይሆን ነበር::

ሩዋንዳውያንም ይሄንን ተያይዞ ከመጥፋት የፀዳ በሳል አስተሳሰብ መርጠው በመከተላቸው ነው ከዛ ሁሉ እጅግ በጣም ዘግናኝ የሆነ አስከፊ እልቂት በኋላ ተአምራዊ ሊባል በሚችል ጥበብ አገራቸውን መልሰው በማቆም ተስፋ ከሚጣልባቸው የአፍሪካ አገሮች መሃከል አንዷ እንድትሆን ያደረጉት::

ሁቱዎች እጅግ በጣም አደንቁሮ ባሳበዳቸው የዘረኝነት መንፈስ ተመርተው ዳግም ቱትሲዎችን በጥላቻ እናጠፋለን ብለው ቢነሱ ኖሮ ወይም ደግሞ ቱትሲዎች "ትላንት ህዝባችንን በግፍ ፈጅተውብናል" በሚል የበቀል መንፈስ ተሳክረው እጃቸውን ሁቱዎች ላይ ለማንሳት ቢሽቀዳደሙ ኖሮ ዛሬ ሩዋንዳ የምትባልን አገር አፍሪካ ካርታ ላይ ፈልሳ ማግኘት የሚታሰብ አይሆንም ነበር::

እናም ወገኖቼ እራስን ክፉ በሆነ የጥላቻ መንፈስ አስክሮ ዳግም ሰይፍ መዞ መነሳት ለመንም አይበጅም:: የራስንና የገዛ ወገኖችን አወዳደቅ እጅግ የከፋ ነው የሚያደርገው ከትላንት ባለመማር ነገ አገር እንዳይኖረን አድርጎ ይበልጥ ማጥፋት ደግሞ እኛን ፊፅሞ ሊመጥነን የማይችል ትልቅ ሞኝነት ነው::

ይሄ እውነት የትላንት አለቆቻችንን ብቻ ሳይሆን የዛሬ መሪዎቻችንንም ነው የሚመለከተው:: የዛሬ መሪዎቻችን በፍፁም አስተውሎት ነገን ቀድመው በመተንበይ ይቺን ከራሷ አልፋ ለሌሎች መብቃት የምትችል ቅድስት አገር መጪ ግዜ ብሩህ ለማድረግና ሁሉም ኢትዮጵያዊ ልቡን ከጥላቻ አንፅቶ በህግ እየተዳኘ በፍቅርና በሰላም አንድ ሆኖ በኩራት ደረቱን ነፍቶ እንዲንቀሳቀስ የማድረግ ትልቅ ታሪካዊ ሃላፊነተ አለባቸው::

ነገር ግን ይሄ ሳይሆን ቀርቶ በአሸናፊነት ኩራትና ትቢት ልባቸውን የኛ ነው በሚል መንፈስ ሌላውን በመርገጥ እራሳቸውንና የኔ የሚሉትን ወገን በዝርፊያ ለማበልፀግ የሚጥሩ ከሆነ ግን እራሳቸውን ለሳዳማዊ ውርደት አገሪቱንም ለኢራቅ አይነቱ ውድቀት ነው የሚያበቋት::

እናም በሳዳማዊ እብሪትና ጅልነት ታውረን ነጋችንን ተያይዘን የምንጠፋበት ከማድረግ እንቆጠብ:: በጀርመናውያን ብልሃት በሩዋዳውያን ጥበብ ራሳችንን በማነፅ እኛም በፈጠርነው ቅዤት መሀላችን ገንብተን ያቆምነውን ክፉ የጥላቻ ግምብ አፈራርሰንና ራሳችንን በመንፈስ ከፍ አርገን ሁላችንም የምንናፍቃትን ብቻ ሳይሆን ለሁላችንም በእኩል የምትበቃ ታላቅ አገር ለመገንባት ከልብ እንረባረብ::

አንድ ሆነን ከተነሳን የማንፈነቅለው አለት፣ የማንወጣው አቀበት የማናንበረክከው ድህነት አይኖርም:: ደሞም በሃቅ ከተነሳን ከተባበርን በፍቅር ከተጣመርን በርግጥም እንችላለን::



ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

# ስለሌላው ነጻነት ከማሰብ በፊት...!?

ካማንኛውም በጎ ወይም ክፉ ድርጊት ጀርባ ሐሳብ አለ:: በአእምሮ ውስጥ ያለ አንድ ሐሣብ ሐሳብ የደረሣቸውን ሰዎች ለድርጊት ሲያነሣሣ /ሲያዘጋጅ/ ወይም ሲፈፀም ሊያስከትል ከሚችለው ወይም ካስከተለው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት በመነሳት በጎ ወይም ክፉ ሐሳብ ተብሎ ሊፈረጅ ይችላል:: ነገር ግን ማንም ሰው የሌሎችን ዜጎች የሐሳብ ነጻነት የሚገድብ ተግባር ሊያደርግ አይፈቀድለትም:: የአንደኛው ግዴታ በአግባቡ ያለመወጣት የሌላውን ነጻነት መከልከል ነው። የሌሎችን ግለሰቦች የፍላጎትና ምክንያታዊ የሐሳብ ነጻነት ለመጋፋት መሞከር በራሱ ትልቅ የመርህ መዛነፍ ነው። ማንም ሰው በጎም ይሁን ክፉ የመሰለውን ሐሳብ ያለ ስጋት በነጻነት የማቅረብ ሙሉ ነጻነት አለው:: ማንኛውም አይነት ሐሳብ ገበያው ላይ ለሸያጭ ቀርቦ ይህ ሐሳብ ክፉ ነው፤ ይህ ሐሳብ በጎ ነው ብሎ፤ ሐሳቡን ሊገዛ ለመጣው ገዢ መተው ይቀድማል:: ከዚህ ውጪ የኔ ሐሳብ ብቻ ነው ትክክል ብሎ ጠመንጃ ደግኖ ተጋተው ማለት ግን የፀረ ዴሞክራሲያዊነት አንዱ መገለጫ ነው:: ምክንያቱም ማንም ሰው ገበያው ላይ የመሰለውን ሀሳብ ለሽያጭ ለማቅረብ ሙሉ ነጻነት ያገኘውን መሀብት ያህል፤ ገዢም ሐሳቡን የመግዛትና ያለመግዛት መብት ሊኖረው እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል::

ከጠመንጃ በመለስ ማንኛውም ግለሰብ ሆነ የፖለቲካ ድርጅት የመሰለውን ሐሳብ ለደጋፊዎቹ ወደ ገበያ የማቅረብ ሙሉ ነጻነት አለው:: ይህ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት አንድ አካል የሆነው የመናገር ነጻነት (Freedom of speech) እንዲከበር በጣም በትልቁ መንግሥት፣ሲቀጥል ፓርቲዎች ከዚያም ሕዝብ ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው:: ለሕዝብ ታዛዥ ነኝ የሚል መንግሥት ከጠመንጃ በመለስ የሕዝቦች ሐሳብን በነጻነት የመግለፅ ነጻነትን ማክበር አለበት:: ሕዝብ ደግሞ በመናገር ነጻነት ላይ ደባ የሰራውን አካል የመከታተል ሲያጠፋ የመገሰፅና የመቅጣት ትልቅ ኃላፊነት አለበት:: የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበሩት ዴሞክራቱ ጆን ኤፍ ኬኔዲ፣ “ሕዝቡ እውነትንና ሐሰትን እንዲዳኝ የማይፈልግ መንግሥት የሐሳብ ገበያ እንዳይኖር የሚፈልግና ሕዝቡን የሚፈራ ነው፤” ብለው ነበር:: ከጠመንጃ በመለስ ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት የመሰለውን አጀንዳ በፈለገው ቦታ፤ በፈለገው መንገድ የማቅረብ ሙሉ ነጻነት አለው:: ሐሳብ የቀረበለት ሕዝብም ሐሳቡን የመግዛት ያለ መግዝት መብት የርሱ ይሆናል ማለት ነው::

ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች በልበ ሙሉነት የሚንቀሳቀሱበት፣ ከሥጋትና ከፍርሀት የሚላቀቁበት ምኅዳር መፈጠሩ ብቻ ሳይሆን ለሀገሪቱ ብሔራዊ ጥቅም መከበር የሚጨነቁ በአገራዊ ጉዳይ የባለቤትነት ስሜት የሚሰማቸው ዜጎች እንዲሆኑ የማድረግ ድርሻም ኃላፊነትም የመንግሥት ነው:: በዚህም የዶ/ር አብይ አህመድ መንግስት ሁሉም ፖለቲከኞች በሀገራቸው ጉዳይ ላይ ያላቸውን ለበጎ የሚሆን ጠቃሚ ጠጠር ለሀገር እንዲወረውሩ ለማድረግ ሁሉም ሀይሎች ወደ ሀገራቸው በሰላም እንዲገቡ ቁጠማ ነስንሶ በደስታ ተቀብሏል:: በተለያየ ጉዳዮች ታስረው የነበሩ እስረኞቸ ከእስር ለቋል:: የዐቢይ መንግሥት ይህን በማድረጉ እንደ መንግሥት ሊወደስ፤ ሊከበርና ሊበረታታ የሚገባው ነው:: ነገር ግን ከዚህ ሁሉ መልካም ነገር ለጥቆ የታየው ነገር ለሕዝብ ያልተመቸ አዳዲስ አላስፈላጊ መንገራገጮች እዚህም እዚያም እየተስተዋለ ነው::

በአሁኑ ሰዐት በሀገሪቷ እየመጣ ያለው የለውጥ ንፋስ በአግባቡ ሳንጠቀምበት በከንቱ እንዳያመልጠን ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችና ሕዝቡ ለውጡ ዳር እንዲደርስ በጥንቃቄ ሊይዙት ይገበዋል:: ቀደም ባሉት ዘመናት የሀገሪቱን ታሪክ በመሠረታዊነት ሊቀይሩ የሚችሉ በርካታ መልካም ፖለቲካዊ አጋጣሚዎች ብናገኝም፤ለመልካም እድል እድለ ቢሶች በመሆናችን፤ የመጣልንን መልካም እድል በአግባብ እና በጥንቃቄ ባለመጠቀማችንና በከንቱ መምከናቸው እንደ ሀገር ትልቅ ዋጋ እንዳስከፈሉን ማንም የሚያውቀው የቅርብ ጊዜ ታሪካችን ነው:: አሁንም የመጣውን አዲስ ለውጥ ሁሉንም ኢትዮጵያውያንን በጋራ የሚጠቅም እንደዲሆን ሁላችን የበኩላችን ጠጠር በመወርወር ለውጡን እሚፈለገው ቦታ ለማድረስ ልንታትር ይገባል:: ለውጡ አንዱን ሕዝብ የሚያቅፍ ሌላውን ሕዝብ የሚያገል እንዳይሆን ብርቱ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል እንላለን:: በአሁኑ ሰዐት አንዳንዶች ከለውጡ በርቀት የተቀመጡና ያኮረፉ የሚመስሉ ኃይሎች፤ ከኩርፊያ ወጥተው የለውጡ አየር ተጋሪና ተቋዳሽ እንዲሆኑ ማድረግ ወደ ኋላ ሊባል አይገባም:: አንዳንዶች ለውጡን ባለማወቅ፤ሌሎቹ ደግሞ በእልህ ጥቂቶች ደግሞ በአወቅኩሽ ናቅኩሽ ለውጡን እየተቃወሙ ይገኛሉ:: ስለዚህ ለጋራ ለሁላችን እንደ ሀገር የመጣውን ለውጥ በውጤቱ እንዳይመክን፤ አኩርፈዋል ከሚባሉ ሀይሎች ጋር ተቀራርቦ በብስለት፤በትህትና በዲፕሎማሲ መንገድ በመነጋገር፤ ሁሉም የድርሻውን ሚና በጋራና በትብብር ለወገኑ እንዲያበረክት ማድረግ የመንግሥት እና የሕዝብ ኃላፊነት ሊሆን ይገባል:: ባለማወቅ ለውጡን ያልተቀበሉ ኃይሎች የለውጡ ትክክለኛ መዳረሻ እና እሳቤ ምን እንደሆነ ማስረዳት፤እነሱ ያዩበት ዕይታ በነጻነት እንዲያቀርቡ ማበረታታት፤ ያቀረቡት የተቃውሞ መንገድ ትክክል ካልሆነ በረጋ መንፈስ በማስረዳት፤ የሚያዩበትን መነፅር የተሳሳተ እንደሆነ አሳምኖ መነፅራቸው እንዲቀይሩ ማድረግ ይመረጣል:: በእልህ ለውጡን የሚቃወም ኃይል ደግሞ በእልህ አገር እንደማይመራ፤አገርና ሕዝብ በብስለት፤በጠረጴዛ ዙርያ እንጂ በእልህ እንዳልሆነ ለማሳየት እንደ መንግሥት ብርቱ ዲፕሎማሲያዊ ሎቢይ በማድረግ፤ ከእልህ መንገድ እንዲወጡ ማድረግ የመንግሥት ድርሻ ትልቅ ነው::

ለውጥ ሲባል ከመነሻው ብዙ ውጣ ውረዶችና መንገራገጮች ያሉት መንገድ ነው:: ለውጥ ዝም ብሎ ከመንገድ የሚታፈስ ስላልሆነ እዚህም እዚያም ችግር መከሰቱ ባህሪያዊ ነው:: በለውጥ ወቅት ደግሞ ፖለቲካ ወደ ሀዲዱ የሚገባው፤የለውጥ አስተሳሰብ ተቀባይነት የሚያገኘውና የሚዳብረው በውይይት በመሆኑ ልዩነትን ያልዘነጋ፣ ነገር ግን እንደ ሀገር ሁሉን አሳታፊ የሚያደርግ ሰላማዊ ውይይት ከሁሉም ሀይሎች ጋር ማድረግ ቅድሚያ የሚሰጠው አንገብጋቢ ጉዳይ ነው ::

አንዳንድ የሀገራችን ፖለቲካ ድርጅቶች ለሕዝብ የቆሙለትንና ለዘመናት ሲታገሉለት የነበረውን አላማቸውን ዘንግተው ዛሬም እንደ ትላንቱ ዋጋ የሚያስፍል ግጭት ዳግም ተመልሰው ሊገቡ አይገባም:: ትላንት ተጨቆንን ሲሉ የነበሩ ኃይሎች፤ ዛሬ እነርሱ ራሳቸው በጨቋኝነት ሥርዓት ውስጥ እንዲዘፈቁ ወቅቱ አይፈቅድላቸውም:: ለሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ነኝ ከሚል አንድ የፖለቲካ ፓርቲና አመራር ▶

በፀረ ዲሞክራሲያዊ ፣በአፈናና በወታደራዊ አገዛዝ ፣በዜጎች ላይ የፈላጭ ቆራጭነት ስሜት በተሞላ የአስተዳደር እርከን ላይ የሚገኝ ከሆነ ከዘመኑ ጋር አብሮ የሚሄድ የፖለቲካ ፍልስፍ ጎዶሎነት የሚንፀባረቅበት ነው ማለት ይቻላል:: ነጻ አውጪና ዴሞክራሲያዊ ነኝ የሚል ኃይል፤ተመልሶ የነጻነት ቀበኛ ሲሆን ማየት አሳፋሪ ነው:: አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ የሚለውን ድንቅ አባባል እዚህ ቦታ ላይ ልዋስና ነጻነትን የማያውቁ ነጻ አውጪነታቸውን ጎላ አድርጎ የሚያንፀባርቅ ይሆናል። ለሕዝብ ነጻ አወጣለሁ ብሎ የተመሰረተ አንድ ፓርቲ ራሱ የነጻነት ትርጉም ሳይገባው ሌላውን ነጻ ለማውጣት ሞራልም ብቃትም ሊኖረው አይችልም:: እንዲህ አይነት ፓርቲ ነጻነት የማያውቅ ነጻ አውጪ ከመባል አይዘልም።

እስከ ዛሬ ድረስ በተለያዩ ጊዜያት የኢትዮጵያን ሕዝብ ነጻ ሊያወጡ ብዙ ፓርቲዎች ተመስርተዋል:: ነገር ግን ኢትዮጵያን ነጻ እናወጣለን ብለው የተነሱት የፖለቲካ ድርጅቶች፤ ተመልሰው ጨካኞችና አፋኞች ሲሆኑ እንጅ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ነጻ ሲያወጡ አላየንም፣ በየጊዜው ምለው እና ተገዝተው እራሳቸውን በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅት ዙሪያ ያደራጁ የፖለቲካ ቡድኖች የአገርንና የሕዝብን ዘላቂ ጥቅም እና ደህንነት ሲጎዱና አደጋ ላይ ሲጥሉ፤ሀገርን ወደ ኋላ ሲመልሱ እንጂ፤ በዘላቂነት ቃላቸውን ጠብቀው ሕዝቡን በእውነተኛነት ነጻ ሲያወጡ፤ከድህነት ሲያላቅቁ በእድሜዬ አላየሁም:: ዛሬም በሀገራችን ያለው ሁኔታ በቅርበት ጠጋ ብለን ካስተውልን አንዳንድ ነጻነት በማያውቁ ነጻ አውጪዎች አገር ወደ ገደል አፋፍ ሊያደርሱ እያስፈሰፉ እንደሆነ ዕያየን ነው:: 'ሳይቃጠል በቅጠል' እንዲሉ ነገም ነጻነትን የማያውቁ ነጻ አውጪዎችን በመንገዳችን ላይ የሰላም ጋሬጣ እንዳይሆኑብን በእንጭጩ ከጥፋትና ከሕገ ወጥ አካሄዳቸው እንዲታቀቡ ሕዝብና መንግስት ሊገስፃቸው ይገባል።

**የኢትዮጵያ ሕዝብ በየትኛውም ዘመን ስለ ብሔሩ ተጨንቆ አያውቅም፡፡ ስለ ቋንቋው አሳስቦት አያውቅም፡፡ አሁን ግን በከፋፍለህ ግዛ መርህ ሕዝብን ሰጥ ለጥ አድርጎ ለመግዛት ሲባል፤አንዱ ፖለቲከኛ ተነስቶ ብሄሩን መሰረት አድርጎ ጥቅም ለማጋበስ የሚጠቀምበት ነው**

አቀጣጣይ እሳት የሚወረውሩ አንዳንድ ሚድያዎችና አጥፊ አክቲቪስቶች የሚያሰራጩት አሉታዊ ውጤት በመከላከል በሕግ የተደነገገውን ውሳኔ ዕውን ማድረግ የሚያስችሉት ብቸኛው መንገድ አጥፊዎችን ቁጥጥርና ክትትል ማድረግና ሕግና ሥርዓት የሚያበጅበት መንገድ ማፈላለግ የመንግሥት የዘወትር የቤት ስራው ሊሆን ይገባል::

የፌስ ቡክ 'ነጻነት የማያውቁ ነጻ አውጪዎቻችንንም' በዚሁ እረድፍ ተሰልፈው ስናይ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ከድጡ ወደ ማጡ እየሄደ ለመሆኑ አንድ ምልክት ሊሆነን ይችላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ አምባገነን ገዢም ሆነ የመብቱ እረጋጭችን በታሪኩ አጥቶ አያውቅምና ነገንም ልታጨልሙብን እንቅልፍ አጥታቸሁ የምትገኙ የፌስ ቡክ 'ነጻነት የማታውቁ ነጻ አውጪዎቻችን' ከዚህ እኩይ ተግባራችው ትታቀቡ ዘንድ በሕዝብ ስም እንመክራለን። ኢትዮጵያውያን በዘመናቸው የዲሞክራሲ ባህል፣ የሕግ ለዕልና እና ፍትሕ የማያበቅሉ፣ ቢያበቅሉም ፍሬ የማያፈሩ ሕዝቦች ናቸው ለሚለው የምዕራቡ ዓለም ትችት ማጠናከሪያ አታድርጉን::

መቼም ይሁን መቼ መንግሥት በሕግ የተደነገጉ ጉዳዮችን የሚጥስ ማንኛውንም ሙከራ ወይም ድርጊት እንዳይከናወን በመከላከል፤ የሕግ የበላይነትን የማረጋገጥ ኃላፊነት በሕዝብ እንደተጣለበት ይታወቃል:: ከዚህ አኳያ በመንግሥት የሚወሰዱ ማንኛውም የመፍትሄ እርምጃዎች፤ የአገሪቱንና የሕዝቦቿን ሰላምና ደህንነት መብት የመጠበቅ ጉዳይ በመሆኑ ተገቢና አስፈላጊነቱ ለክርክር የሚቀርብ ጉዳይ ሊሆን አይገባም::

በአፍሪቃ የጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ትግል ፈር ቀዳጅ የሆነች ኢትዮጵያ ዛሬም አዲስ የነጻነት ትግል እንድታደርግ ተዘጋጅታለች:: ከዘረኞችና ከጠባብ ብሔርተኞች ጋር ዳግም ትግል ትሻለች:: ዛሬ አብሮ የመኖር አዲስ አስተሳሰብ፣ለአዲስ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት፣ዜጎች በፈለጉት ቦታ መኖር መብት መከበር፣ለሰላምና ለጋራ ወንድማማችነት የማያቋርጥ ትግል ካላደረግን እየመጣ ያለው ጫፍ የወጣ የዘረኝነትና የጠባብ ብሔረተኝነት ጋሬጣ ወደ ፊት አያራምደንም:: እጃችንን አጣጥፈን ዝም ብለን ከተቀመጥን የዘረኞችና የጠባብ ብሔርተኞች አካሄድ አገራችንን ከገደል አፋፍ ሊያደርሳት ይችላል:: ስለዚህ ለአዲሱ ትውልድ የምትሆን ሁሉን አቃፊ አገር ለመመስረትና ልጆቻችን በሰላም የሚኖሩባት ፤በኩራት የሚሰሩባት አገር እንድትኖረን ከፈለግን ከዛሬ ጀምረን ትግላችን ከዘረኞችና ከጠባብ ብሄርተኞች ጋር ሊሆን ይገባል::

የአንዳንድ ፖለተካ ፓርቲዎች ነጻነትን የሚያዩበት መነፅር የተንሸዋረረ ነው:: °ነጻነትን ሳያውቅ ነፃ አውጪ° መሆን ደግሞ ይበልጥ ያሳፍራል:: በአገራችን አባባል ሞኝ አሸነፈ፣ ምን ብሎ? እምቢ ብሎ የሚል አለ:: እኛም ስለ ነጻነት በቅጡ ያልገባቸውን ላለመታገል እምቢ ብለን ዝም ብንል ተጎጂዎች እኛ ብቻ ሳንሆን ልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችን ድረስ ይዘልቃል:: አንደኛው ሀይል ነጻነት እንዲያገኝ ሌላውን ባርያ ማድረግ አይገባም:: የነጻነት ትርጉምና እሳቤ በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ነው::

የዜግነት ፖለቲካ አራምዳለሁ የሚልም ሆነ የዘውግ ፖለቲካ ድርጀት፤ በየትኛውም ክልል ሄዶ የፖለቲካ አላማውን የማስረዳትና የመቀስቀስ ሙሉ መብት አለው:: ነገር ግን የዘውግ ድርጅቱ የዜግነት ፖለቲካ የሚያራምደውን ፓርቲ፤ ሐሳብህ °በኔ ብሄር° ቦታ ላይ ልትሸጥ (ልታቀርብ) አትችልም የማለት ምንም መብት የለውም:: ያንን ክልል ለርሱ ብቻ ማን ሰጠው? በኢትዮጵያ ምድር እንዲህ የሚል የተፎካከሪ ፓርቲ በዕይናቸ እያየንን ነው:: እንዲህ አይነት ፓርቲ በብሔሩ ተወሽቆ፤አዲስ ሐሳብ ፈርቶ፤ አማራጭ የሌለውን የብቻውን ሐሳብ እሱ ብቻ ሊሸጥ የፈለገ መሆኑ ስናይ የፖለቲካ አቅም ያጠረው መሆኑ ቁልጭ አድርጎ መስታወቱ ያሳየናል:: እንዲህ አይነት ፓርቲ ሲጀመር ፓርቲ ነው ብሎ ለመቀበል ይከብዳል:: ሲቀጥል ሐሳብ የሚፈራ ፓርቲ፤ በያዘው አላማና ፕሮግራም እምነት ስለሌለው ነው፤ ፓርቲውን የመሰረቱ አባላት ፓርቲ ከሚያቋቁሙ ሌላ ሥራ ቢፈልጉ ወይም አርፈው ቢቀመጡ ይሻላቸው ነበር::

በኢትዮጵያ አሁን ከምንም በላይ የሚያስፈልገው ዘረኝነት ማስፋፋት ሳይሆን የሕዝብ ነጻነትና የሕዝብ ብልፅግና፤የሰው ልጅ ስብእናን የማክበርና የሀገር ሉአላዊነት ማስክበር ላይ ተግቶ መስራት ይመረጣል:: አቶ ኦባንግ ሜቶ አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ሲያወያዩ እንዳሉት "በኢትዮጵያ የዘር የበላይነት ሳይሆን የሕግ የበላይነት ሊኖር ይገባል" ነው:: የሕግ የበላይነትና የሰው ልጅ ስብእና ማክበር፤ልዩነትን ማድነቅ ፤የሀገር ሉአላዊነት ከምንም ነገር በላይ፤ከወረቀት አልፎ በትክክል ወደ ተግባር ከተለወጠ ብሄርና ዘር መቁጠር ቀስ በቀስ ወደ እንጦሮጦስ ይገባሉ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በየትኛውም ዘመን ስለ ብሔሩ ተጨንቆ አያውቅም:: ስለ ቋንቋው አሳስቦት አያውቅም:: አሁን ግን በከፋፍለህ ግዛ መርህ ሕዝብን ሰጥ ለጥ አድርጎ ለመግዛት ሲባል፤አንዱ ፖለቲከኛ ተነስቶ ብሄሩን መሰረት አድርጎ ጥቅም ለማጋበስ የሚጠቀምበት ነው::

ዛሬ በሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊገነባ የሚችለው በአንድ ወገን ፍላጎት ወይም ጥረት ብቻ ሳይሆን በሁሉም ኃይሎች የጋራ ሆነ መግባባት ያስፈልጋል:: ለመግባባት ደግሞ በነጻነት መነጋገርና መደራደር የሚቀድም ጉዳይ ነው:: ዛሬ የሌለ ምክንያት እየፈጠሩ ወይም በተራ ጉዳይ የፖለቲካ መጠላለፍ ውስጥ መግባት፤የሕዝብን የልብ ትርታ አለማዳመጥ ወይም የህዝብን ችግር አለመረዳት ነው:: እንደካሁን ቀደሙ በጉልበትና በአጉል ብልጣ ብልጥነት የተጀመረውን በጎ ሒደት መቀልበስ አገርን ችግር ውስጥ ህዝብን መካራ ውስጥ መክተት ነው:: ሁሉም ወገኖች ለሕግ የበላይነት ክብደት በመስጠት ለዘመናት ፍትሕ፣ ሰላም፣ ዴሞክራሲና ልማት የተጠማውን ሕዝብ ለማርካት በቁርጠኝነት ታጥቀው መነሳት ይገባቸዋል::

በሀገራችን የተጀመረው የለውጥ ጉዞ የሚሰምረው ሁሉም ያገባናል የሚሉ ወገኖች ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ ለተግባራዊነቱ ተዓማኒነት ሲያገኝ ብቻ ነው:: ለዚህ ደግሞ ከወዲሁ ከጠመንጃ በመለስ የማንኛውም ወገን ሀሳብ በየትኛውም ገበያ ላይ ቀርቦ እንዲሸጥ መፍቀድ፤ የነጻነት አስተሳሰብ አለኝ የሚል ማንኛውም ሀይል የመጀመሪያና ትንሿ ፈተናው ናት:: በዚህች ከወደቀ በሌላ በምን ሊያልፍ አይችልም:: ምክንያቱም የነጻነት መርህና እሳቤ የማያውቅ ሀይል ነጻነት የማያውቅ ነፃ አውጪ ይሆናል:: ስለዚህ ስለ ሌላው ነጻነት ከማሰብ በፊት መጀመሪያ እራስን በአስተማማኝ የነጻነት ቁመና ላይ መገኘት የግድ ይላል!

*ኢትዮጵያ ለዘላለም በክብር ትኑር*



ተሾመ ሽፈራው

# የአሰላሳዮቹ አብዮት

የዓለም የሥልጣኔ ታሪክ ጸሓፍት በዘመንም አሰፋፈር መካከለኛው የሚባለው ክ/ዘመን እስኪጠባ ድረስ የሰው ልጅ ሥጋዊ /ቁሳዊ/ ሕይወቱን ንቆ መንፈሳዊነትን ያስቀድም ስለነበር ዓለም የሥልጣኔ ዐይኗ አልተገለጠም ነበር:: ለዘመናት ተከናንቦት የነበረው የመንፈሳዊነት ካባውን ማውለቅ ሲጀምር ነው ጨለማው ወገግ እያለለት የመጣው:: የሰው ልጅ የሚያምነውን ቀኖና እንዲፈትሽ ሲፈቅድ እና ከጭፍን አምላኪነት እንዲላቀቅ የሚያስገድድ አዲስ ንቃተ ኅሊና ማቆጥቆጥ ሲጀምር፣ ያን ጊዜ ነው ዓለምና የሰው ልጅ ታላቁን ቁሳዊ ሥልጣኔ መተዋወቅ የጀመሩት፤ በተለይ ከ14ኛው መቶ ክ/ዘመን ሁሉም ነገር መፈተሽና መሞከር አለበት በሚል እሳቤ በሰው ልጅ አእምሮ ላይ ዕውቀታቸውን መዝራት የጀመሩት ጥልቅ አሰላሳዮች ምስጋናውን የሚወስዱ ናቸው:: መካከለኛው ዘመን ተከትሎ በ17ኛው በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን የሰው ልጅ የዕውቀት ዐይኑ የበራበት እና ሁሉንም ነገር በሳይንስ መነጽር መመልከት የጀመረበት ወቅት ነው::

የዓለም የሥልጣኔ መሰረቷ የቆመው በተለያዩ ዘመናት የማኅበረሰቡን ዐይን ገላጭ በሚባሉ ልሂቃን የፈጠራ ሥራ በተለይ ደግሞ ከ17ኛው መቶ ክ/ዘመን አንስቶ ብቅ ብቅ ማለት በጀመሩት ሳይንቲስቶች የምርምር ሥራ እንደሆነ እሙን ነው:: የልሂቃኑ ማንነት እና የሥራ ድርሻን ስናወጋ ታዲያ በቀዳሚነት ከሚዘከሩ ልሂቃን መካከል እንግሊዛዊው የሕግ ሰው ፍራንሲስ ቤከን እና ፈረንሳይ ምድር የተወለደው ሬኔ ዴካርት ይገኛሉ:: እነዚህ የተለየ እውነት እና እውቀት ይዘው ወደ አደባባይ የወጡ ግለሰቦች ከ17ኛው እና 18ኛው መቶ ክ/ዘመን ቀደም ብሎ ድፍን አውሮፓን በማሰስ እና የተለያየ ሀገር ማኅበረሰብ ባህል እና ታሪክ በማጥናት የአውሮፓውያኑን ዐይን ገለጡለት:: በእነሱም ምክንያት አውሮፓዊያን ከራስ ሀገር ባሻገር ስላለው ሌላ ዓለም፤ አዲስ ማኅበረሰብን ለማወቅ እንዲጓጉ አድርገዋል:: ይሄ ደግሞ የሰው ልጅ ሌላውን ሕዝብ እና አህጉርም መጎብኘት የሚያመጣውን መንፈሳዊ እና ቁሳዊ እርካታ የእውነት በመረዳቱም እስከ አፍሪቃ እና አሜሪካ ድረስ ማሰስ ጀመረ::

በብዙ ሀገር መንግሥታት ሕዝቦቻቸው ለውጥ በሌለው የመከራ አዙሪት ውስጥ እንዲከተቱ የሚሆኑበት አንዱ ምስጢር የተሻለ ሐሳብ አፍላቂ አሰላሳዮቻቸውን ቦታ ባለመስጠታቸው ነው፡፡ የፈላስፎቹን ሐሳብ የሚያስተናግድ መሪ ሕዝቡን ወደ ሥልጣኔ ማማ ያወጣል፡፡ የአዋቂዎችን መለምት አክብሮ የሚያደምጥ መሪ ተከታይ ያፈራል

አዲሱን የዕውቀት ጎዳና ፈር በመቅደድ የተዘጋውን የአውሮፓውያኑን የአእምሮ በር የከፈቱት ሳይንቲስቶቹ እና አሳሾቹ ፍራንሲስ ቤከን እና ሬኔ ዴካርት “ሳይንስ” በምክንያትና በተጨባጭ ነገር መነሳት እና ማሸነፍ አለበት፣ የሚል ጥልቅ ሐሳብ ሲያቀርቡ በመኖራቸውም፣ በኋላ ላይ ለተወለዱት የ17ኛው እና የ18ኛው መቶ ክ/ዘመን ሳይንቲስቶች መነሻ መሆን ችለው ነበር::

በ17ኛው እና በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን መካከል ላይ ብቅ ብሎ የራሱን አዲስ ሐሳብ እና ዕውቀት ይዞ አውሮፓን ጉድ ያሰኘው ከእንግሊዝ ሰማይ ሥር በዕለተ ገና የተወሰደው አይዛክ ኒውተን ነው:: ስለ ምድር አፈጣጠር፣ ስለ ሕዋ ሳይንስ፣ ስለ ሶላር ሲስተም አወቃቀር በጥልቀት ያጠና የሒሳብና የሳይንስ ሊቅ አይዛክ ኒውተን፣ የሰው ልጅ ወደ አዲስ የሳይንስ ዓለም እንዲገባ የመጀመሪያዋን የመሠረት ድንጋይ ጣይ ነው:: በኋላ ላይ ትውልድ እና ዘመን እየቆጠሩ የመጡ ሳይንቲስቶች በእሱ ንድፈ ሐሳብ ላይ ቆመው ወደ ሌላ ሳይንሳዊ ግኝት ለመንደርደር ችለዋል::

ሌላው የዛው ዘመን ሊቅ ደግሞ በሥነ ሕይወት ዘርፍ ጥልቅ ምርምር በማድረግ እና በእንስሳት እና በእፀዋት አፈጣጠር ላይ አዲስ ግኝት በማስመዝገብ የሚታወቀው “the father of Modern Physiology” የሚል ማዕረግ የተሸለመው ጆሴፍ ፐርስሊ ነው:: እነዚህ ፈላስፎች በኋላ ላይ ጊዜውን ጠብቆ ለተፈጠረው ሳይንሳዊ እና ሞጋች ኅብረተሰብ የራሳቸውን ጡብ እየደረደሩ አልፈዋል:: ቀጥለው የመጡት እና በአዲስ የሙያ ዘርፍ ግዙፍ አሻራቸውን ያስቀመጡ የፖለቲካ ልሂቃኖቹ ፈረንሳዊው ቻርልስ ሞንትስኪው እና የሥነ መንግሥት አጥኚው እንግሊዛዊው ጆን ሎክ ናቸው:: ዛሬም ድረስ በፖለቲካው

◀ ዓለም ስለዘመናዊ የፖለቲካ አስተዳደር የፃፉት እንደማጣቀሻ የሚነሳላቸው ሞንቶስኪው እና ሎክ የዛን ዘመኑ አስተዳደሪዎች ከጥንታዊው አገዛዝ ወጥተው የሰለጠነ ሥነ መንግሥት እንዴት ማዋቀር እንዳለባቸው ድንቅ የሚባል ምርምር ያደረጉ የፖለቲካ ልሂቃን ናቸው::ጆን ሎክ የሚባለው እንግሊዛዊ ሥነ መንግሥት እና የፖለቲካ ተመራማሪ የነፃ አስተሳሰብ አቀንቃኝ ሊብራሊስት ነበር:: አንድ መንግሥት በዘላቂነት ሕዝቡን መምራት ከፈለገ የግለሰብ ነፃነትን ማስፈን እንዳበት እጅግ የሚደንቅ አዲስ የፖለቲካ ንድፈ ሐሳብ ቀመረ ሲሆን ሌላኛው ሞንትስኪው ሕዝብ በምን ዓይነት የፖለቲካ ሥርዓት መያዝ እንዳለበት ዘመን የማይሽረው አበርክቶት አድርጓል:: Two treatises of Government የሚለው መጽሐፉም ዛሬም ድረስ ማጠቀሻ ነው::

ሌላው ከአዲስ የመንግሥት አወቃቀር ጋር በተያያዘ ደግሞ ሐሳቡን ያስቀመጠው ሳይንሳዊው ተመራማሪ ዣን ነው:: ይሄ ድንቅ የፈረንሳይ ልጅ አብዮትን አቀንቃኝ ነው:: ሥር ነቀል የሥነሥርዓት ለውጥ ለማምጣት አብዮት እጅግ አስፈላጊ መሣሪያ ነው ብሎ በንድፈ ሐሳብ የሚሰበክ ነው:: ይሄ ሰው የእውነት ሊቅ ነው:: በኋላ ላይ ለተወለደው ለታላቁ የፈረንሳይ አብዮት አንድ ምክንያት ሩሶው ስለ ሰው ልጅ ሁለንተናዊ ነፃነት ይፅፋቸው የነበሩት ንድፈ ሐሳቦች ናቸው:: ምክንያቱም እሱም ሆነ ሌላኛው የፈረንሳይ ልጅ ሞንትስኪው ይጽፉት በነበረው አነቃቂ ንድፈ ሐሳብ መነሻ አድርገው ነው ፈረንሳዊያን ወደ አብዮት የተከተቱት:: በ17ኛው መቶ ክ/ዘመን እኩሌታ ላይ የራሱን ሐሳብ ይዞ ብቅ ያለው  የስኮቲሽ አሰላሳይ የሆነው አዳም ስሚዝ ነው:: አዲስ የምጣኔ ሀብት በማመንጨት ፈርቀዳጅ የሆነው ይህ ፈላስፋ ዘዌልዝ ኦፍ ኔሽን የሚል የኢኮኖሚክስ ንድፈሐሳብን በጥልቅ ሁኔታ በመተንተን የሚታወቅ መጽሐፍ በመፃፍ ይታወቃል:: የመጀመሪያው የምጣኔ ሀብት ልሂቁ አዳም ስሚዝ ለግሉ የኢኮኖሚ ዘርፍ ማደግ መንግሥታት ምን ማድረግ እንዳለባቸውና ከዘመናት ድብርቱ ያልተነቃቃውን የአውሮፓ ኢንዲስትሩ በምን ስልተ ምርት መቃኘት እንዳለበት ግሩም ምርምር ያደረገ ነው:: የነፃ ገበያ ሥርዓት አቀንቃኝ የሆነው አዳም ስሚዝ ለዚህም ነው የኢኮኖሚክስ አባት የሚል ህያው ስም የተቸረው::

በ17ኛው ክ/ዘመን ላይ በእጅ ሥራ ባለሙያ "ጉተንበርግ" የተፈጠረው የሕትመት መሣሪያ ደግሞ ሌላው የዛ ዘመን ድንቅ የሚባል አብርክቶት ነበር:: በየዘመኑ ብቅ ብቅ እያሉ የተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሳይንሳዊ ንድፈ ሐሳባቸውን በጥልቅ ምርምር ያበረከቱት ፈላስፎች ይህ የሕትመት ማሽን በዛው ዘመን ባይፈጠር ኖሮ የመንግሥታቱን ዙፋን የሚነቀንቁና አብዮት የሚያቀጣጥሉ ጽሑፎቻቸው ወደ ሕዝብ አይደርሱም ነበር:: በትክክለኛው ዘመን እና ሰዐት በጉተንበርግ ጭንቅላት አማካኝነት ወደ ተግባር የተለወጠው የሕትመት ማሽን ሌላው የ17ኛው እና የ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሰው ልጅ ለዓለም ካበረከታቸው ድንቅ ምርምር ውጤቶች ውስጥ እንደ አንዱ ሆኖ ተመዝግቧል::


> **በብዙ ሀገር መንግሥታት ሕዝቦቻቸው ለውጥ በሌለው የመከራ አዙሪት ውስጥ እንዲከተቱ የሚሆኑበት አንዱ ምስጢር የተሻለ ሐሳብ አፍላቂ አሰላሳዮቻቸውን ቦታ ባለመስጠታቸው ነው**

በ17ኛ እና በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተከሰቱ ድንቅ ፈላስፎች እና ሳይንቲቶች ውስጥ ሳይጠቀስ ያይታለፈው ሰው ቮልቴር የሚባል ብዕሩ እንደ ጦር የሚዋጋ የፖለቲካ ፈላስፋ ነው:: ቮልቴር ብልሹ የመንግሥት አሰራርን ፊት ለፊት በብዕሩ የመንግሥትን (የሥርዓትን) መበስበስ ለሕዝብ በማጋለጥ ሕዝባዊ አብዮት እንዲቀጣጠል ሰፊ ዕውቀት ሲሰጥ የኖረ ግሩም ፀሐፊ ነው:: ይሄ ብዕሩ የሚፈራለት ቮልቴር በተለይ ደግሞ ሃይማኖዊ አስተምህሮቶችን በመመርመር እና ጉድፉን ወደ አደባባይ በማውጣት ሕዝቡ እምነቱ እንዲተች እና እንዲመረመር ያደረገ ግሩም ፈላስፋ ነው:: ሌላው በአይረሴ የምርምር ንድፈ ሐሳቦቹ የሰውን ልጅ አይቀሬ ለሆነው ሁሉን አቀፍ ለውጥ እንዲያመጣ ጥልቅ ሳይንሳዊ ምርምር ካደረጉ አሰላሳዮች ውስጥ "ቻርለስ ዳርዊን" ይነሳል:: በሥነ ፍጥረት (በሥነ ሕይወት) ምርመሩ ታዋቂነትን ያተረፈው "ቻርለስ ዳርዊን" የዛን ዘመኑን ማኅበረሰብ ዐይን ገልጧል:: በዛ ዘመን ከተፈጠሩት ፈላስፎች መካከል አንዱ ተብሎ ስሙ የሚነሳው እና የራሱን ግሩም ሚና የተጫወተው ደግሞ የፖለቲካ ፈላስፋው ቶማስ ሆብስ ነው:: በዜጎች ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የውጭ ወይም የመንግሥት ጣልቃ ገብነት አያስፈልግም በሚል ሕዝብን ሲያስተምር ኖሯል:: የዜጎችን ግላዊ መብት በማክበር እና በመጠበቅ ላይ የተመሠረተ መንግሥት መታነጽ አለበት ብሎ በመፃፍ ዜጎችን የመቀስቀስ ሥራ ሰርቷል:: ቶማስ ሆብስ በደረሰው ሌቪቲያን በሚባለው የፖለቲካ ፍልስፍና መጽሐፉ ታዋቂ ነው::

እንግዲህ በተለያየ ዘመን እና ትውልድ ብቅ እያሉ የሰው ልጅ ከዚህ ቀደም አይቶት የማያውቀውን አዲስ አመለካከት በተለይ ለአውሮፓውያኑ ማስተዋወቅ የጀመሩት ልሂቃኒ ወደ ሰው ልጅ አእምሮ መስረጽ ጀመሩ:: እነዚህ ፖለቲካዊ፣ ሳይንሳዊ፤ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፍልስፍናዎች (ንድፈ ሀሳቦች) ታዲያ ሰው ልጅ ሲከተል የኖረውን ሀይማኖት እንዲፈተሽ እንዲመረመር በሩን ከፈተሉት፤ ለህዝብ ሩቅ የነበሩት የቤተ ክህነት ደጆች እና ፊውዳላዊ መንግስታት ለህዝብ ተፈተሹ፤ በተፈጥሮ ላይ ያለው ዕውቀትም እየተገለጠለት ሲመጣ የማይቻለውን የተፈጥሮ አወቃቀር በድፍረት መመርመር ያዘ፤ መንግስታት በህዝቦቻቸው ፊት ቆመው ተገልጠው ተገመገሙ:: የሰው ልጅ ጠያቂ፤ ሞጋች መሆን ጀመረ:: እና "የምክንያታዊ" ዘመን የሚባለው ታላቁ የtransformation ወቅት ተከሰተ:: እየቆየም በድፍን አውሮፓ ንቃተ ኅሊናው እያደረገ የመጣው ሕዝብ መንግሥታቱን የሰብዓዊና የዲሞክራሲ ጥያቄዎችን በማንሳት መሪዎችን ማስጨነቅ ጀመረ:: እናም የሰው ልጅ አድርጎት የማያውቀውን አብዮት በማንሳት አለምን አጥለቀለቀ:: ለዚህ ደግሞ ሦስቱ ታላላቅ የዓለማችን ሕዘባዊ አብዮቶች ምስክር ናቸው፡ ፤ የአሜሪካውያን፣ የእንግሊዝ እና የፈረንሳይ በእዮቶች ሞጋች ማኅበረሰብ መፍጠርን ማሳያ ምሳሌዎች ተደርገው ይነሳሉ::

እንግዲህ የዓለም የሥልጣኔ ገድል ሲነበብ የልሂቃኑ የሐሳብ አብዮት ለሰው ልጅ ንቃተ ኅሊና መወሰድ ምክንያቶች ሆነዋል:: ታዲያ የልሂቃ የሐሳብ ከፍታ፣ የአሰላሳዮችን ሳይንሳዊ የሆነ ንድፈ ሐሳብ የሚቀበል መንግሥት እና ማኅበረሰብ መኖሩ ሌላው ሁለተኛ ፀጋ ሆኖ እናገኘዋለን:: እንደ ቀድሞዎቹ የእንግሊዝ ነገስታት "የልሂቃኑ ንድፈ ሐሳብ ሀገር ይገነባል" ብሎ የሚያምን፣ አምኖም ፈላስፎች ይበልጥ በሐሳብ ከፍታ እንዲመላለሱ የሚያደርጉ መንግሥታት ማግኘት መታደል ነው:: በ17ኛው መቶ ክ/ዘመን በእንግሊዝ ምድር በሥነ መንግሥታት አወቃቀር ላይ ጥልቅ ፍልስፍና ያደረጉ የነበሩትን የነ ጆን ሎክ ዘመን ልሂቃን ለዚህ ምስክር ናቸው:: የቤተ መንግሥት ሰዎች ከጎናቸው ነበሩና::

በብዙ ሀገር መንግሥታት ሕዝቦቻቸው ለውጥ በሌለው የመከራ አዙሪት ውስጥ እንዲከተቱ የሚሆኑበት አንዱ ምስጢር የተሻለ ሐሳብ አፍላቂ አሰላሳዮቻቸውን ቦታ ባለመስጠታቸው ነው:: የፈላስፎቹን ሐሳብ የሚያስተናግድ መሪ ሕዝቡን ወደ ሥልጣኔ ማማ ያወጣል:: የአዋቂዎችን መላምት አክብሮ የሚያደምጥ መሪ ተከታይ ያፈራል፤ አዎ! የልሂቃኑ የሐሳብ አብዮትን ነፍስና ሥጋ የሚዘራ ንጉስ የእርሱ ዘመን "የሥልጣኔ ዘመን መንግሥት" ተብሎ በብዙ ትውልድ ይዘከራል:: ልሂቃንን እናድምጥ፤ የፈረሰን ሀገር መልሶ የሚገነባ፤የተበላሸን አስተዳደርን መልሶ ለማነጽ ዋናው ሐሳብ መፍለቂያው የነዚህ ጥልቅ አሳቢዎች ብሩህ አእምሮ እንደሆነ ይታወቃል::ከልሂቃኑ መንደር ሀገርን ቀጥ አድርጎ የሚያቆም የሐሳብ ምሶሶ አለ::እናም የልሂቃኑን አብዮት እንውደደው::



ብሩክ መኮንን

# ሲዊዲናዊው ጄነራል በኢትዮጵያ



ሜጀር ጄነራል ኤሪክ ቨርጂን

ዛሬ 83 ዓመት በፊት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የኢትዮጵያን የመንግሥት አስተዳደር በዘመናዊ መልክ ለማደራጀት በማሰብ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ተሰማርተው የሚያገለግሉ በርካታ የውጭ ዜጎችን ቀጥረው ነበር::

ከነዚህ አያሌ የውጭ ዜጎች ውስጥ ስዊዲናውያን የጦር መኮንኖች ይገኙበታል:: ከነዚህ ውስጥም የኢትዮጵያ ነጉሠ ነገሥት የፖለቲካ አማካሪና የመጀመሪያው የጦር ትምህርት ቤት መሥራች የነበሩት ሜጀር ጄነራል ሪክ ቨርጂን ይባላሉ::

በግንቦት ወር 1876 ዓ.ም ስኮቫዲ በተባለ ስፍራ የተወለዱት ኤሪክ ቨርጂን ከልጅነታቸው ጀምሮ በአባታቸው በኮሎኔል አቬራ ቨርጂንን ወታደራዊ ስብዕና ዕያዩ፣ አባታቸውን ለመሆን እየተመኙ ነበር ያደጉት:: የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ በውትድርና ሙያ ሀገራቸውን ለማገልገል ተቀጠሩ::

የስዊድን ንጉሣዊ መንግሥት በጊዜው በስዊድን የሮያል ሴንትራል ጅምናስቲክ ኢንስቲትዩት ለሦስት ዓመታት የሚሰጠውን ትምህርት ተከታትለው እንዳጠናቀቁ ወደ ጦር ኃይሉ ገብተው ሀገራቸውን ማገልገል ጀመሩ:: ይህ የሆነው 1868 ነበር::

ለስድስት ዓመታት በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ተመድበው ግዳጃቸውን ሲወጡ ከቆዩ በኋላ ለመቶ አለቃነት ማዕረግ የሚያበቃቸውን ሥልጠና እንዲወስዱ በሮያት ስዊዲሽ አርሚ ስታፍ ኮሌጅ የእጩ መኮንንነት ማዕረግ፣ ለሁለት ዓመታት የሚሰጠውን የተግባር ፈርጀ ብዙ ትምህርትና ሥልጠና ከወሰዱ በኋላ ከፍተኛ ብልጫ በማስመዝገብ በማዕረግ ተመረቁ::

ወጣቱ መኮንን ኤክ ቨርጂን በአራት ዓመት የሚበልጣትን ኦልጋ ኢዊርሌፍን በ1902 ዓ.ም ስቶኮሆልም ውስጥ በማግባት ትዳር መሠረተ::

ለሁለት ዓመታት የአዛዥነት ኮርስ የወሰደበት የሮያል ስዊዲሽ አርሚ ስታፍ ኮሌጅ፣ በመምህርነት በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ለዓመታት ካገለገለ በኋላ በሻምበልነት ማዕረግ የስታፍ ኮሌጁ ዋና አዛዥ በመሆን ተመደበ::

ሻምበል ኤሪክ ቨርጂን በ1917 ዓ.ም እንዲሁም በ1918 በኦስትሮ ሀንጋሪያን ጦር የአንደኛ፣ የአምስተኛ፣ የአስሮች ሬጂመንት ውስጥ በመመደብ በጦርነቱ ወቅት የጀርመን ጦር ኃይል በምዕራብ ጦር ግንባር ስለሚያካሄደው ውጊያ እና አጠቃላይ እንቅስቃሴ እንዲያጠና በስዊድን የጦር ኃይል ከፍተኛ አመራሮች ተመድቦ ነበር::

ለሁለት ዓመታት በጦር ግንባር ሲንቀሳቀስ ግዳጁን ሲወጣ የቆየው ኤሪክ ቨርጂን ወደ ሀገሩ ሲዊድን እንደተመለሰ በሌተና ኮሎኔልነት ማዕረግ የጦር ኃይሉ የመረጃና የዘመቻ መኮንን ሆኖ ተመደበ:: የስዊድን የምድር ባቡር ጥበቃ ኃይልን እና የተለያዩ የጦር ክፍሎችን በአዛዥነት መርቷል:: ከስድስት ዓመት አገልግሎት በኋላም በ1927 ዓ.ም በሜጀር ጄነራልነት ማዕረግ ተሰጦት የስዊድን አየር ኃይል ዋና አዛዥ ተደርጎ ለአራት ዓመታት ሀገራ አገልግሏል::

በወቅቱ ከኢትዮጵያው ነጉሠ ነገሥት ጋር ጠንካራ የወዳጅነት ግንኙነት መስርተው የነበሩት የስዊዲደኑ ንገሠ ነገሥት አልጋ ወራሻቸውን ኢትዮጵያን ይጎበኙ ዘንድ ወደ ኢትዮጵያ ልከው ነበር:: ለአንድ ሳምንት ያህል በኢትዮጵያ ቆይታ የነበራቸው የስዊድኑ አልጋ ወራሽ አፄ ኃይለሥላሴ ሀገራቸውን ከተቀረው ዓለም እኩል ለማድረግ እያደረጉ ያለውን ጥረት ለማሳካት ሀገራቸው ሲዊዲን ሁለንተናዊ ድጋፍ እንደምታደርግ ቃል ገብተው ነበር ወደ ሀገራቸው የተመሰሉት::

በጊዜው በአሁኑ የካቲት 12 ሆስፒታል በዚያን ጊዜው ቤተሳይዳ ሆስፒታል የሕክምና አገልግሎት የሚሰጡት በተጨማሪ በኢትዮጵያ ▶

◀ የስዊድን መንግሥት ቆንስል በመሆን ሲያገለግሉ የነበሩት ዶክተር ሐርነር የተባሉ ስዊዲናዊ ባለሙያ ለእረፍት ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ልዩ መልዕክታኛቸው አድርገው በመሰየም፣ የስዊድን መንግሥት በገባላቸው ቃል መሠረት ስዊዲናውያን ባለሙያዎችን እንዲሰዱላቸው አስፈላጊውን ሁሉ ጥረት እንዲያደርጉ ይልኳቸዋል::

ይህ የሆነው በኦክቶበር ወር 1933 ዓ.ም ነበር:: ስዊዲናዊው ዶክተር ሔርናርም ወደ ስቶክሆለም በማምራት ለስዊድን ውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በእጅ በተፃፈ ማመልከቻ የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት ለራሳቸው የፖለቲካ አማካሪ እና በዘመናዊ ሁኔታ ለሚያዋቅሩት የኢትዮጵያ ጦር ኃይልን የሚያደራጅላቸው የጦር መኮንን በኮንትራት ለመቅጠር እንደሚፈልጉና ለነዚህ ኃላፊነቶች ብቁ ነው ብሎ የስዊድን መንግሥት ያመነበትን ሰው ይመድብላቸው ዘንድ ጥያቄ ያቀርባሉ::

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ማመልከቻውን ለስዊድን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ያቀርቡና እንዲወደዱበት ያደርጋሉ::የስዊድን ካቢኔ አባላት በንጉሠ ነገሥቱ ጥያቄ ዙሪያ ሰፊ ምክክር ካደረገ በኋላ የስዊድን የጦር ሚኒስትር ለዚህ ኃላፊነት ብቁ ነው የሚለውን ስዊዲናዊ እንዲያፈላልግ ኃላፊነቱን ይሰጣሉ::

የስዊድን የጦር ሚኒስትር የሥራ ኃላፊዎች ከዶ/ር ሐርነር ጋራ በተደጋጋሚ ባደረጉት ውይይት ወደ ኢትዮጵያ የሚላከው ስዊዲናዊ ፣በኢትዮጵያ የሚኖረው ቆይታ ለሁለት ዓመት የሚታደስ የኮንትራት ቅጥር ውል ሊፈረምለት እንደሚገባና ደሞዙና ጥቅማ ጥቅሙን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ነጉሠ ነገሥት መንግሥት ጋራ በርካታ የቴሌ ግራሞች ልውውጥ አድርጎ ከስምምነት ላይ ይደርሳል::

ይህ ከሆነ ከሁለት ሳምንት በኋላ የስዊድን አየር ኃይል ዋና አዛዥ ሜጀር ጄነራል ኤሪክ ቨርጅን ለኢትዮጵያ ነጉሠ ነገሥት የፖለቲካ አማካሪና የኢትዮጵያ ጦር ኃይልን አደራጅ ለመሆን ራሳቸውን በእጩነት ያቀርባሉ::

በስዊዲናውያን ባለሥልጣናትና በሜጀር ጄነራል ኤሪክ ቨርጂን አቻ የሆኑ የጦር መኮንኖች የአየር ኃይል አዛዡ ራሳቸውን በእጩነት ማቅረባቸው እጅግ አስገርሟቸው የዚያን ሰሞን መነጋገሪያቸው አድርጓቸው ነበር::

የስዊድን መንግሥት ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ጋራ ባደረጋቸው ጥቂት የቴሌግራም ልውውጦች፣ ሜጀር ጄነራል ኦሪክ ቨርጂን ለኢትዮጵያ መንግሥት ለሁለት አዓመታት በኮንትራት ለመሥራት የሚያችላቸውን የኮንትራት ውል ተዋውለው ወደ ኢትዮጵያ ለማቅናት ዝግጅት እንዲያደርጉ ይታዘዛሉ::

ሜጀር ጄነራል ኤሪክ ቨርጂን ሜይ 5 ቀን 1934 ዓ.ም አዲሱ ሥራቸውን ለመጀመር ወደ ኢትዮጵያ ሲያቀኑ ከስዊድን ነጉሠ ነገሥት ጉስታቭ አምስተኛ የተፃፉ የግል ደብዳቤን ለንጉሡ ለአፄ ኃይለ ሥላሴ ይዘው ነበር::

ኤሪክ ቨርጂን ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት፣ የንጉሠ ነገሥቱ የፖለቲካ አማካሪ በመሆኑ ንጉሡ የጀመሩት ዘመናዊ የኢትዮጵያ ጦር ኃይልን የማደራጀት፣ የማሰልጠን ሥራ ለመጀመር ሲነሱ ገና ለውትድርና ሙያ የሚያስፈልገውን ሥልጠና ክህሎት የሚሰጥበት የጦር መኮንኖች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት መቋቋም የግድ መሆኑን በመግለፅ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ያሳምናሉ::

ሜጀር ጄነራል ኤሪክ ቨርጂን የኢትዮጵያ የጦር ኃይል ዘመኑ የሚጠይቀውን የውጊያ ብቃት ሳይንስ የሚማርበት የጦር መኮንኖች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ሲቋቋም ወታደራዊ ትምህርት ሥልጠና ለመስጠት ከስዊድን የጦር መኮንኖች ለማስመጣት ያቀረቡት ጥያቄ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ተቃውሞ ይገጥመዋል::

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የፖለቲካ አማካሪያቸው ያቀረቡላቸውን ሐሳብ የተቃወሙት፣ ስዊድኖች ይህ ነው የሚባል የጦር ልምድ የላቸውም፤ ተዋግተውም አያውቁም፤ ለሚቋቋመው ትምህርት ቤት መምህራን እና አሰልጣኞች ለመሆን ቤልጄሞች ይሻላሉ:: በቂ የሆነ ተሞክሮም አላቸው፤ በተጨማሪም ፈረንሳይኛ ቋንቋ ተናጋሪ ስለሆኑ ከኢትዮጵያውያን ጋራ በቶሎ በቋንቋ ሊግባቡ ይችላሉ ከሚል አቋም ተነስተው መሆኑን ለኤሪክ ቨርጂን ያስረዳሉ::

በኦገስት 1934 ዓ.ም ሜጀር ጄነራል ኤሪክ ቨርጂን ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጋራ በነበራቸው ስብሰባ ላይ ስለ ጦር ትምህርት ቤቱ አደረጃጀት፣ የመምህራን አቀጣጠርን በተመለከተ ሰፊ የሆነ ውይይት ካደረጉ በኋላ የጦር ትምህርት ቤቱን አስተዳደር የአዛዥነት ኃላፊነት ለስዊድኖች ወታደራዊ ሥልጠናውን ለቤልጄሞች ለመስጠት ከመግባባት ላይ ይደርሳል:: ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሜጀር ጄነራል ኤሪክ ቨርጂን ለዚሁ ተግባር አምስት ከፍተኛ ልምድና እውቀት ያላቸው ስዊድናውያን የጦር መኮንኖች ከስዊድን እንዲያስመጡ ኃላፊነቱን ይሰጣሉ::

ይህንንም የንጉሠ ነገሥቱን ውሳኔ ተከትሎም ሜጀር ጄነራል ኤሪክ ቨርጂን ቀደም ሲል ከአዲስ አበባ ከተማ በስተምዕራብ አርባ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ የዳግማዊ አፄ ምኒልክ ባለቤት እቴጌ ጣይቱ ብጡል አስርተውት የነበረ፣ በሆለታ ገነት የሚገኝ መለስተኛ ቤተ መንግሥትን ሕንፃ የጦር ትምህርት ቤት እንዲሆን አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ ካመቻቹ በኋላ አምስት ስዊዲናውያን የጦር መኮንኖችን በኮንትራት ወደ ኢትዮጵያ ይመጣሉ::

በዚህም መሠረት ካፒቴን ቫሮኪንግ ታምም፣ ሌተናንት ኤ ደብሊው ቶርበርን፣ ሌተናንት ኤን ኢ ቡቫንጋ፣ የመድፈኛ ሻለቃ አዛዥ የነበረውን ጂ ቪ ሁማን፣ ወታደራዊ መኃንዲሱን ኤ አብሎም የተባሉ የጦር መኮንኖችን ወደ ኢትዮጵያ አስመጥተው ሥራ እንዲጀምሩ አደረጉ::

በሜጀር ጄነራል ኤሪክ ቨርጂን ሌሎቹ ስዊድናውያን ጓደቻቸው Ecole de Gurre Haile Salassie የተሰኘውን የሆለታ የጦር ትምህርት ቤት የመጀመሪያዎቹን አንድ መቶ ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን ተቀብሎ ማሰልጠን ጀመረ::

የገነት ጦር ትምህርት ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ ከተቀበሏቸው ሰልጣኞች ውስጥ ከዓመታት በኋላ በኢትዮጵያ ጦር ኃይል ውስጥ ለከፍተኛ ማዕረግ ኃላፊነት በቅተው የነበሩት ሜጀር ጄነራል ሙሉጌታ ቡሊ፣ ብርጋዴር ጄነራል መንግሥቱ ነዋይ፣ ሜጀር ጄነራል ከበደ ገብሬ ይገኙበታል:: ለአስራ ስድስት ወራት የሚሰጠውን ሥልጠና ለመውሰድ ወደ ጦር ትምህርት ቤት የገቡ የመጀመሪያዎቹ ሰልጣኞች ሥልጠናውን ሳያገባድዱ ነበር የኢጣልያ ጦር ኢትዮጵያን ለመውረር የተንቀሳቀሰው::

የንጉሠ ነገሥቱ የፖለቲካ አማካሪና በፊት ሜጀር ጄኔራል ኤሪክ ቨርጂን ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴን በአማካሪነት ያገለግሉ ከነበሩት ከስዊሱ አበርስን ከአሜሪካዊ ኮልሰንና ከአብዛኛው የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣናት መሳፍንትና መኳንንት ጋራ እጅግ የጠበቀ ግንኙነት ነበራቸው:: በዚህም የተነሳ በኢትዮጵያውያኑ ዘንድ "ነጬ ንጉሥ" የሚል መጠሪያ ስም አግኝተው ነበር::

ለኢትዮጵያ መንግሥት እና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ልክ እንደ ኢትዮጵያዊ በሚያዙት አቋም ምክንያት በተደጋጋሚ በኢትዮጵያ የስዊድን ቆንስላ በራሳቸው ባልንጀሮች ሳይቀር ተቃውሞ እና ውግዘት ይደርስባቸው የነበረው ሜጀር ጄነራል ኤሪክ ቨርጂን፣ ለወራሪው የኢጣልያ መንግሥት የሚያብጠለጥላቸው የኢጣልያ ቁጥር አንድ ጠላት ተደርገው ነበር::

የወልወልን ግጭት እንደ ምክንያት አድርጎ ኢትዮጵያ ላይ በተለያዩ አቅጣጫዎች ወረራ የከፈተው የኢጣልያ ጦር ወደ ኢትዮጵያ መዲና ግስጋሴውን ሲጀምር፣ በስዊድን መንግሥት ወትዋችነት ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ የተገደዱት ሜጀር ጄነራል ኤሪክ ቨርጂን ፣ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ የገቡበትን የሥራ ውል ሳላጠናቅቅ ወደ ሀገሬ አልመለስም ብለው ጦርነቱ እስኪፋፋም ድረስ ያለ እረፍት በሥራቸው ላይ ቆይተው ነው በመጨረሻ ወደ ሀገራቸው የተመለሱት::

ሜጀር ጄነራል ኤሪክ ቨርጂን ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ የስዊድን ተጠባባቂ የአየር ኃይል ጦር አባል በመሆን ከማገልገላቸው በተጨማሪ የስዊድን ቀይ መስቀል የብሔራዊ ሥራ አመራር ቦርድ ሊቀ መንበር በመሆን የስዊድን የውጊያ ሳይንስ አካዳሚ ፕሬዚዳንት በመሆን ለዓመታት ሠርተዋል::

ኤሪክ ቨርጂን የሁለት ወንድ እና ሴት ልጆች አባት ሲሆኑ ኢትዮጵያን በተመለከተ THE Abyssinia I knew የተሰኘ መጽሐፍ በ1936 የፃፉ ሲሆን በስዊድንኛም ኢትዮጵያን የተመለከቱ ሌሎች ሁለት መጽሐፍትን ጽፈው አሳትመዋል::

ሜጀር ጄነራል ኤሪክ ቨርጂን ለአካሄዱዋቸው የረዥም ጊዜ አገልግሎትና አስተዋፅኦ ከስዊድን መንግሥት የሀገሪቱን ከፍተኛ ሜዳሊያ የተሸለሙ ሲሆን የኢትየጵያ መንግሥትም ታላቁን የኢትዮጵያ ኮከብ እንዲሁም የታላቁን የአፄ ምኒልክ ኒሻን ከነ ክብሩ አበርክቶላቸዋል::

ሜጀር ጄነራል ኤሪክ ቨርጅን በተወለዱ በ73 ዓመታቸው ለዓመታት ሲያሰቃያቸው በነበረው የልብ ድካም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው፣ በሜይ 12 ቀን 1950 ዓ.ም በስቶኮሆልም በኖራር ቤጌር ቨኒንግስ ፕሌትስ መካነ መቃብር የቀብር ሥነ ሥርዓታቸው ተፈፅሟል::

ከሜጀር ጄነራል ኤሪክ ቨርጂን ጋራ የሆለታ ገነት የጦር ትምህርት ቤት ካቋቋሙት፣ በከፍተኛ ኃላፊነት የሰሩ ስዊድናውያን የጦር መኮንኖች አብዛኛዎቹ ከኢጣልያ ጦር ሽንፈት በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በሙያቸው ሀገራችንን ሲያገለግሉ እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያወሳሉ:: ስዊድናዊውን ጄነራል ኤሪክ ቨርጂንን ሥራ ሕይወት የዘከርንበት ጥንቅር እዚህ ላይ አበቃን፤ መልካም ገና!

# «የመሸበት የእግዜር እንግዳ!»

ኢትዮጵያዊ በመሆኔ ከሚያኮሩኝ ማሕበራዊ እሴቶ መሀል «የመሸበት የእግዜር እንግዳ!» ብሎ የጠየቀን የመሸበት መንገደኛ ሁሉ ያለ "ማነህ?"፣ "ከየት ነህ?"፣ "ምንድነህ?"፣ "ደምህ ወፍራም ነው ቀጭን?"፣ "ዘርህ ስንዴ ነው ገብስ?" እና "መታወቅያ አሳይ!" ሳንል በክብር ማስተናገድ የራሳችን ክብር ሆኖ መኖሩ ነው፡፡

አንድ ሰው የገጠር መንገድ ሲሔድ ውሎ፣ ያሰበበት ሳይደርስ መንገድ ላይ ቢመሸበት ወደ አንድ ቤት ጠጋ ብሎ «የመሸበት የእግዜር እንግዳ!» በማለት እርዳታ እንዲደረግለት ጥሪ ያቀርባል፡፡ በጥሪው መሰረት የቤቱ አባወራ ካለ አባወራው ወጣ ብሎ ያለ ምንም ማቅማማትና ማንገራገር እንግዳውን አክብሮ ወደቤት እንዲገባ ይጋብዘዋል፡፡

አባወራው በቤት ከሌለ ግን እማወራዋ ወጣ ብላ ትብብር የጠየቀ ወገኗን ታይና ተመልሳ ከመደቧ ላይ አጎዛና ከሌ ወይም ዳውጃ አንስታ ከበር ውጭ ታነጥፍለትና "ትንሽ ይጠብቁ!" ብላ ወደውስጥ ትመለሳለች፡፡ ይህ አንቱታ የእድሜ ገደብን የሚገልጽ ሳይሆን እንግዳ የመሆን ክብር ያመጣው ማዕረግ ነው፡፡

ወደ ውስጥ ገብታ አባወራዋ እስኪመለስ ምግብ ታዘጋጃለች፡፡ በዚህ መሀል አባወራው ከመጣ እንግዳው ከተቀመጠበት በመነሳት «የመሸበት የእግዜር እንግዳ!» ለማለት ሲዘጋጅ ባለቤቱ ደግሞ ሰውየውን በአይኑ "ዘመድ ይሆን!" በሚል ይመረምረዋል፡፡ ወዲያው እንግዳው «የመሸበት የእግዜር እንግዳ!» በማለት ፍቃድ ሲጠይቅ አባወራው ሀጃ ወጣ ብሎ አስነስቶ ወደቤት ውስጥ ይዞት ይገባል፡፡

ለእንግዳ ክብር ተብሎ (በዚህ መልኩ የሚመጣ እንግዳ ስለማይጠፋ) የጠላ ድፍድፍ አይጠፋምና እሱ ይዘጋጃል፣ ከአዘቦቱ ለየት ያለ ምግብም ይሰናዳል፡፡ ልጆች ውሃ ያሞቁና የእንግዳውን እግር ያጥባሉ፡፡ ጨዋታ ይነሳል፡፡ ስለአዝመራ ይወራል፣ መረጃ ይለዋወጣሉ፡፡ በዚሁ ዘመድ መሆን ይከተላል፡፡ መወለድ ቋንቋ ነው ይከተላል፡፡ ክብረት ይከተላል፡፡ ልቅና ይከተላል፡፡ ኢትዮጵያዊነት ይከተላል፡፡

ይህ እንግዳ ተነጥፎለት እንዲያርፍ ይደረግና (ሲሆን ለክብሩ ልጆች ቦታቸውን ይለቁለታል) ሁሉም ወደማረፊያው ይሔዳል፡፡ ሲነጋጋ ማልዶ ይወጣና እየመረቀ ጉዞውን ይቀጥላል፡፡ በዚህ ታሪክ እንኳን እኔ ማዳጋስካር ትኮራለች፡፡

**ሱለይ አደም**

## አስደናቂዋ ኢትዮጵያዊት



ራሄል በላቸው ስዊዲን ውስጥ አንዷ ጸዴ አርክቴክት ናት፡፡ለስቶክሆልም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያንም ጸዴ ዲዛን ሰርታልች አዲስ መጥታ የአዲስን ሞደርን ነን ባይ ህንፃዎች ብታይ በሀፍረት ኢትዮጵያዊነቷን የምትክድ ይመስለኛል፡፡

ናሳ በ2021 ወደ ህዋ ለሚልካት መንኮራኩር በሉሲ ድንቅነሽ ስም ስያሜ አውጥቶላታል፡፡ መንኮራኩሯም ተልእኮዋ ወደ ኋላ የዩንቨርስን አመጣጥ ለማጥናት ነው ተብሏል፡፡

እና ምን ለማለት ነው የኢትዮጵያ ብሄርብሄረሰቦች እስካሁን እየተቀጣቀጣችሁ ነው ወይ ለማለት ነው፡፡

**ሰሚር አሊ**

# 40-40-20 ኢትዮጵያዊ የአፓርታይድ ሥርዓት

ካኢ.ብን አመራሮች ጋር ወደ ድሬ ለመሄድ ከመነሳታችን በፊት ድሬን ምናልባትም እጅግ ቀላሉ የፖለቲካ ቻሌንጅ ያለባት ቦታ ብለን ነበር የፈረጅናት፡፡የጠቅላይ ሚኒስትሩን እስከዛሬ ድረስ ድሬ አለመርገጥ (አንዳንዶቹ ጋር እየደጋገሙ ከመሄዳቸውም በላይ ከቢዝነታቸው አንጻር ትርጉሙ ያልገባንን የጨፍና የገብስ /ማሳ ጉብኝታቸውንም ታሳቢ አድርገን) ድሬን ከፖለቲካ አንጻር የረጋች ሰላማዊ ደሴት ብለን ብንፈርጃት አይፈረድብም ነበር፡፡ ነገርግን እግራችን ከተማዋን ረግጦ የመጀመሪያውን ቡድን ማነጋገር ስንጀምር ግምታችን የተገላቢጦሽ እንደሆነ ለመረዳት የመጀመሪያው ደቂቃ በቂ ነበር፡፡

በወያኔ ቀመር መሰረት (እነሱ" የአባይ ጸሃዬ ሴራ" ይሉታል) የድሬ ህዝብ በእናት ሀገሩ እንደ ባእድ የበይ ተመልካች ሆኖ የሚያደርገው ጠፍቶት ቁጭ ብሏል፡፡ማናቸውም ነገሮች… ከቀበሌ የስልጣን ወንበር እስከ የአነስተኛና ጥቃቅን ሼዶች ደረስ የሚደለደለው በዚሁ ባልተጻፈ የአፓርታይድ ስርአት ቀመር ነው፡፡ አስር ሱቆች በከተማው አስተደደር ከተሰሩ 4ቱ ለሶማሌዎች 4ቱ ለኦሮሞዎች ሲከፋፈሉ 2ቱ ደግሞ ለተቀሩት ድሬ ውስጥ ሊገኙ ለሚችሉ 80-2…78 ብሄረሰቦች "የሚዳረሱ" ይሆናል ማለት ነው፡፡

ይህ እንግዲህ በሁሉም መስክ የሚደረግ ክፍፍል ነው…ምናልባትም አታምኑም ይሆናል እንጂ የድሬዳዋ የእግር ኳስ ክለብ የደጋፊዎች ማህበር እራሱ በዚሁ ቀመር ከየቀበሌው በተውጣጡ ወጣቶች የተዋቀረ እንደሆነ ሰምተናል….በእውነት የመቻቻል የፍቅር እና የአብሮነት ከተማ በሆነችው ድሬ ላይ የሚሰራው ስራ በጣም ያማልም ..ያጸይፋልም…

የሆስፒታል ዶክተሮች እንኳን የኪራይ ቤት ለማግኘት በዚሁ ቀመር እድላቸውን መሞከር ያለባቸው መሆኑን መስማት ያሳፍራል( ማን ያውቃል የሆስፒታል አልጋም በዚሁ መልክ ለበሽተኞች የሚዳረስ ይሆን ይሆናል!)

የትአለ ህገመንግስቱ!?

የት አለ እኩልነት!?

የት አለ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት!?

እንዴት ሰው በገዛ ሀገሩ ተወልዶ ባደገበት ቀዬ አንተ ከሌላው ታንሳለህ ተብሎ አይኑ እያየ ከተማው ውስጥ አንድ ቀን እንኳን አይቶት በማያውቀው ከሌላ ቦታ በመጣ ሰው ብልጫ ይወሰድበታል !?

ቡድኖቹ ችግራቸውን ሲዘረዝሩ እኔ አእምሮ ውስጥ ይመላለስ የነበረው በቅርቡ በወዳጃችን እና አባላችን ጥላሁን ግርማ ወደ አማርኛ የተመለሰው "የአመጸ ልጅ" የተሰኘ የደቡብ አፍሪካን የአፓርታይድ ስርአት ክፋት የሚገልጸው ምእራፍ ነበር..ደራሲው ሲስተሙን "አፓርትሄት" (ከፋፍለህ አጠላላ) በማለት ይገልጻዋል፡፡ ወያኔ ለድሬ የመረጠችው ይሄን አስነዋሪ አፓርትሄት ስርአት ነበር፡፡

አዎ ድሬ ዛሬ በአፓርትሄት ጎዳና ላይ እንደምትገኝ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

በተለምዶ 20% የሚባለው የህብረተሰብ ክፍል(በነገራችን ላይ 20% ይባላል እንጂ ቁጥሩ ከዚህ በአያሌው እንደሚበልጥ እንኳንስ አይን ያለው ሰው ማየት የተሳነው ሰው እንኳን ከተማዋ ውስጥ ለግማሽ ቀን ወክ ቢበላ የሚረዳው ሃቅ ነው) በገዛ ሀገሩ እየተደረገበት ባለው በደል ቀን ተቀን እያረገዘ ያለው የመገፋት እና የቁጭት ስሜት ነገ ምን ሊፈጥር እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡

አዲሱ ጠቅላይሚኒስቴር ይሄንን ነውረኛ ስረአት ወዲያ አሽቀንጥረው እንደሚጥሉት እናምናለን ወይም ማመን እንፈልጋለን፡፡ ይህ እስከሚሆን ግን ንቅናቄያችን አምርራ ከምትታገልላቸው ጉዳዮች ውስጥ "ኢትዮጲያዊውን የአፓርታይድ ስርአት" በደማቁ በፖለቲካ ፕርግራማችን ላይ እንደጻፍነው ላነጋገርናቸው ሁሉ(ይህን አምርረው ለሚታገሉት" ሳተናው" ተብለው ለሚታወቁት ስብስቦች ጨምሮ) ነግረናቸው ነበር የመጣነው፡፡

አዲስአበባ ከገባው በኋላ ምላሴ እና ጉሮሮዬ ላይ በድሬ ሳጣጥማቸው የቆየኋቸው ጣፋጭ ምግቦች ገና ባይጠፉም ከጣፋጭ ምግቦቻቸው ይልቅ የተገፉት ወጣቶች ፊት ላይ ያየሁት ምሬት አእምሮዬ ላይ ጉልህ ድርሻ ይዟል፡፡

"አንደበት ላጣ ህዝብ ካልተናገሩለት

ወንጀል አይሆንም ወይ ወገኑ ነኝ ማለት"

…አልነበር ሃይሉ ገሞራው ያለው ፡፡

**አንዱአለም ቡኩቶ ገዳ**

# የታህሳስ ወር በታሪክ ውስጥ

### ታህሳስ 3 ቀን 1906 ዓ.ም
ዳግማዊ አፄ ሚኒልክ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ::

### ታህሳስ 3 ቀን 1919 ዓ.ም
“አባ መላ” በመባል የሚታወቁት የዳግማዊ አፄ ሚኒልክ፣ የአቤቶ ኢያሱ ፣የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ሚኒልክ የሥልጣን ዘመናት የጦር ሚኒስትር የነበሩት ፣ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ::

### ታህሳስ 3 ቀን 1810 ዓ.ም
በኢትዮጵያ ዘመነ መሳፍንት ሲጀመር ከዙፋናቸው ወርደው አክሱም በስደት ለይ የነበሩ እና “ተፍፃሜ ነገሥት” የሚባል ቅፅል ስም የተሰጣቸው ቀዳማዊ አፄ ተክለ ጊዮርጊስ በዚህ ቀን ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: ከቀናት በኋላም በአክሱም ጨለቆት ሥላሴ ተቀበሩ::

### ታህሳስ 4 ቀን 1953 ዓ.ም
በወንድማማቾቹ መንግሥቱ ነዋይ እና ግርማሜ ነዋይ የተጠነሰሰው የታህሳስ ግርግር በመባል የሚታወቀው የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ተጀመረ::

### ታህሳስ 5 ቀን 1953 ዓ.ም
የለውጥ ፈላጊ ናቸው የተባሉትን ልዑል ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴን በጠቅላይ ሚኒስትርነት መሾማቸውን፣ አልጋወራሹን ልዑል አሰፋ ወሰንንም በማስማማት ፣መንግሥት በቆረጠላቸው ደመዎዝ እየተዳደሩ ለሕገ መንግሥቱ የሚገዙ ንጉሥ ሆነው እንደሚያገለግሉ ራሳቸው ለሕዝቡ በሬድዮ እንዲያስተላልፉ አደረጉ::

### ታህሳስ 7 ቀን 1953 ዓ.ም
የክቡር ዘበኛ መኮንን የነበሩ ሻምበል ደረጀ ኃይለማርያም ማሞ ልጅ ፣የንጉሠ ነገሥቱ የልጅ ልጅ፣ የልዕልት ሶፊያ ደስታ ባለቤት፣ የመፈንቅለ መንግሥቱን አድራጊዎች በመቃወም የቤተ መንግሥቱን አጥር በታንክ አፍርሰው ወደ ግቢ ሲገቡ በመፈንቅለ መንግሥቱ አድራጊዎች በተተኮሰ ጥይት ተገደሉ::

### ታህሳስ 9 ቀን 1954 ዓ.ም
በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ገነተ ልዑል ይባል የነበረው ቤተ መንግሥት የከፍተኛ ትምህርት የምርምር ማዕከል እንዲሆን ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ በሚል ስያሜ መርቀው ከፈቱት::

### ታህሳስ 10 ቀን 1947 ዓ.ም
የአሁኑ የሀገር የፍቅር ቴአትር ቤት አዳራሽ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የአሜሪካን የመጀመሪያ ጉብኝታቸውን የፎቶ ግራፍ አውደ ራዕይ ለማቅረብ በተወጠነ አላማ መሰረት፣ ተመርቆ ተከፈተ ::

### ታህሳስ 01 ቀን 1930 ዓ.ም
የፋሽስት ኢጣልያ መንግሥት ሀገራችንን በግፍ ከወረረ በኋላ በዓለም አቀፍ ደረጃ በደረሰበት ውግዘትና ነቀፋ የንግድ እገዳ ምክንያት በማድረግ ከሊግ ኦፍ ኔሽን ከዓለም መንግሥታት ማኅበር አባልነት ወጣች::

### ታህሳስ 11 ቀን 1967 ዓ.ም
ሐምሌ 1 ቀን 1966 ኢትዮጵያ ትቅደም የሚለውን መፈክር የነደፈውና ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መስከረም 1 ቀን 1967 ዓ.ም ከሥልጣን ያስወገዳቸው የጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ 60ዎቹን ከፍተኛ ሹማምንት ከገደለ ከአንድ ወር በኋላ የኢትዮጵያ ኅብረተሰባዊነት (የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም) በይፋ አወጀ::

### ታህሳስ 12 ቀን 1929 ዓ.ም
ሁለቱ ስመጥር አርበኞች ደጃዝማች አበራ ካሳ እና ወንድማቸው ደጃዝማች አስፋወሰን ካሳን በወቅቱ ኢትዮጵያን በኃይል የያዘው የፋሽስት ጦር በሰላም እጃቸውን ቢሰጡ ምንም እንደማይደረጉ ቃል ተገብቶላቸዋል:: ለኢጣሊያዊው ጄነራል ትራኪያ እጃቸውን ሰጡ:: ጄነራል ትራኪያ ወንድማማቾቹን ፍቼ ላይ በዚህ ቀን አስረሽኖ አንገታቸውን አስቆረጣቸው::

### ታህሳስ 12 ቀን 1967 ዓ.ም
ደርግ የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ሶሻሊዝምን መመሪያው ማድረጉን ይፋ ካደረገ ማግስት የብሔራዊ የእድገት በኅብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ የተሰኘ መርሃ ግብር በሥራ ላይ እንዲውል አደረገ::
በዚሁ ቀን 60 ሺህ የሁለተኛ ደረጃ የዩንቨርስቲ ተማሪዎች እና መምህራን በመላው ሀገሪቱ እንዲሰማሩ አደረገ::

### ታህሳስ 13 ቀን 1922 ዓ.ም
የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አጎት ደጃች ወልደስላሴ ለመንግሥት ሥራ በአውሮፕላን ወደ ደሴ ተልከው ሲመለሱ አደጋ ተፈጥሮ የአውሮፕላኑን የመቀመጫ ቀበቶ ሳያስሩ ቆመው ሲፎክሩ አውሮፕላኑ በድንገት ሲያርፍ የአውሮፕላኑ ጣሪያ ራሳቸውን በኃይል ስለመታቸው በአውሮፕላኑ ከነበሩ ተሳፋሪዎች ውስጥ እሳቸው ብቻ በደረሰባቸው ጉዳት ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: በዚህም በኢትዮጵያ ታሪክ በአውሮፕላን አደጋ በመሞት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ እኚህ የራስ መኮንንን ወንድም ደጃች ወልደ ሥላሴ መሆናቸው ታሪክ መዝግቦታል::

### ታህሳስ 14 ቀን 1928 ዓ.ም
የፋሽስት ኢጣሊያ ጦር በራስ እምሩ ኃይለሥላሴ በሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ላይ የመርዝ ጋዝ ጭስ አርከፈከፈ::

### ታህሳስ 14 ቀን 1967 ዓ.ም
በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ መንግሥት በብሔራዊ ደረጃ የሚከበሩ በዓላት ዝርዝር ውስጥ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የሚያከብሯቸውን ሁለት ዐበይት በዓላትን በይፋ ያከብሩ ዘንድ የሚፈቅደውን ድንጋጌ ይፋ አደረገ::

### ታህሳስ 15 ቀን 1905 ዓ.ም
የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግስት የምድር ባቡር ኩባኒያ በኋላ ላይ የኢትዮጵያና የፈረንሳይ የምድር ባቡር ኩባኒያ የሐዲድ ዝርጋታ ሥራ በዚህ ዕለት ከጅቡቲ አዲስ በተመሰረተችው ድሬድዋ ከተማ ደረሰ::

### ታህሳስ 18 ቀን 1967 ዓ.ም
የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ደርግ በሬዲዮና በቴሌቭዥን ስርጭት የወሰነውን ማሻሻያ ይፋ አደረገ:: በዚህም መሰረት በሬዲዮ የኦሮሚኛ ስርጭት የአየር ሰዓት ሲፈቅድ በአንፃሩ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ስርጭጥን ሰረዘ፤ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚተላለፉ ፕሮግራሞችን በሬዲዮም በቴሌቭዥንም ቅነሳ እንደሚደርግ አሳወቀ::

### ታህሳስ 19 ቀን 1962 ዓ.ም
የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ማኅበር ፕሬዝዳንት ጥላሁን ግዛው በፖሊስ ተገደለ:: ይህ ድርጊትም በርዶ የነበረውን የተማሪዎች አመፅ እንደገና እንዲቀጣጠል አደረገ::

### ታህሳስ 20 ቀን 1951 ዓ.ም
የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአፍሪቃ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የመጀመሪያውን ስብሰባውን የተመድ ዋና ፀሐፊ ዳግ ሃመር ሾልድ በተገኙበት ሥነ ሥርዓት በአዲስ አበባ ከተማ አካሄደ::

### ታህሳስ 21 ቀን 1948 ዓ.ም
የኢትዮጵያ አየር መንገድ በዚህ ዕለት ተመሠረተ::

### ታህሳስ 23 ቀን 1967 ዓ.ም
የኢትዮጵያ የጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ የመንግሥት የግል ባንኮችን የኢንሹራንስ ኩባኒያዎችን በሙሉ የብሔራዊ ንብረት አድርጎ ወረሳቸው::

### ታህሳስ 24 ቀን 1882 ዓ.ም
የኢጣልያ መንግሥት ከመረብ ምላሽ ይባል የነበረውን የኢትዮጵያን ግዛት “ኤርትራ” ብሎ በመሰየም የቅኝ ግዛቱ አደረገ::

### ታህሳስ 28 ቀን 1928 ዓ.ም
የቅዱስ ጊዮርጊስ የእግር ኳስ ቡድን አዲስ አበባ ውስጥ አራዳ አካባቢ ተመሠረተ::

### ታህሳስ 29 ቀን 1879 ዓ.ም
የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ሠራዊት የሐረሩ አሚር አብዱላሂ ሠራዊት በሜታ ወረዳ ምስራቅ ሐረርጌ ውስጥ በምትገኘው ጨለንቆ ላይ ውጊያ ገጥመው ከ70 ደቂቃ ውጊያ በኋላ የአሚሩ ሰራዊት ተሸንፎ ወደ ሐረር ሸሸ የምኒልክም ጦር እግር በእግር ተከታትሎ ሐረርን በቁጥጥሩ ሥር አደረገ::

### ታህሳስ 17 ቀን 1980 ዓ.ም
ኢትዮጵያ ባዘጋጀችው የምስራቅና መካከለኛው አፍሪቃ የእግር ኳስ ዋንጫ (ሴካፋ) ውድድር ዙምባቤዌን የኢትዮጵያ ቡድን በፍፁም ቅጣት ምት በማሸነፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ዋንጫ በላች::
ዋንጫውን የሰጡት የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ዋንጫው ለቡድኑ አምበል ለገብረ መድህን ኃይሌ ከሰጡ በኋላ ባደረጉት ንግግር 10 ሺህ ተመልካች የሚይዝ ዘመናዊ ስታዲየም ለመሥራት ቃል ገቡ::

### ታህሳስ 26 ቀን 1926 ዓ.ም
በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የንፋስ ስልክ የሬድዮ ስርጭት ተጀመረ::

### ታህሳስ 23 ቀን 1917 ዓ.ም
የብርሃንና ሠላም ጋዜጣ ተመሠረተ::

# ግዮን መጽሔት

## በአጭር ጊዜ ገበያ ውስጥ ለመግባት የቻለችው ግዮን የእርስዎ መፅሔት

መጽሔታችን ከተጀመረች ጀምሮ የእናንተ ውድ አንባቢያን አቀባበልና አስተያየት ሳይለየን ቆይተናል። በአዲስ ዓመት በአዳዲስ አምዶች

**ትምህርት፡-** በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ያሳያል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ፍኖተ ካርታን በተመለከተና ከትምህርት ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች

**ኢትዮጵያዊነት፡-** አገራችን የአንድነት ጉዞ በምትጀምርበት ወቅት ኢትዮጵያዊነት ምንድን ነው? በሚልና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በተከታታይ እናቀርባለን።

በእነዚህ አምዶች ላይ ባለሙያ የሆናችሁና የተለየ ሀሳብ አለን የምትሉ ተሳታፊዎች በኢሜል ፅሁፍ መላክ ትችላላችሁ።

በልዩ አቀራረብ፣ በአዳዲስ አምዶችና በሳል ፀሃፊያን በመታገዝ

## በየሳምንቱ ቅዳሜ ከእጅዎ ትደርሳለች።

ቢጨመር ፣ ቢሻሻል የሚሉትን ከወዲሁ ይጠቁሙን!





+251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 122333

www.faceboook.com/enqu2013
Facebook
Gihon-meg Fekadu
ኢ-ሜይል:
enqu2013@gmail.com